# የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ዘመን

እሺ። አሁን፡ እንደሚመስለኝ፡ ያ መብራት ቢጠፋ ይሻላል። እሺ።

2 በጌታ አገልግሎት እዚህ በመገኘታችን ዛሬም በጣም ደስ ብሎናል። ትናንት ማታ የሺህ አመት መንግስት የደረሰ ያህል ተሰምቶኝ ነበር። ይመስለኛል የቀረቡልን ጥቂት ጥያቄዎች፡ እዚህ ተቀምጧል፡ እ—እንዲጸለይላቸው የፈለጉ… የጸሎት ጥያቄ ይመስለኛል… እና ኪሴ ውስጥ አስገባዋለሁ። እና… የቻልኩትን ያህል—በጥሩ ሁኔታ ለመመለስ እሞክራለሁ።

3 እንደው ያን… ጨረሩ ፊት ለፊቴ ስለሆነ፡ ከቻለ ወይም ከቻላችሁ ዶክን "አጥፋለት፡" በሉት፡ ስለዚህ፡ ከመድረክ መብራት ስር እንዳልሆን ነው። ታውቃላችሁ፡ እኔ—የመድረክ መብራት ስር ሆነው እንደሚሰብኩ ሰባኪዎች አይደለሁም። ስለዚህ እሱ ባይኖር የተሻለ ነው፡ ብዬ አስባለሁ። በመጨረሻ…

4 ዶክን፡ አምጡልኝ ያልኩትም ራሴ ነኝ። አየህ፡ አሁን ንሰሓ እየገባሁ ነው፡ ንሰሓ እ—እየገባሁ ነው። ኦህ፡ ኦህ፡ አንተስ… ? እዚያው አብርተኸው ቀዶ ጥገና ብታደርግበት አይሻልም? [ወንድም ብራንሃም ከወንድሙ ጋር ውይይት አደረገ፡ ዶክ—አርታዒ።] ኦህ፡ በቃ፡ ተውት። አዎን። በቃ፡ ተውት። አይ፡ ተው! ምናልባት፡ እንዳትጥለው። አዎን። አሁን ይሻለኛል። አንዳንድ ጊዜ… ታውቃላችሁ፡ ፊት ላይ የሚያበራ መብራት አልወድም። እና—በተሻለ ማየት በምችልበት ላይ በርቷል። አመሰግናለሁ፡ ጌታዬ። ዋጋ ያስከፍለዋል።

5 ታውቃላችሁ፡ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መጨረስ አትችሉም። እና ዛሬ በዚህ ላይ ሳጠና፡ ለሚስቴ ተናገርኳት፡ እና እንዲህ አልኳት፡ "ኦህ፡ ማይ! ከዚህ ብቻ አምሣ ስብከት የምሰብክበት በቂ ርዕሶችን አገኘሁ አልኳት።" አያችሁ? በእነርሱ ዘንድም… ዋና ዋናዎችን ከመነካካት በቀር ይህን የምናደርግበት መንገድ የለም፡ ምናልባት መጽሐፉን ስንጽፍ ከዚያ የበለጠ ለማግኘት እንሞክራለን።

6 ወንድሜ፡ አላየሁህም ነበር። እንዴት ነህ፡ ወንድም ዌስት? የወንድም ዳልተን ቤተሰብ የመጨረሻው አባል መግባቱን፡ ጥሩ ዜና ሰምቻለሁ፡ ሌላ ወንድ ልጅ… ሌላ ሴት ልጅ። አስረኛ፡ ነው አይደል? ዘጠኝ። በአዲሱ አገልግሎት ውስጥ ጌታ ቤተሰብህ በሙሉ ይድናል ብሎ እንደተናገረው… ታስታውሳላችሁ። ምን እያልኩ እንደነበረ ሳላውቅ፡ ቆሜ እየጸለይኩላቸው ነበር፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለ፦ "ቤተሰብህን እሰጥሃለሁ።" አያችሁ? ኧህ-ህህ። ይኸው እያንዳንዳቸው፡ እዚህ አሉ። ጌታ እንዴት እንደሚሰራ አያችሁ? ቃሎቹ ፍጹም፡ በጭራሽ፡ በጭራሽ የማይወድቁ፡ መሆናቸውን ተመልከቱ። እንግዲህ፡ ወደ መለኮታዊ ፈውስ መግባት አንፈልግም፡ የቻልነውን ያህል… በዚህ በትንቢታዊው ክፍል በኩል፡ መቆየት እንፈልጋለን።

7 አሁን፡ ዛሬ ማታ መናገር የምፈልገው ነገር፡ በተለይ ከቻልኩ፡ የዚህ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ታሪካዊው ዳራ ውስጥ መግባት ነው፡ ዛሬ ማታ ወደ ሁለተኛ… ወይም ሦስተኛው ቤተ ክርስቲያን ዘመን እንገባለን። ደስ እያላችሁ ነው? እጅግ ድንቅ ነው። ጌታ ኢየሱስ እንዴት እንደባረከን እና እነዚህን

ነገሮች እንደሰጠን በእውነት የሚያስደንቅ ይመስለኛል፡ በሙሉ ልባችንም እናመሰግነዋለን፡ ጊዜው ሳይደርስ ወደፊት የሚሆነውን ነገር አስቀድሞ አሳውቆናልና። መጨረሻውን ከመጀመሪያው ያውቀዋል፡ ስለዚህ እኛም በጣም ደስተኞች ነን። ስለዚህ ጌታ እንደሚባርከን እናምናለን።

8 ትናንት ማታ፡ መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን፡ አስተውላችኋል (ስብከቱ ካለቀ በኋላ) ሦስት መልዕክቶች እና ሦስት ነፍሳት ሰጠን። በትክክል። መንፈስ በተናገረ ጊዜ፡ በመጨረሻው ትርጉም እንደገና መጣና፡ በድጋሚ፡ እንዲህ አለ፡ "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን... " ኦህ፡ "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ ያለው ይስማ።" መንፈስም... በቤተ ክርስቲያን በሥጦታው በኩል ይናገራል። እነሆ፡ ቤተ ክርስቲያንም ይህን አክብራ መያዝ ይሁንላት፡ እናንተም፡ አክብራችሁ ያዙ። ተጠንቀቁ፡ ሰይጣን ይመጣልና፡ በጉዳዮች ላይ ጫፍ ወስዶ ሊያታልላችሁ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አረጋግጡ። መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፡ ስለ ለሚሆነው ነገር ፊት ለፊት ይናገራልና። ይህም ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ነው። አያችሁ? በእነዚህ ነገሮች ትሑታን ከሆናችሁ፡ እግዚአብሔር አብዝቶ ይሰጣችኋል። አያችሁ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመራችሁ ቀጥሉ። እና...

9 አሁን፡ ሰው ደውሎ እየጠየቀን ነበር... ሰዎች ዛሬ ደውለው የፈውስ አገልግሎት መቼ እንደሚሆን ይጠይቁ ነበር። አሁን፡ ይህ አገልግሎት እንዳበቃ፡ በሚቀጥለው እሁድ ምሽት፡ ለጥቂት ቀናት እሄዳለሁ፡ ጉሮሮዬን ትንሽ አሳርፈዋለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ምናልባት በሚቀጥለው እሁድ፡ ከዚያ ቀጥሎ ባለው እሁድ ማለዳ፡ የፈውስ ፕሮግራም ይኖረናል። መቼ ይሆናል... ያ ቀን ምን እንደሚሆን አላውቅም፡ ነገር ግን ከዚያ ሳምንት በኋላ... በ18፡ እሁድ ጥዋት-... መሆን ይችላል፡ ወንድም ኔቪል? እህም? [ወንድም ኔቪል፡ "አዎን፡ ጌታዬ" በማለት መለሰለት።—እርታዒ።] እሁድ ጥዋት፡ በ18፡ ለታመሙ ይጸለያል።

10 በዚህ አጋጣሚ፡ ስለ ፓስተራችን፡ ለመናገር እድል አላገኘሁም ነበር፡ እናንተ ግን ሁላችሁ፡ ፓስተራችንን ለማግኘት ሞክሩ። በክርስቶስ—እውነተኛ የማትጠራጠሩበት ወንድም ነው። በሜቶዲስት ዳራ ከቅድስና ጋር ያደገ... ወንድም በማግኘታችን ደስተኞች ነን። ኦርማን ኔቪልን ሁላችንም እናውቀዋለን፡ እዚህ ያለ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። በህይወቱ ላይ ማንም ጣት አይቀስርበትም። እንደው... ይህ እንድናገርለት አይፈልገኝም፡ ይሁን እንጂ ከሄደ በኋላ የአበባ ጉንጉን ከማስቀመጥ፡ እንቡጥ አበባ አሁን ብሰጠው ይሻለኛል። አያችሁ? ጊዜውም አሁን ነው።

11 አንድ ቀን ማታ ከቤተ ክርስቲያን እየወጣን አንድ ሰው መጣና "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ በእውነት ስብከትህ እጅግ አደነቅኩት፡" አለኝ።

እኔም "አመሰግናለሁ፡" አልኩት።

12 (እዚሁ ተበርናክል፡ ከብዙ አመታት በፊት ነው) በር ላይ አንድ ሰው ቆሟል፡ አገልጋይ ነው፡ እሱም "ኧረ፡ እግዚአብሔር ይባረክ፡ እኔ ማንም ሰው እንዲህ እንዲለኝ አልፈልግም፡" አለኝ። አያችሁ? "ክብሩ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንዲደርስ እፈልጋለሁ፡" አለ።

እኔም “መድረሱ’ማ፡ አይቀርም።” አልኩት። አያችሁ? “መቼም፡ እኔ በበኩሌ፡ ደስ ይለኛል፡” አልኩት። “እውነተኛ ብሆን ይሻለኛል፡” አልኩት። “እኔ በጣም ደስ ይለኛል፡” አልኩት።

እሱም፡ እንዲህ አለኝ፡ “ኧረ’ኔስ፡ እግዚአብሔር ይባረክ ሰዎች ስለ እኔ እንዲህ ሲሉ ደስ አይለኝም!”

እኔም “በእኔ እና በአንተ መካከል አንድ ልዩነት አለ፡ እኔ ቅን ነኝ፡ አንተ ግን አይደለህም፡” አልኩት።

13 ሰው ሁሉ ይህን ይወዳል… ለምሳሌ አንድ ህጻን ልጅ፡ ጎሽ ስትሉት፡ ስራውን በተሻለ መንገድ ያደርጋል። አያችሁ? ልክ ነው። አያችሁ? እግዚአብሔርም፡ ልጆቹ መልካም ባደረጉ ቁጥር፡ ሁልጊዜ ጎሽ ማለት ይወዳል። በተሳሳቱ ቁጥር ልትነቅፏቸው ከወደዳችሁ፡ መልካም ሲያደርጉ ጎሽ ማለት ምን ከበዳችሁ? አያችሁ?

14 ስለዚህ ወንድም ኔቪል በዚህ ተበርናክል ውስጥ የመንጋው መጋቢ በመሆኑ እግዚአብሔርን በእውነት አመሰግናለሁ። የኋላ ታሪኩ ከሜቶዲስት የነበረ ይህ ሰው፡ ሰናየው… ለምን፡ በተሳሳተ ገብታ መብላት ፈልጎ ነበር። ስለዚህ… በታላቁ መንፈስ ቅዱስ—ፍለጋ ግን፡ አሁን ወደ እነዚያ ስጦታዎች ደርሷል፡ እና አእምሮውን መጠቀም በተወ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዴት አቀላጥፎ እንደሚጠቀምበት። ትርጉሙን በተመሳሳይ ሪትም፡ በተመሳሳይ ፍሰት፡ ሰሞችን እና ተውላጠ ሰሞችን ሳይቀር፡ ወዲያው በፍጥነት እንዴት እንደሚመልስ፡ ተመልከቱ።

15 ይሄኛው ወንድማችንም፡ ጁኔር ጃክሰን ይመስላል… ወይስ ሌላ ሰው ነው። እንግዲህ፡ እንዲህ እያልኩ መቀጠሌ አይቀርም፡ ጁኒዬ። ስለ ጁኒ ጃክሰን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡ ይህ ወንድምም በእርግጥ ታላቅ የጌታ ስጦታ አለው።

16 ሁልጊዜም ትሕትናችሁን አትተው። እንግዲህ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ድርሻ አለው፡ ይሁን እንጂ ለሌላ ነገር መጠቀም በጭራሽ እንዳትሞክሩ፡ ከሌላው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር ይዋሃድ። ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። አያችሁ? አያችሁ? በልሳን መናገር፡ ልሳንን መተርጎ ሁላችሁም አትፈልጉ።

17 መልካም የሆነውን ለማድረግ ሞክሩ መልካምነታችሁ ይቀጥል፡ ክፋትን፡ ቂምን አትያዙ፡ ምንም አይነት መራራነት አይኑርባችሁ። ሰዎች የቱንም ያህል መጥፎ ቢሆኑ ስለ እናንተም ቢናገሩባችሁ፡ በእነርሱ ላይ በልባችሁ ፈጽማችሁ ክፋትን አታስቡ፡ ‘ምክንያቱ ዲያብሎስ በዚያ መንገድ መግቢያ አግኝቶ፡ ስራውን ሊሰራ ይችላልና። በአምላካዊ ፍቅር፡ በመናዘዝ፡ እና በማስተካከል ብቻ እየሸፈናችሁ፡ ክፉ ለሚያደርጉባችሁ ሁሉ መልካም አድርጉ። “መልካም ለሚያደርጉላችሁ ብቻ መልካም ብታደርጉ፡ ምን ይጠቅማል፡” አለ ኢየሱስ፡ “ቀራጮችስ እንዲህ አይደሉምን? ” አያችሁ? ኃጢአተኞች፡ እና ሰዎች ሁሉ መልካም ለሚያደርጉላቸው መልካም መሆን ይችላሉ። ነገር ግን መልካም ለማይሆኑላችሁ መልካሞች ሁኑ፡ ምንም ለማይሠሩላችሁ አንድ ነገር አድርጉ። በአንተ ላይ ክፉ ለሚናገር ሰው መልካም ቃል ተናገር፡ በዚህ መንገድ መራራነትን

ሁሉ ከልባችሁ አስወግዱ፡ ስለዚህ ፍቅርን እስከጠበቃችሁት ድረስ፡ ከሰው ሁሉ ጋር ሁሌ በፍቅር ትሆናላችሁ።

18 ምናልባት "እንዲህ፡ አደረጉብኝ... " ትል ይሆናል። እኛ ፈራጅ አይደለንም፡ ፍርዱ ለእግዚአብሔር ነው። መቼስ ይህ ምስኪን ሰው እንዲጣል አትፈልጉም፡ ትፈልጋላችሁ'ዴ? ምንም ቢሆን፡ እንዲህ አትፈልጉም። እያስፈልጋችሁም፡ ስለዚህ ደጎች ልትሆኑላቸው ሞክሩ። "ፍቅርም የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና።" ኧሀ-ህህ። አዎን፡ ወዳጄ። ፍቅር፡ ክርስትያናዊ፡ እና አምላካዊ፡ መልካም ፍቅር።

19 አንድ ሰው መጥቶ "ሆሊ-ሮለር" ቢላችሁ ወይ ሌላ መጥፎ ስድብ ቢናገራችሁ፡ ልክ—ልክ እንደነሱ አትሁኑ፡ እያችሁ፡ ካልቻልክ ግን፡ ትታችሁ ሂዱ። በልባችሁ ግን፡ እንዲህ ወደ ማለት መድረስ አለባችሁ፡ "እንግዲህ፡ ይህ... አሁን፡ ምናልባት፡ ወንድሜ፡ እንደ'ኔ ሆነህ፡ ከተረዳኸኝ፡ የእኔ ስሜት ይገባሃል።" እያችሁ? በትክክል መልካም ሆናችሁ፡ መንገዳችሁን ቀጥሉ። ምንም እንኳን ምዕራብ ከምስራቅ እንደሚራራቅ ብንለያይም፡ ይህ ምንም ለውጥ አይኖረውም።

20 በቀደም ማታ ላይ እንዳልኩት፡ አንድ ወንድሜ አለ... ሜልቪን ይባላል፡ የሰው-ልክ ሰው ነው፡ ረጅም፡ ባለ ወርቃማ-ጸጉር። እና፡ ምንም ዓይነት ዝምድና እንደሌላቸው ያህል እኔና እሱ በምንም አንመሳሰልም። አፒታይታችን— እና ምኞታችን ሁሉ ለየቅል ነው፡ ነገር ግን የሱ እናት የእኔም እናት ናት፡ አባቱ አባቴ ነው፡ ወንድሜ ነው። እያችሁ? ምክንያቱ አንድ ቤተሰብ ውስጥ ስለተወለድን ነው።

21 እንግዲህ፡ እንለያያለን። ሜልቪን ክርስቲያን አይደለም፡ ቤዝቦል፡ የፈረስ ግልቢያ፡ እና የመሳሰሉ ነገሮች ይወዳል። ሌላም እ—እንደሚመስለኝ ቸኮሌት ፓይ ይወዳል፡ ስለዚህ በትክክል እንለያያለን። ደግሞ የፈረስ ግልቢያ እና ቤዝቦል እ—አልወድም፡ አሣ ማጥመድ እና አደን እወዳለሁ። እያችሁ? በዚህ ምክንያት ግን ሰላምታ አይከለክለኝም፡ እኔም በበኩሌ በሌላው ምክንያት ሰላምታ አልከለክለውም። እናም ደግሞ፡ ተመልከቱ፡ እሱ ቸኮሌት ፓይ ይወዳል እኔ ግን ቼሪ እወዳለሁ። እናም ደግሞ...

22 እንግዲህ፡ ጥቆማ ማድረጌ አይደለም፡ እያችሁ። አንድ ጊዜ ሰብሰባ ላይ፡ ቸኮሌት ፓይ እወዳለሁህ ብዬ ተናግሬ፡ ቀጣይ ምሽት ላይ አምስት ቸኮሌት... ማለቴ ቼሪ ፓይ መጣልኝ፡ እህቶች ጋግረው አምጥተውልኝ አራት ይሁን አምስት ቼሪ ፓይ ሰጥጠውኛል። አቤት! ቢሮዬ ውስጥ አውደ አመት ነበር የሆነልን! እ—እንደዚያ ይሁን ማለቴ ግን፡ አይደለም። እያችሁ?

23 ስለዚህ ልዩነቱን ብቻ ለማሳየት ያክል ነው፡ እንግዲህ። ምንም ቢሆን ግን፡ ወንድሜ ነው፡ እወደዋለሁ። ክርስቲያን አይደለም ምክንያቱ ለነገሮች ያለው ምልከታ በሌላ ብርሃን ነው፡ እኔ ነገሮችን የማይበት ብርሃን የክርስቶስ ብርሃን ነው፡ ቢሆንም ግን ወንድሜ አይደለም ልለው አልችልም፡ ምክንያቱ ከአንድ ቤተሰብ የተወለድን ወንድማማቾች ነን።

24 አሁን፡ ባለፈው ምሽት፡ በመጨረሻ አንድ ጥቅስ አቅርቤ ነበር። አሁንም አስታውሱ፡ እናንተ ከምታውቋቸው የመጀመሪያዎቹ መልዕክቶች ሌላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣ አንደኛ መልዕክት፡ ኬንታኪ ላይ ከመጡ ሌላ፡ በዚህ ጉባኤ

ላይ ሰዎችን እጅግ የሚያስደነግጡ ምስጢራዊ ነገሮች ይሆናሉ የሚለውን ነበረ። አስታወሳችሁት? አሁን፡ ቴፕ ውስጥ ተቀድቷል። አያችሁ? ትናንት ማታ እንደኛው ተገልጧ። ስለዚህ ያለቀው በአንድ ሰከንድ ውስጥ ነበር፡ በደንብ እንደያዛችሁት ግን እርግጠኛ ነኝ፡ ምክንያቱ መሆን የሚገባውን፡ መንፈስ ቅዱስ ግልጽ አድርጎልናል፡ "ዘለአለማዊ ሲኦል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ብሎ ነገር የለም።"

25 ለአለማዊ ሲኦል የለም። ዘላለማዊ ቢሆንማ... በሲኦል ውስጥ ለዘላለም የምትቃጠሉ ከሆናችሁ፡ ከኖራችሁ፡ እንግዲያውስ በዚያም ዘለአለማዊ ህይወት አላችሁ። ዘለአለማዊ ህይወት ግን አንድ ብቻ ነው፡ እሱም እግዚአብሔር አምላክ ነው! አያችሁ? ስለዚህ፡ ስለ ሲኦል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት "ኤቨርላስቲንግ" እንደሆነ እንጂ፡ **ዘለአለማዊ** እንደሆነ አያስተምርም። ይህ ማለት ለአስር ሺ ዓመታትም ሊሆን ይችላል፡ እኔ አላውቅም፡ ከሆነ ጊዜ በኋላ ግን ይጠፋል።

26 ይህን የመናገር ግዴታ ያለብኝ እኔ ነኝ። መናገር እስካለብኝ ጊዜ ድረስ... ከአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰውሬው ቆይቻለሁ። እና በእነዚህ ውስጥ እኔ ልናገራቸው የሚገቡኝ ነገሮች ብዙ አሉ፡ እና በየምሽቱ እናያቸዋለን።

27 አሁን ግን፡ ከዛሬ ማታ ጀምሮ፡ መንፈሳዊ አስተሳሰባችሁን መልበስ ጀምሩ፡ አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻውን ይግባ። ከዚያ በኋላ ሰምታችሁ ካልተዋጠላችሁ፡ መንገዳችሁን ቀጥሉና እንዲህ በሉ፡ "ምስኪን ወንድም ብራንሃም፡ በእውነት ገና በትክክል—አላወቀውም። እጸልይለታለሁ።" እናንተ ይህን ካደረጋችሁ፡ ከዚያ በኋላ... እውነት ምን እንደሆነ ጌታ ራሱ እንዳውቅ ያደርገኛል፡ እናንተ ግን እዘኑልኝ፡ እንጂ አ—አታውግዙኝ። እንዲሁም፡ በሱ መልኩም ሊሆን ይችላል፡ ኦህ፡ እኔ ግን፡ በዚህ መንገድ ነው ብዬ እያሰብኩት እጅግ ደስ እያለኝ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱን ጫፍ እያገነናኘ ነው። ኧረ፡ እኔም፡ ምናልባት—ተሳስቼ ይሆናል፡ ምናልባት እኔ ገና ያልደረስኩበት ማስሪያ በሆነ ሰፍራ ላይ ይኖር ይሆን፡ ምናልባት እናንተ የደረሳችሁበት ከሆነ፡ ጌታ ለእኔ ደግሞ እንዲያሳየኝ ጸልዩልኝ።

28 እና አሁን፡ ከሁሉም በላይ፡ አንዳችሁ ለሌላው መጸለይን ቀጥሉ ዲያቢሎስ ምንም አይነት መራራነት እንዲያሳይ የትም በር አትክፈቱለት። አያችሁ? በዚህ ሰአት ነፍሶቻችሁን ንፁህ አድርጉ፡ በዚህ አለም ታሪክ የመጨረሻ ሰአት ላይ ደርሰናልና። አያችሁ? ወዳጆች ሆይ፡ ያለ አንዳች ጥርጥር፡ መጨረሻ ላይ ነን።

29 በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ስናልፍ፡ በቅርቡ ምናልባትም በዚህ ምሽት፡ ብዙ ለማወቅ እንሞክራለን። ይብዛም ይነሰም ለዚህ ነገር መዝጊያ የሚሆነን ነገር እያገኘን እና እየሰራን እንገኛለን፡ አሁንም በዚህ ምሽት አንዳንድ እውነተኛ መንፈሳዊ ነገሮችን እንገልጣለን። መንፈሳዊ አስተሳሰባችሁን እንድትለብሱ፡ ማሳሰቤን፡ አሁን አትርሱ። ይሁን እንጂ ቅዱስ ቃላትን ጠብቁ፡ **በቅዱስ** ቃል መሆን ይገባል፡ እንዲሁም **ከቅዱስ** ቃል መሆን አለበት። አያችሁ? እንግዲህ ልብ በሉ... የቃሉ እውቀት፡ እንዲህ እያሉ መናገር ብቻ፡ "እንዴ፡ እኔ'ኮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አለኝ። መጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቻለሁ። ኮሌጅ ጨርሻለሁ።" ያ ምንም አይጠቅምም። ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ሁሉ

ተመሳሳይ ያው ነበሩ፡ ኢየሱስን ግን አላወቁትም የአንድ ሚሊዮን ማይሎች ርቀት ነበራቸው። አያችሁ?

30 ቅዱሳት መጻሕፍት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ፡ “ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ተሰውሯል፡ መማር ለሚወዱ ለህጻናት ተገልጧል።” እንግዲያውስ እኔና እናንተም ሕፃናት እንሁን እና ልባችንን ነጻ አድርገን፡ እንዲህ እንበል፦ “ጌታ ሆይ፡ አንተ—አንተ ንገረን፡ እኛም—እንሰማለን።” ከዚያም መንፈሳዊውን መተግበሪያ ይኑራችሁ። አሁንም ይህን አስታውሱ፡ ከዛሬ ማታ ጀምረው ለሚነገሩ ቃላት ሁሉ፡ መንፈሳዊ መተግበሪያ ይኑራችሁ፡ ምክንያቱም ወደ ታላቅ ሚስጥራዊ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እየመጣን ነው።

31 እንግዲህ፡ ይህ ብቻ ይመስለኛል። አስታውሱ ነገ ማታም፡ በእያንዳንዱ ምሽት ሌላ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንማራለን። እናም ነገ ቀኑን ሙሉ ከዚያም ነገ ምሽት፡ በዚህን ነገር ላይ ለመማር ብዙ ጊዜ እንደሚኖረን እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን፡ ደግሞ፡ ብዙዎቹ ስራ ስለሚኖራቸው የዚህ መልዕክት ዋና ዋና ነጥቦችን ብቻ ለመነካካት እሞክራለሁ፡ እዚህ የተነገሩትን ነጥቦች እነካካለሁ፡ እናንተም አንዳቸውን ይዛችሁ ቀጥሉ፡ ሌላ ጥያቄ እስከማይኖር ድረስ በደንብ አጥኑት። አያችሁ? እናንተም… ግን ወደ ቤታችሁ ሄዳችሁ ማጥናት አለባችሁ፡ እኔም እጸልይላችኋለሁ፡ እናንተም ስለ እኔ ትጸልያላችሁ፡ እግዚአብሔርም እንደ አማኝ ልጆቹ በአንድነት ይባርከናል።

32 አሁን ከመጀመራችን በፊት፡ ተነስታችሁ ብትቆሙ እጅግ ከባድ እንደማይሆንባችሁ አስባለሁ።

ለምን ቆሜ መጸለይ እንደምወድ ታውቃላችሁ? ኢየሱስም፡ “ለጸሎት ስትቆሙ፡ ‘በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፡ ጸልዩ።’ ያኔ እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ፡” ብሎናል። አያችሁ? ያን ጊዜም ጌዴዎን ስራዊቱን ሲመርጣቸው ጊዜ ጉንበስ ብለው በተቀመጡት እና አጎንብሰው ውሃውን በጠጡት ላይ፡ ወይም ቆመው ውኃውን የጠጡትን መረጣቸው። አያችሁ? ስለዚህ የወደቁት ሁሉ፡ ማለት በጣኦታት ፊት—ከተንበረከኩት ወገን የነበሩትን ሁሉ፡ ለመሄድ ብቁዎች እንዳልነበሩ አወቀ። ስለዚህ፡ እነዚያን አይናቸውን ሳይከድኑ የሚጠባበቁት ሁሉ ሄዱ። እኛም የምናደርገው እንዲሁ ነው፡ ቆመን እንጸልያለን። እንግዲህ፡ ተንበርክኮ በመጸለይም፡ አምናለሁ፡ ይሁን እንጂ፡ ቆሞ መጸለይ፡ በተለየ መልኩ፡ ለየት ያለ ትርጉም እንዳለው አስባለሁ።

አሁን አንገታችንን ዝቅ አርገን፡ እያንዳንዳችን ልባችንንም እናንበርክክ፡

33 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ወደ ፍርድ ወንበርህ በትሕትና እንቀርባለን፡ እንድትፈርድልን ለመጠየቅ ግን አይደለም፡ እንዲሁ ቢሆን ሁላችንም እንጠፋ ዘንድ አለንና፡ እኛ ግን “አቤቱ፡ ማረን!” እያልን እየለመንን ቀርበናል፡ ዛሬ ማታ፡ ከመንፈስህ፡ በእኛ ላይ አፍስስ፡ የተገባን ስለሆንን አይደለም፡ ነገር ግን ይህ የማይገባቸው መሆናችንን፡ አውቀን በመረዳታችን ነው፡ በራሳችን ስም አልመጣንም፡ ስማችን ዋጋ የለውምና። ፍርዳችን ከንቱ ነው፡ ወይም—ወይም ተራ ነው፡ ትልቁ ጽድቃችን በይናችህ ፊት እንደ መርገም ጨርቅ ነው። ስለዚህ በትህትና በጌታ በኢየሱስ ስም እንመጣለን፡ የቃል ኪዳኑን ደም፡ በፊታችን አቅርበን፡ በልባችን ላይ ይዘን፡ እንዲህ እንልሃለን፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ በመከራ ጊዜ ምሕረትን ለምንለምንህ ኃጢአተኞች ማረን።” ይህም፡ አንድ ቀን

የመጨረሻው ሰብከት ይሰበካልና፡ እኛም ቀኑ መቼ እንደሚሆን አናውቀውም፡ አየር ላይ የመጨረሻዋ ጩኸት በተሰማች ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ፑልቢት ላይ እንደተዘጋ ይቀመጣል፡ ክንዶች ይተጣጠፋሉ፡ ቧንቧዎች ያንጠባጥባሉ፡ ጸሐይም ትጠልቃለች። አምላክ ሆይ! የዘመናት አለት ሆይ፡ በዚያች ሰዓት፡ አቤቱ ሰውረኝ።

34 እና አሁን በአንተ በኩል እንጂ፡ ምንም ማምለጫ እንደሌለ እናያለን። ህዝቦች ሲሰባበሩ አይተናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲፈጸም አይተናል። እስራኤል ስትነቃ አይተናል። ለቤተ ክርስቲያን የተላለፈውን መልእክት አይተናል። ታላላቅ ነገሮች በሚገለጡበት፡ ሰባት ማሕተሞች በሚከፈቱበት ወቅት፡ ጊዜው ሊያልቅ ተቃርቧል።

35 እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፡ አቤቱ ማረን፡ ምህረትን እንማጸናለን። እኔም እንደ ባርያህ፡ ዛሬ ማታ በመለኮታዊ ህልውና ላሉ ሁሉ ምህረትን እማፀናለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፡ በነፍሱ ውስጥ ኃጢአት ያለበት አንድ ሰው ከእኛ መካከል አይገኝ፡ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ደም ይንጻ፡ ይህም ሁላችንም ከሰማይ ባሻገር በዚያ በተድላው ቦታ እንገናኝ ዘንድ ነው።

36 አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታም ወደ ቅዱሳት መጻህፍት ቀርቤአለሁ፡ አቤቱ፡ እኔ ለዚህ አልበቃም። እግዚአብሔር ሆይ ማናችንም በቂ አይደለንም። አባት ሆይ፡ ምንም እንደማናውቅ እንታመናለን፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጥልን ግን በትሕትና በእርሱ ላይ እንደገፋለን። አንተ በሰጠኸን የአእምሯችን—እውቀት የሆነውን፡ ታሪክ ስንገልጥ፡ መንፈስ ቅዱስ ለልባችን መንፈሳዊ አተገባበርን ይስጠን። አባት ሆይ፡ በልጅህ በኢየሱስ ሰም እንጠብቅሃለንና፡ ሰጠን። ኣሜን። ተቀመጡ።

37 በራእይ መጽሐፍ 2ኛ ምዕራፍ፡ እና ሁለተኛዋ ቤተ ክርስቲያን፡ በሦስተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን። በቀዳሚነት... [እንዲት እህት በልሳን ተናገረች—አርታዒ።] ይቅርታ አርጉልኝ።

38 በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፡ ሰምህ ይቀደሰ። መንግሥትህ ትምጣ፡ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች፡ እንዲሁ በምድር ትሁን። አባት ሆይ፡ ከኛ ጋር እንድትሆን፡ እንድትባርከንም እንለምንሃለን፡ እናም በዚህ በታላቅ ጭንቀት መካከል በሰዎች መካከል ብልሃተኛ አናጢዎች እንድንሆን እርዳን። ግራ መጋባት እና ሁሉም ነገር በሞላበት ዘመን ላይ፡ ጌታ ሆይ፡ በክርስቶስ ሰም፡ የተወደዱ ባርያዎችህ እንድንሆን እርዳን። ኣሜን።

39 እንግዲህ፡ ይህን ታውቁ ዘንድ፡ አሰቀድሜ ይሄን እላለሁ። የቃሉ ትርጉም እንዳልተሰጠ አስተውላችኋልን? እህታችን በመንፈስ ቅዱስ መቀባቷ፡ ጥርጥር የለውም፡ ነገር ግን ቃሉ ከመጣ በኋላ መልእክቱን አስተላለፈች፡ አያችሁ። ከነገሩ ቅደም ተከተል ትንሽ ተዛንፏል። እንግዲህ፡ ማንም ሁኚ፡ ውድ እህታችን፡ ያም መልካም ነው። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይሁን፡ ኡህ፡ እፍነሽ መያዝ በጣም ይከብዳል፡ አውቃለሁ። ልክ እንደ... ወይም ሌላ ነገር ስትናገሩ... አያችሁ፡ ግን መልካም ነበር፡ እንደውም ከመጀመራችን ቀደም ብሎ ሰሜቱን አጣጥማችሁታል፡ አያችሁ። መንፈስ ሲሰራ፡ እንደገና የሚመጣበት ምክንያት

ይህ ነው፡ አያችሁ። የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ተገዥ ናቸው፡ አያችሁ። እናንተን ነው።

40 አሁንም፡ ምናልባት እንደገና... ጉባኤው ካለቀ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሚቀባችሁ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚያም ትርጉሙ ሲመጣ ታያላችሁ፡ ምክንያቱ፡ ሁሉም በቅደም ተከተል መምጣት አለበትና፡ አያችሁ፡ አሁን ግን፡ እንደምታዩት፡ ወደ ቃሉ እየገባን ነው። ስለዚህ፡ አሁን፡ ያ በእውነት የእግዚአብሔር እንደሆነ፡ በእርግጥም እንደነበር አምናለሁ፡ በሙሉ ልቤም ይሰማኛል፡ ምክንያቱ ቀጣይ-ነጥቡ ተሰምቶኛል፡ አያችሁ። ለመንፈስ ቅዱስ ግን... ጊዜው አልነበረም። በእህታችን በኩል ለቤተ ክርስቲያን መልእክት አለው፡ መልእክቱን እየሰራው ያለው ግን **እዚህ** ነው። አያችሁ፡ እራሱን ግራ አያጋባም፡ ነገርን ሁሉ በቅደም ተከተል ያደርጋልና። ሁሉም ሰው እንደሚረዳው እርግጠኛ ነኝ፡ አያችሁ፡ ነገርየው ልክ ነው።

41 አሁን በ—በራእይ መጽሐፍ 2ኛው ምዕራፍ። እና... ዛሬ ማታ የምንጀምረው—ከጴርጋሞስ ዘመን ይሆናል፡ 12ኛ ቁጥር። ምክንያቱ፡ ትላንትና ማታ በ11ኛው ቁጥር ላይ ቆመናልና፡

> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ** ያለው **ይስማ፡ ድል የነሣው** በ**ሁለተኛው ሞት አይጎዳም።**

42 እንግዲህ፡ በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ኒቆላውያን መጀመሩን አውቀናል። እግዚአብሔር... ኢየሱስ ራሱን ሁሉን እንደሚችል አምላክ ገልጧል፡ እርሱ ራሱ አምላክ ነበረ እንጂ፡ ሌላ አካል፡ ሌላ ቁርጥራጭ፡ ሌላ ነገር አይደለም።

43 በትናንትናው ማታ የቤተ ክርስቲያን ዘመንም፡ እንዲሁ፡ በሩ ላይ ቆሞ እነዚህን ነገሮች ለቤተ ክርስቲያን ጽፎ፡ ስለ ድህነታቸው እንደነገራቸው ተረድተናል። ነገር ግን ስለ እነዚህ ነገሮች... ኒቆላውያን፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች፡ እጠላለሁ አለ።

44 ትናንት ማታ ስለ ሰማዕት... የሰማዕቱን አክሊል ስለ መልበስ ነበረ። እስከ ሞት ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ አትፍሩ—አላቸው። ከዚያ በኋላ በማለቂያው ላይ እንዲህ አላቸው፡ "ድል የነሣው! ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።"

45 አሁን፡ አንደኛው አለ ከተባለ፡ እሱን እናውቀዋለን፡ እንግዲያውስ ሌላኛው ሞት በሌላ ሰፍራ ይኖራል፡ ምክንያቱ አንደኛው ሞት በዚህ በሥጋ እንሞታለን፡ ሁለተኛው ሞት በመንፈስ እንሞታዋለን፡ በነፍስ። "ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ ፈጽማ ትሞታለች፡" ነውና። **መሞት** ማለት፡ "ከሌላው ነገር ሙሉ በሙሉ መለየት ነው፡" አያችሁ፡ እ—እ... **ሞት** ማለት፡ "መጣል ነው፡ መ—መ—መወገድ፡ መሰወር።" የምንወዳቸው ሰዎች ሲሞቱ፡ እስከምናውቀው ድረስ ከሕልውና ውጭ ናቸው። ያም ሞት ብለን እንጠራዋለን።

46 ክርስቲያን ግን አይሞትም። ክርስቲያን ይሞታል የሚል አንድም ቃል የለም፡ ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት ስላለው ነው። ኃጢአተኛ ሲሞት ግን፡ ያበቃለታል፡ ነፍሱም በመጨረሻ ትሞታለች። አንድ ክርስቲያን ሲሞት ግን፡ እንደገና ተመልሶ እንዲመጣ ከኢየሱስ ጋር እየጠበቀ ይቆያል። እነሆ፡ በዚህ በዛሬው ምሽት ራእይ መጨረሻ ላይ፡ ወደዚያ ወደተመለስንበት ለመግባት

ጊዜ አገኛለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡ እናንተም የሁለተኛው ሞት በተመሳሳይ መንገድ እንዴት እንደሚገባ፡ ታያላችሁ። ዛሬ ምሽት ላይ ያለንበት ይህ ምዕራፍ ራሱ ተመሳሳይ ነገር፡ እና በጣም የሚያምር ማስታወሻ ያመጣልናል።

47 እ—አሁን፡ የዛሬ ማታ፡ ደብዳቤውን ቶሎ ብለን እናነበዋለን፡ ምክንያቱ በመጀመሪያ ታሪካዊ ዳራውን አይተን፡ ብዙም ላቆያችሁ እንደማይገባኝ—አንዳንድ መረጃዎች ደርሰውኛል። አሁን፡ ጉባኤው ካ... ካለቀ በኋላ፡ ምናልባት በፍጥነት ያነበብኩት እንደሆነ፡ ማስታወሻውን ማግኘት ከፈለጋችሁ፡ ወንድማችን ሜርሲየርን አግኙት፡ ሁሉንም ለእሱ ስለምሰጠው እሱ ሁሉንም ይዟል፡ በተጨማሪም መጽሐፉን እያዘጋጀ ስላለ፡ የ—የምትፈልጉት ነገር ሁሉ... እሱ ሁሉንም ይሰጣችኋል። ምንም ችግር የለውም እሺ፡ ወንድም ሜርሲየር።

48 12ኛው ቁጥር፦

> በ**ጴርጋሞስ ወዳለው** ወደ **ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ** ያለው **እንዲህ ይላል፡**
>
> **የሰይጣን ዙፋን ባለበት... የምትኖርበትን፡ አውቃለሁ፡ ስሜንም... ትጠብቃለህ፡ ሰይጣንም በሚኖርበት፡ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ፡ በነበረበት ዘመን እንኳ፡ እምነቴን አልካድህም።**
>
> **ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ፡ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በአንተ ዘንድ አሉና፡ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን እንዲጥል ባላቅን ያስተማረ፡ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ስላሉ፡ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ።**
>
> **እንዲሁም ደግሞ ያን ትምህርት የሚጠብቁ** አሉ... **የኒቆላውያን ትምህርት፡**... (በዚያ በኤፌሶን ላይ ስራ ይባል የነበረው፡ አሁን "ትምህርት" ሆነ)... (ባለፈው ምሽት ስነግራችሁ፡ ያንን ነገር እንዴት ፍሬ እንዳፈራ የነገርኳችሁ ነገር ታስታውሱታላችሁ? በኤፌሶን ላይ **ስራ** የነበረው፡ አሁን "ትምህርት" ሆኗል)... **እ—እኔ የምጠላቸው** ነገሮች፡ **የኒቆላውያን ትምህርት።** (እህህ!)
>
> **ንስሐ ግባ፡ አለዚያ ቶሎ ወደ አንተ እመጣብሃለሁ፡ ከእነርሱም ጋር እዋጋቸዋለሁ...** (እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያንን አይደለም)... **እነርሱን በአፌ ሰይፍ።**
>
> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ፡ ድል የነሣው ከተደበቀ መና ይበላ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡ ነጭ ድንጋይም** (ለእርሱ) **እሰጠዋለሁ፡ በድንጋዩም ውስጥ** ከተቀበለው **በቀር፡ ማንም የማያውቀው አዲስ ስም ተጽፎአል።**

ጌታ በዚህ ላይ በረከቱን ይጨምር፡ እኛንም በዚህ በጥረታችን ላይ ይርዳን።

49 አሁን የዚህ ቤተ ክርስቲያን ዳራው ይህ ነው። ጴርጋሞስ ይባላል፡ ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። እና ይ—ይህች ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት ዘመን ከ 312፡ **ዓ.ም.** ከ 312 እስከ 606 ነበር።

50 ዘመኑ፡ የውሸት ትምህርት፡ የሰይጣን ውሸት፡ የጽጽሰና አገዛዝ ምስረታ፡ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት የተጋቡበት ዘመን ነው።

51 ሽልማቱም፡ የተደበቀ መና፡ ነጭ ድንጋይም ነበር።

52 የዚህች ቤተ ክርስቲያን መልአክ፡ ኮከቡ፡ መንፈስ ቅዱስ በመራኝ ነገር ሁሉ፡ ቅዱስ ማርቲንን ወሰጃለሁ። ይህም—በተሰጠኝ መገለጥ አደረግኩት፡ በዚያ ዘመን ስለነበሩ ቅዱሳን ሁሉ አንብቤአለሁና። ቅዱስ ማርቲንን የመረጥኩት የእግዚአብሔር ሰው ስለነበረ ነው፡ በእኔ እምነት ከቅዱስ ፓትሪክ ይልቅ አሥር እጥፍ የበለጠ ሐዋርያ ነበር።

53 ቅዱስ ፓትሪክ፡ የቅዱስ ማርቲን የእህት ልጅ ነበር፡ የቅዱስ ማርቲን እህት የቅዱስ ፓትሪክ እናት ነበረች። ይህ ማለት ቅዱስ ማርቲን… የቅዱስ ፓትሪክ አጎት ነበረ፡ ማለት ነው።

54 በህይወት የነበረበት ዘመን፡ ከ315 እስከ 399 **ዓ.ም.** ነበረ። በዚያ ዘመን ከነበሩ ቅዱሳን ይልቅ እርሱን የመረጥኩበት ምክንያት ይህ ነው፡ ምክንያቱ የግሉ አቋም ነው። እንግዲህ እኔ ይህን አላምን፡ በእግዚአብሔር ምሪት ስር ሆኜ…

55 ሌላው፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ውስጥ አላካተተችውም፡ እውቅና አልሰጡትም፡ እሱን የመረጥኩት ሌላ ምክንያት ይህ ነው። ኧህ-ህህ፡ ኧህ-ህህ። እንዲሁም በእነዚህ በምናያቸው፡ መንፈሳዊ አገልግሎቶች የነበራቸውን ሁሉ፡ የጥንቷ ቤተ ክርስትያን ታወግዛቸው ነበር። በእነዚህም ነገሮች መንፈሳውያን በመሆናቸው፡ የኒቆላውያን—ቤተ ክርስትያን አትቀበላቸውም ነበር። እና እዚህ እንደሳልኩት ሰዕል፡ ከመጀመሪያ ጀምሮ የኒቆላውያኖች ትምህርት ብዙዎች ስለነበሩ—እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ግን፡ ጥቂቶች ስለነበሩ ቤተ ክርስትያን ጭንቅ ላይ ነበረች፡ ከድሮም እንዲሁ ነው።

56 ከመጀመሪያውም እንዳልኩት፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ "አንተ ታናሽ መንጋ፡ አትፍራ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና።" መንግሥቱ መንፈሳዊ መንግሥት ናት የምልበት ምክንያትም ይህ ነው። እንግዲህ እኛ… መንፈሳዊ መንግስት አለን፡ በዚያም እጅግ ሐሴት እናደርጋለን፡ በዚያ በመንግስቱ ውስጥ ንጉስ አለ። እርሱ የቅዱሳን (**ለተቀደሱት**)፡ ንጉሣቸው ነው፡ የሚመራቸውና ንጉሣቸው መሆኑን አስታውሱ።

57 የቅዱስ ማርቲን ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ ከማንም ታላቅ ተአምር-የተሞላ ሕይወት አንዱ… ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ፡ ከነበሩ ዋና መንፈሳውያን ሰዎች የላቀ መንፈሳዊ ሰው ነበር። እሱም…

58 ከመጀመሪያዎቹ ተአምራቶቹ አንዱ… ከጅምሩ፡ ወታደር እንደነበረ፡ አምናለሁ። አንድ ቀን በመንገድ እየመጣ ሳለ አንድ ሰው አገኘ… ሰ—ሰውዬውም በብርድ እየተንቀጠቀጠ፡ መሬት ላይ ተኝቶ ነበር፡ በዚያም የነበሩ ሰዎች ሁሉ ሊረዱት… ማለት፡ ሊያግዙት አልወደዱም፡ መርዳት ግን ይችሉ ነበር፡ **በደጉ ሳምራዊ** እንደነበረ—ልክ እንደ ሌዋዊው እና እንደ ካህኑ

ዝም ብለው አለፉት። ቅዱስ ማርቲን ሲያልፍ ግን፡ እንደ የክርስቲያን እንደ አማኝ ግዴታውን ተገነዘበ፡ የለበሳት አንዲት ኮት፡ እንዲሁም በትከሻው ላይ መጎናጸፊያ ነበረው፡ በሰይፉ ለሁለት ከፍሎ ግማሹን ለለማኙ ሰጠው፡ ግማሹን ለራሱ ወሰደ። በዚያችም ሌሊትም፡ አገልግሎቱን ጀመረ፡ ምክንያቱ፡ ለሁለት የከፈለውን መጎናጸፊያ ለብሶ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ ተገልጦለት ነበርና፡ ይህም "ለእነዚህ ያደረጋችሁላቸው፡ ለእኔ አደረጋችሁት፡" ተብሎ የተጻፈውን ቃል ስለፈጸመ ነው።

59 ስለዚህ ይህ ለትምህርት ይሁናችሁ። ለማንም የምታደርጉት ነገር፡ ለክርስቶስ እያደረጋችሁት ነው። እንዳትረሱት። እስኪ አንድ ላይ... አብረን እንበለው [ወንድም ብራንሃም እና ጉባኤው በአንድነት ተናገሩ—አርታዒ።]፡ "ለሌሎች የምታደርጉት ሁሉ፡ ለክርስቶስ አደረጋችሁት።" ስለዚህ ዋናው ነገር እሱ ስለእናንተ የሚያስበው ሳይሆን፡ እናንተ ስለሱ የምታስቡት ነገር ነው፡ አያችሁ፡ በረከቱን የሚያመጣው ያ ነው።

60 የመጀመሪያ ተአምራቱ እና የአገልግሎቱ መጀመሪያ ያ ነው። ስለሱ በጣም ብዙ ነገር አለ፡ ጊዜ ግን አ—አይኖረኝም። ምክንያቱ ነገ ማታ እና ዘወትር ማታ እንድትመለሱ ስለምፈልጋችሁ፡ ብዙ ላቆያችሁ አልፈልግም።

61 እሺ፡ ዛሬ ማታ ልነግራችሁ የመደብኩት ቀጣዩ ተአምር አለ።

62 አረማዊነትን በፍፁም እያፈረሰ፡ የሮምን ቤተ ክርስቲያን አጥብቆ ይቃወም ነበር። ከመጀመሪያዎቹ የሮም ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ጋር ፈጽሞ አይስማማም፡ እጅግ... ዓለማዊነት እና ሌላ ብዙ ነገሮች ውስጥ ተዘፍቀው ነበርና፡ በዚህም ተቃወማቸው። በርግጥም ይቃወማቸው ነበር። በእንደዚያ ዓይነት ዘመን በሕይወት መኖር መቻሉ በራሱ ተአምር ነው። አሁን...

63 አንድ ቀን ግን የጣዖት አምልኮን እያፈረሰ፡ የአረማውያንን መሠዊያ እያፈረሰ ነው፡ በአረማዊው መሠዊያ አጠገብ አንድ የአምልኮ ዛፍ ቆሞ ነበር። ይህንንም ዛፍ እየቆረጠ ነበር፡ በዚያም የቆሙ ብዙዎችም ተቆጡ። እንዲህም አላቸው፡ "የእግዚአብሔር ሰው ከሆንኩ... ዛፉ በሚወድቅበት በኩል እሰሩኝ እና ዛፉ በላዬ ላይ ይውደቅ። የእግዚአብሔር ሰው ከሆንኩ... የእግዚአብሔር ሰው ካልሆንኩ፡ ዛፉ ይገድለኛል። የእግዚአብሔር ሰው ከሆንኩ ግን፡ አምላኬ ያንን ዛፍ የሚወድቅበት አቅጣጫ ሊያዞረው ይችላል።" ከባድ ፈተና ነው! ስለዚህ ዛፉን መቁረጥ ጀመሩ፡ ዛፉ መውደቅ በጀመረ ጊዜ፡ አቅጣጫውን ቀይሮ ከተመልካቾች ብዙዎችን ገደለ። እግዚአብሔር ወደ ኮረብታው በኩል አዞረው። ተአምር ነው! አቤት፡ በሰብሰባዎቹ ውስጥ ሁል ጊዜ ተዓምራቶች ነበሩ።

64 ሌላው ላወራው ያሰብኩት ተአምር፡ መንገድ ዳር ወድቆ የሞተ ሕፃን እስከሬን ነው። እና ለዚህ ሕፃን ለተወሰነ ጊዜ ከጸለየ በኋላ፡ እንደገና ወደ ሕይወት ተነሳ።

65 ሌላው በጣም የሚገርመኝ፡ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ነው። ይህ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ-የተሞሉ ሰዎችን ሊገድላቸው ዝግጅት አደረገ። እና በእርግጥ ይህ ሰው—በዚያን ጊዜ የሮም የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ቢሾፕ ለነበረው ሰው፡ የቀኝ እጁ የነበረ ነው፡ በርግጥም ጳጳስ ከመባሉ በፊትም ጳጳስ ሆኖ ነበር። ስሙም ዳ-ማ-ሱ-ር ይባላል፡ ሊገድላቸው የያዛቸው

ክርስትያኖችን በሙሉ ይገድላቸው ነበር። እና—እና የዚህ ንጉሠ ነገሥት ሚስት፡ አረማዊት ስትሆን፡ ልቧ ጨለማ ወርሶት ነበር።

66 ይህም ቅዱስ ሰው ቅዱስ ማሪቲን ሊማጸን በመጣ ጊዜ፡ እነዚህ ክርስቲያኖች እንዳይገደሉ ይማልድላቸው ዘንድ ወደ አጠገቡ እንዲቀርብ ሚስቲቱ አገዘችው። እርግጥ ነው፡ በስተመጨረሻ ወደ እሱ ሲደርስ፡ ምንም ማድረግ አልቻለም፡ ምክንያቱም ጳጳሱ ቀኝ-እጅ ስለነበር፡ እነዚያን በመንፈስ ቅዱስ-የተሞሉ ክርስቲያኖችን ገደላቸው።

67 ቅዱስ ማርቲን ግን ከእርሱ ጋር መነጋገር ፈለገ፡ጠባቂዎች ግን በሩ ላይ አስቆሙት። እንግዲህ፡ ቅዱስ ማርቲንም እግዚአብሔር እንዲገባ እስኪያሳየው ድረስ በዚያ በግንባሩ ተደፍቶ መጸለይ ጀመረ። በተነሣ ጊዜም፡ ወደ ተቆለፉ ደጆች መሄድ ጀመረ በሮቹም አውቀው በራሳቸው ተከፈቱ፡ እየተራመደም ገባ።

68 እንግዲህ፡ ይህ ታሪክ ነው፡ ማንም ሰው ተነሥቶ የጻፈለት አይደለም፡ እንደ ትንሽ... እንዲያ ቢህን ግን፡ የአንድ ቤተ ክርስትያን ነገር ቢሆን ግን፡ ወሬ ይሆን ነበር፡ ወይም፡ እኔ እንደምለው፡ ቢያንስ፡ በተለይም የጳጳሱ ቤተ ክርስቲያን፡ እነዚህን ነገሮች አይጠቅሱም። ይሁን እንጂ፡ ታሪክ ግን፡ እውነትን ይጠቅሳል። አያችሁ?

69 እና ይህ ቅዱስ ማርቲን የተባለ ሰው፡ ጠባቂዎችን ሁሉ፡ እና ሌሎች ነገሮች በሙሉ አልፎ፡ ወደ ንጉሱ፡ በፊት ለፊቱ ቀጥ ብሎ ገባ። ንጉሡ ግን የእግዚአብሔርን ባርያ ማክበር አልፈለገም። ታውቃላችሁ፡ ያ—ያ ነገር—ያ አግባብ አይደለም። ምንም ክብር ስላልነበረው ጭንቅላቱን አዞረበት። እግዚአብሔር ያደረገውን ታውቃላችሁ? ሊያናግረው ሞከረና ዝም ብሎ ጭንቅላቱ አዙሮ ዝም አለው፡ እግዚአብሔርም ይህ አሕዛብ ለባሪያው ክብር እንዲሰጥ ፈለገ። ከዚያ የተቀመጠበትን እሳት አደረገበትና፡ አቃጥሎ ከመቀመጫው፡ ብድግ አደረገው፡ እግሮቹ አስቆመው።

70 አሁን እንግዲህ—ያ **የኒቂያው ጉባኤ፡** የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነው። የእግዚአብሔርን አገልጋይ ማክበር ስለነበረበት፡ እንዲነሳ አደረገው። ተቀምጦበት የነበረውን ወንበር ሳይቀር አቃጠለው፡ እሳቱ በሰውነቱ በኩል አለፈ እና የወንበሩ መቃል እሳት አነደደበት፡ ስለዚህ ዘሎ መነሣት ግድ ሆነበት። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራበት መንገድ አለው። ኧህ-ህህም። "እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል።" ያንኑ እግዚአብሔር ራሱ ዛሬ ማታ በመካከላችን እንዳለ፡ አሁን አስታውሱ። ያው አምላክ ነው። በጣም ጥሩ።

71 ከዚያም ሌላ የምወደው ነገር፡ ከዚያ እጨርሳለሁ። ሌላም ይኖራል፡ ይሁን እንጂ.... ከሁሉ አብልጬ የምወደው ይሄኛው ነው፡ አንድ ቀን ሰዎቹ እስኪመጡ ድረስ፡ በጥናት ክፍሉ እየጸለየ ነበረ።

72 ይህ ሰው—ታላቅ ሰው ነበረ፡ የመንፈስ ቅዱስ-ሙላት የነበራትን ቤተክርስትያኑን ይመራ ነበር፡ እንደው ሁላችንም... እነሆ፡ እርሱ... ጉባኤው በሙሉ፡ በመንፈስ የተሞሉ ናቸው። እና በአገሪቱ የነበሩ ክርስትያኖች በሙሉ፡ ድንቆች እና ተአምራቶች የሚያደርጉ ነበሩ።

73 ምክንያቱ፡ እግዚአብሔር ለመልእክተኛው ይናገራል፡ መልእክተኛው ደግሞ ለምዕመናን ይናገራቸዋል። እና እንደምታዩት፡ የነገሩ አካሄድ እንዲሁ ነው፡

ምዕመናን እና እሱ በእግዚአብሔር ምሳሌ—ያቆያቸዋል፡ ይህ ማለት፡ መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ በሰዎች ዘንድ መመላለሱ ነው።

74 ብዙ ጊዜ በስማዕትነት ሲሰዉ አገልጋዩን ከመካከላቸው አቁመው፡ (**በእንዲህ** ዓይነት) ሁሉንም በአንድ ጊዜ ይገድሏቸው ነበር። በእነዚያ ሰዎች ያደረጉት ግፍ! በእሳት ያቃጥሏቸዋል። ወንዶችን ወሰደው... ግንድ ላይ ይቸነክሯቸዋል፡ ከዚያም የዱር ውሾችን ይለቁባቸው ነበር፡ ወይም... ግለሰቡ ገና ከመሞቱ በፊት፡ አንጀታቸውን እየጎተቱ ከጀርባቸው በኩል እንዲበሏቸው ያደርጋሉ። ሴቶችን ወሰደው የቀኝ ጡታቸውን ይቆርጣሉ፡ የልብ ምታቸው አቁሞ እስኪንቀጠቀጡ፡ እና እስኪሞቱ ድረስ፡ በዚህ መልክ፡ ቆመው እንዲቆዩ ያደርጓቸዋል። ከደረሱ እርጉዝ እናቶች ልጆቻቸውን በማውጣት ልጆቻቸው ለአሳማዎች እና ለሌሎች ነገሮች ይሰጧቸዋል፡ እናቶቻቸውም ይህን ሲሆን እንዲያዩ አስቁመው ያሳዩአቸው ነበር። ሌላ ብዙ ዓይነት ነገርም ነበር!

75 መቼም፡ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች ይህን ያደርጋሉ ብላችሁ አታስቡም። ነገር ግን ሰሙኝ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ መስሏቸው፡ እናንተን የሚገድሉበት ጊዜ ይመጣል።" አስታውሱ፡ በአንዱ መንፈስ ይህን ነገር የተናገረው፡ ራሱ ኢየሱስ፡ በዘመን ፍጻሜም እንዲሁ እንደሚሆን ትንቢት ተናግሯል። መሆኑ አይቀርም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በትክክል ካልተመሳሰለ፡ ከታሪክ እና ከመጽሀፍ ቅዱስ ቃል ጋር በትክክል ካልገጠመ ተመልከቱት። እግዚአብሔር ይሆናል ብሎ እንደተናገረው፡ እዚህ ጋር ደግሞ ታሪክ ተፈጽሟል ይለናል፡ እዚህ ጋር እግዚአብሔር ይሆናል ያለው፡ እነሆ እዚህ ጋር ሆነ። አያችሁ፡ በትክክል። እንግዲህ ወደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ስንደርስ ምን እናደርጋለን (አሁን ያለንበትን፡ ተመልከቱ) ወዮዎቹን እና ሌሎች ነገሮችን ይሆናል አልተባለለትምን?

76 ስለዚህ፡ አሁን፡ ይሄኛው፡ ጉባኤውን እየጠበቀ በጸሎት ጊዜ ነበር። እናም አንድ ለማኝ ወደ በሩ መጥቶ በሩን አንኳኳ፡ በሩንም ከፈተለት (በስራ ተጠምዷል)፡ ይህም ልብስ—እንደሚፈልግ ነገረው። ራቁቱን ነበር ምንም አልነበረውም፡ ይበርድ ነበርና፡ እንዲህ አለው... ወደ ዲያቆናት አለቃ ሄዶ እንዲጠይቅ ላከው። የዲያቆኑም አለቃ ተናደደና አባረረው። ባባረረው ጊዜ ግን፡ እንደገና ዞሮ መጣና፡ ዲያቆኑ—ሂድ ብሎ አባሮኛል—በማለት ቅዱስ ማርቲንን ነገረው።

77 እና፡ ያን ጊዜ፡ ይህ የዲያቆናት አለቃ ተመልሶ መጣና እንዲህ በማለት በፍጥነት ተናግረው፡ "ጉባኤው አንተን እየጠበቀ ነው! እየጠበቁህ ነው!" አለው፡ እርሱ ግን ጸሎት ላይ ነበረ። እግዚአብሔር ውጣ የሚለው ምሪት እስኪያገኝ ድረስ ቢጸልይ ይሻለዋል።

78 እናም ይህ ለማኝ ወደ በሩ ተመለሰ። ቅዱስ ማርቲንም የራሱን ውድ ልብስ አውልቆ ለለማኙ ሰጠው፡ እና ሌላ ልብስ እንዲያመጣለት የ—የ—የዲያቆናት አለቃውን ነገረው። ከዚያም፡ እንዲሁ ልብስ አመጣለትና፡ ቅዱስ ማርቲንን አለበሰው። ከውድ ልብሱም ይልቅ ርካሹን ልብስ በሰዎች ፊት ለበሰ።

79 ይህ ምን ለማሳየት ነው፡ ያለህን መልካሙን ነገር ሰጥ፡ ህይወትህን ሰጥ፡ ጊዜህን ሰጥ፡ ሁሉንም ነገርህ ለክርስቶስ ሰጥ። በክርስቶስም የነበረው ያ መንፈስ፡ በእናንተ ደግሞ ይኖራል፡ እና—እና በአካባቢያችሁ እና አብራችሁ

በምትውሏቸው ሰዎች ዘንድ የሚኖራችሁ ተጽዕኖ፡ ክርስቶስ ያደረጋቸውን ነገሮች እስክታደርጉ ድረስ እጅግ ክርስቶስን ትመስላላችሁ።

80 በመጨረሻም በጨለማ ስር የወዳደቁት ሰዎች ሁሉ ይፈወሳሉ። ይህ—እውነት ነው፡ በዙርያቸው እጅግ ብዙ የፍቅር ኃይል ይሆንላቸዋል። እና እንዲህ ይባላል "ያንን ርካሽ ልብስ ለብሶ ከወጣ በኋላ፡ ቅዱስ ማርቲን እየሰበከ ሳለ፡ ዙርያው በሙሉ የሚያብረቀርቅ ብርሃን ተሞልቶ እንደነበረ ጉባኤው ሁሉም እንዳዩት ይናገራሉ።" ኡህ-ህህ። እያችሁ? ምክንያቱ፡ ትክክለኛ ነገር ስላደረገ ነው።

81 ሁሌም ትክክለኛ ነገር አድርግ፡ ይህም ለእግዚአብሔር የሚሆን ግዴታህ ነው፡ ቅን ነገር አስብ፡ ስለራስህ ግዴታህ ነው፡ ያኔ ትክክለኛ ትሆናለህ። ትክክለኛ ነው፡ ይህ ማድረግ አለብህ።

82 አሁን፡ ማብራሪያ ቀኖና ለመውሰድ በመሞከር አሁን ይህንን መጀመር እንፈልጋለን፡ ዛሬ ማታ፡ ምክንያቱ ይህ ነገር ጠንካራ ነው።

> አሁንም፡ **ወደ ጴርጋሞስ ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ ጻፍ፡** በሁለት የተሳለ-... **በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም... ሰይፍ** ያለው **እንዲህ ይላል፡**

83 አሁንም እንድታስተውሉት የምፈልጋችሁ ነገር ዛሬ ማታም አምላክነቱ እያስተዋወቀ መሆኑ ነው። እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን በከፊል የክብሩ ውበት ነጸብራቅ ናት፡ አሥራ ሁለት ከዋክብት የያዘው... ማለት "በእጁም ሰባት ከዋክብት የያዘው፡ በሁለት-ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው፡" እያችሁ፡ ሌላ ነገርም፡ "የናስ እግሮች ያሉት፡ የእሳት ነበልባል የሆኑ... አይኖች ያሉት።" ይህ ማለት እንደገና በአምላክነቱ እራሱን ማስተዋወቁ ነው።

84 ምናልባት እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ "በዚህ ውስጥ አምላክነት የት አለ፡ 'በሁለት- ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ከአፉ የወጣ ነውን'? "

85 እንግዲህ፡ **ሰይፍ** ማለት "ቃል" ነው። ዕብራውያን 4፡ ስለ አምላክነቱ በመጀመሪያ በወሰድን ጊዜ አይተነዋል። በዕብራውያን 4:12፡ የሚገኘው፡ ይህ ሰይፍ፡ "የእግዚአብሔር ቃል ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው።" ልክ ነው? ያ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ነው... ? እንግዲህ፡ አሁን ተመልከቱ፡ እነዚህን-... ትርጓሜዎች ታገኛላችሁ። አሁን ይህ ከዮሃንስ 1 ጋር፡ አስተያዩት፡ "በመጀመሪያ" (ያኔ ድሮ) "ሰማይን እና ምድርን የፈጠረ ቃል ነበረ።" ልክ ነው? "ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። እግዚአብሔርም ሥጋ ሆነ በእኛ ዘንድ አደረ።" ልክ ነው? "ቃል ሥጋ ሆነ በእኛ ዘንድም አደረ።"

86 እነሆ በመጀመሪያ የነበረው፡ እዚህ ጋር ቆሟል፡ "ለጴርጋ-... ለጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ—በል። እንዲህ በለው፡ 'የእግዚአብሔር ቃል እኔ ነኝ።'" እነሆ፡ በራዕይ ላይ ስንመለከተው፡ ልብሱን በደም ተነክሮ፡ በራሱ ላይ እክሊል ጭኖ፡ በጭኑ ላይ "የእግዚአብሔር ቃል፡" የሚል ጽሑፍ ተጽፎበት፡ ነጭ ፈረስ እየጋለበ ሲመጣ እናየዋለን። አቤት፡ ሰወደው። እርሱ ቃል፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ ይህን አምላክ፡ እርሱ ቃል እንደሆነ፡ እራሱን ሲያስተዋውቅ አይተነዋል።

87 ስለዚህ፡ እርሱ ሕያው ቃል ከሆነ፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈው የእሱ ቁራሽ ነው፡ እናንተም ይህን፡ ወደ እርሱ (ማለት ወደ ቃል) ስትቀበሉት፡ ይህ ቃል በእምነት ወደ እናንተ ይመጣል፡ ሕያውም ያደርገዋል፡ ምክንያቱ ይህ… ኦህ! ይህን ተረዱት! ወደ እናንተ የሚመጣው ቃል፡ መንፈስ ቅዱስ በዚያ ውስጥ ካለ፡ ልክ እንደገባ ህያው ነው፡ ያኔ እያንዳንዱ ተስፋ ቃል እውን ይሆናል። ምንም ቢመጣ… "ስለዚህ፡ ይህን ተራራ 'ተንቀሳቅስ፡' ብትሉት፡ በልባችሁም ባትጠራጠሩ።" ምክንያቱ (ምንድነው? ) እየተናገርክ ያለኸው አንተ አምላክ ነህ። ታምናላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ይላልና። ባትጠራጠሩት የምትናገሩት ሁሉ ይፈጸማል፡ ዓለምን እና መላዋን—ከውስጣችሁ ማስወጣት ከቻላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ያደርጋችኋል፡ ምንም ዓለም፡ ኩነኔም፡ ጥርጣሬ የሌለበት ትሆናላችሁ። እንዲህ ከሆነ፡ ታዲያ ምንድነው? እናንተ አይደላችሁም፡ በእናንተ ውስጥ የሚኖረው እግዚአብሔር ነው። ከዚያም ቃሉ ትጠቅሳላችሁ፡ ቃልኪዳን ነውና፡ "አባት ሆይ፡ ቃልኪዳንህ ነው፡" ትሉታላችሁ። "ሰይጣንም፡… " የሆነ ነገር መንቀሳቀስ አለበት። አያችሁ? አያችሁ?

88 አሁን፡ ያ ጉዳይ ምን መሆን እንዳለበት እግዚአብሔር እስካልገለጠላችሁ ድረስ ያንን ማድረግ አትችሉም። አያችሁ? ከዚያ በኋላ ግን፡ ጉዳዩ ምን እንደሚሆን ስታውቁት፡ እንደ ኢየሱስ ማለት ትችላላችሁ። እርሱ ቃል **ነበርና**። ልክ ነው? ይህ ሰው ግን፡ ማለት ኢየሱስ፡ ማደሪያው ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ "አብ አስቀድሞ ካላሳየኝ በቀር ከራሴ ምንም አላደርግም።"

89 እንግዲያውስ ለእናንተ ለራሳችሁ እስኪገለጥ ድረስ ያንን ቃል አይደለም። ገብቷችኋል? ሰዎች "የተአምራት ዘመን አልፏል" ማለታቸው አይደንቅም፡ ቃሉ ለእነርሱ ስላልተገለጠላቸው ነው። በመንፈስ ቅዱስ ማመን አለመቻላቸው ምንም አያስደንቅም፡ ቃሉ አልተገለጠላቸውም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የጥምቀትን መገለጥ ማየት አለመቻላቸው ምንም አያስደንቅም፡ ቃሉ ገና አልተገለጠላቸውም፡ ነገር ግን የሚያመጡት አንድም መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የላቸውም፡ ማንም በሌላ መንገድ የተጠመቀበት ስፍራ የለምና።

90 ስለ መንፈስ ቅዱስ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፡ ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ሊለው የሚችል የለም፡" ሰዎችም መንፈስ ቅዱስ ትክክል ነው ብለው እንደማያምኑ ይናገራሉ። አያችሁ? አያችሁ፡ ለእነሱ አልተሰጠም። ኢየሱስም አለ፡ "አባቴ አስቀድሞ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። እንዲሁም ለአብ የነበረው ሁሉ" (ያለፈ ጊዜ) "ለእኔ የተሰጠ ወደ እኔ ይመጣል።" አቤት፡ አያምርም ወይ! "አብ የሰጠኝ ሁሉ፡ ወደ እኔ ይመጣል። ከጥፋት ልጅ በቀር አንዳቸውም አይጠፉም፡ እኔም… (እርሱም ለዚህ ዓላማ ተወለደ)፡ በመጨረሻው ቀንም አስነሣቸዋለሁ።"

91 ኦህ፡ ማይ! በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማችን የተቀመጠበት፡ ገና ከዓለም ምስረታ ጀምሮ ነው። አያምርም ወይ! እንዴትስ እንጠራጠረዋለን?

92 አምላክ ሆይ፡ ጥርጣሬን ከመካከላችን አርቅ፡ በመካከላችን ምንም ጥርጥር እስከማይኖር ድረስ ምስኪኑን የሰው ልባችንን ግረዝልን። ጸሎቴ ይህ ነው። ጌታ ሆይ፡ ጥርጣሬን ሁሉ አስወግድልን። በጣፋጭነት፡ በትህትና እንድኖር፡ እንደ—እንደ እግዚአብሔር በግ በምድር ላይ እንድመላለስ እርዳኝ።

እሱ እንደተራመደ እኔም ል—ልራመድ። እሱ እንደሚናገረው እኔም ልናገር። አሳቤ እንደ አሳቡ ይሁን። ሌ—ሌሎች በእኔ ላይ... ኢየሱስን በእኔ ውስጥ ያግኙት። ጌታ ሆይ፡ እራሴን ለቀቅ ላድርግ፡ እና በአንተ ዘንድ ልገኝ። ይኸው ነው፡ እራሴን ለቀቅ አድርጌ በአንተ ዘንድ ልሁን፡ እርሱ በሚናገረው ነገር፡ ለጥርጣሬ ምንም አይነት በር እስከማይኖር ድረስ በክርስቶስ ዘንድ ልሸፈን።

93 እንግዲህ፡ ወጥታችሁ እንዲህ አትበሉ፡ "እግዚአብሔር ይባረክ! ሃሌሉያ! ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ምን ማድረግ እንደምችል እያችሁ? ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!" ገና አልገባችሁም። እርሱ እንደዚያ አላደረገም፡ በጭራሽ፡ ደረቱን ነፍቶ፡ "ምን ማድረግ እንደምችል እያችሁ? አዎን፡ ወዳጄ። እኔ እከሌ-... እባላለሁ" አላለም። መቼም ቢሆን ክብር ለራሱ ወስዶ አያውቅም፡ ክብርን ለእግዚአብሔር ሰጠ፡ ሰዎችም በዙሪያው ባለው ንጹ አየር መሆን እስኪወዱ ድረስ በትህትና እና በጣፋጭነት ተመላለሰ። ጠላቶቹ ብቻ... ደግሞም ሁልጊዜ እስኪጸልይላቸው ድረስ፡ በበቂ ሁኔታ ወደዳቸው። ይህም እርሱ ደዋ ለእኛ ያደረገልንን፡ ለሌሎች ማድረግ እንችል ዘንድ፡ የእኔ እና የእናንተ ምሳሌ ነው።

94 አሁን፡ እዚህ እንደገና በ2ኛው ክፍል፡ 13ኛው ቁጥር የሚሆነውን፡ ልብ ማለት እንፈልጋለን፡

> **ሥራህን፡ እና—የሰይጣን... ዙፋን ባለበት፡ የምትኖርበትም አውቃለሁ... ስሜንም ይዘህ ጸንተሃል፡ እምነቴንም** አል**ካድክም፡...**

95 እያችሁ፡ ሰይጣን ዙፋኑ በነበረበት ሰፍራ ይኖሩ ነበር፡ ሆኖም ግን የኢየሱስን ስም ይጠብቁ ነበር። እያችሁ፡ "እምነቴንም አልካድህም።" ምን አይነት እምነት ሰጧቸው ነበር? የመጀመሪያው፡ የጴንጤቆስጤ እምነት። በዚያ ገና በመሰራት የነበሩ፡ እንደነ ኒቆላውያን እምነት፡ ድርጅታዊነት፡ ወዘተረፈ በዚያ ነበሩአቸው፡ በመደራጀት ወደ ሕልውና የምትመጣ ቤተ ክርስቲያን፡ እርሱ ግን አላቸው፡ "እኔም ደግሞ የምጠላውን፡ ጠልተኸዋል፡ ከዚያም ርቀሃል። ስሜንም አልካድክም፡ ወደ ትንንሽ አምልኮቶቻቸውን እና ነገሮቻቸውን አልተከተልክም፡ ሰሜን በጽናት ጠብቀህ ቆይተሃል። በመጀምሪያ እንደነበረች እምነቴ አሁንም ይዘሃል።" አቤት፡ ደስ ሲል!

> በ**እነዚያ ዘመን እንኳ፡** (አ-ን-ቲ-ጳ-ሰ የምትሉት ይመስለኛል) **እምነቴን አልካድክም... ሰይጣን በሚኖርበት፡ በእናንተ መካከል የተገደለው፡ ታማኝ ሰማዕቴ አንቲጳስ ነበር።**

96 እዚህ ጋር አንድ ደቂቃ ቆ አደርገዋለሁ። "የሰይጣን ዙፋን።" በእነዚህ ነገሮች ላይ እንድንነቃቃ እንፈልጋለን፡ እንድትረዱት እፈልጋለሁ። መረዳታችሁን፡ አሁን እርግጠኞች ሁኑ። "የሰይጣን፡ ዙፋን።" እንግዲህ፡ በዘፍጥረት ላይ የሰይጣን መቀመጫ የነበረበትን፡ ያውም በባቢሎን እንደሆነ እግዚአብሔር ተናግሯል። ይህ ሁሌም ቢሆን የሰይጣን ዙፋን ነበር፡ በራእይ መጽሐፍም እንዲሁ ነው። ነገር ግን፡ ካስተዋላችሁ፡ ባቢሎን ራሷን **ከጣኦት** ወደ "ጵጵሰና" ቀየረች።

97 እና አሁን ይህ ከመሆኑ በፊት፡ ወይም በመጀመሪያዎቹ ዓመታት (ጥቂት ዓመታት)፡ ታላቁን የሰይጣን ዙፋን ተሰራ... ምን ትሉታላችሁ ካህ-...

የከለዳውያን ንጉሥና-ካህን ሆነ። ፐርሺያውያን እሱን ባሳደዱት ጊዜ የባቢሎን የስልጣን ተዋረድ ዙፋኑን ቀየረው፡ እና ባቢሎንን ለቆ ወጣ። ስሙ አ-ጣ-ሉ-ስ ይባላል፡ ታላቁ የባቢሎን ንጉሥና-ካህን፡ አጣሉስ ነው። ፐርሺያውያን መጥተው ባቢሎንን በተቆጣጠሯት ጊዜ፡ ከለዳውያን ሸሹ፡ ንጉሣቸውና-ካህናቸው፡ አጣሎስ፡ ሸሽቶ ዙፋኑ በጴርጋሞስ አደረገ። "**የሰይጣን ዙፋን** ባለበት የምትኖርበት።" ገባችሁ?

98 ስለዚህ፡ የቤተ ክርስትያን ታሪክ ለማግኘት ወደ ኋላ መመለስ የነበረብኝ ለዚህ ነው፡ የት ለማግኘት... "የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን፡" ብሎ በተናገረ ጊዜ የተፈጠረውን ፍለጋ።

99 እኔም "እንግዲህ፡ ይህ 'የሰይጣን ዙፋን፡' የተባለ ነገር፡ የት ይሆን? " ብዬ አሰብኩ፡ ከዚያም ይህ ታላቅ ንጉስ፡ ያኔ ሰልጣን ከያዙት ፐርሺያውያን የሸሸ እንደሆነ አወቅሁ (በዳንኤል ራእይ መሠረት) በሮም፡ ወደምትገኘው፡ ወደ ጴርጋሞስ ከተማ መጥቶ፡ ማዕከላዊ መንግስቱን አቆመ። ሰይጣን ማዕከላዊ መንግስቱን ከባቢሎን በማፍለስ ወደ ጴርጋሞስ አዞረው፡ ይህም (ለወደፊት) አዲሲቷ ባቢሎን የሚመሰርትበት ሰፍራ ነው። ኦህ፡ ማይ! አሁን ያለንበትን ዱካ በደንብ አግኝታችኋል። በጣም ጥሩ።

100 አሁን፡ ይህ ድንቅ ወንድም፡ አንቲጳስም፡ ሰማዕት የሆነበት ስፍራ ይህ ነው።

101 ከዚያም ዘዴውን ቀየረ። በመጀመሪያ የክርስቲያኖች አሳዳጅ ነበር። አቤት፡ ክርስትናን እንዴት እንደሚጠላ! እርሱ ራሱ ካህንና-ንጉስ ሆነ፡ በርግጥ ግን በአካሄድ እና በተፈጥሮ አረማዊ ነበረ። ከዚያም አመለካከቱን ቀይሮ ከቆስጠንጢኖስ ጋር ተባበረ።

102 ቆስጠንጢኖስ (ድሮ እና በዛሬው በጳጳሶች ጭምር) የኮሎምበስ ሰራዊት ጀማሪ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል፡ አሁን፡ ይህም የደም አፋሳሹ መሃላ ያደረገው እርሱ ነበር። ስለ ቆስጠንጢኖስ (ይህን በአክብሮት እና በትህትና እላለሁ)፡ እንደኔ ከታሪክ እንዳነበብኩት አረዳድ፡ ፈጽሞ ያልተለወጠ ሰው ነበረ።

103 እና፡ አንድ ቀን በህልሙ፡ መስቀል አየና... ጦርነቱን በዚህ ድል አደርጋለሁ፡ ብሎ ተናገረ፡ ለ... ክርስትያኖቹም እፎይታ አደርግላቸዋለሁ በማለት ቃል ገባላቸው፡ ያን ጦርነት እንዲያሸንፍ ከጸለዩለት፡ ክርስቲያን እንደሚሆን ተናገራቸው። በዚያም እርሱ... ተኝቶ፡ ህልሙን ያየበት፡ ያን ድልድይ፡ ከድልድያቸው ወዲያኛው ጫፍ ቆሜበታለሁ፡ ከዚያም ነቅቶ፡ በራሱ እና በሰራዊቱ ሁሉ በጋሻዎቻቸው ላይ ነጭ መስቀል ሳለበት። ስለዚህ በሮማ ካቶሊክ አገዛዝ ስር የሚገኘው የኮሎምበስ ሰራዊት የተቋቋመበት ስፍራው ያ ነው። ነገር ግን ያደረገው አንድም ሃይማኖታዊ ነገር የለም፡ በታሪክ ውስጥ የተጻፈው እሱ ያደረገው ብቸኛው ነገር፡ እኔ እንዳየሁት ከሆነ፡ በቅድስት ሶፊያ ቤተክርስትያን ጉልላት ላይ፡ መስቀል አስደርገዋል። (አሃ!) ያኔ ግን ፖለቲከኛ ነበር፡ የሮም ንጉሠ ነገሥት በነበረ ጊዜም፡ እርሱና ይህ አረማዊ ቄስ፡ አንድ ላይ፡ ሕብረት በመፍጠር በዚያን ጊዜ ኒቆላዊያን የተባለችውን ለብ ያለች ቤተ ክርስቲያንን አመጡ። ወደ ክሃናት ስርዓት እያጋደለ የነበረው፡ ክርስትናም፡ ይህን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲሆን ፈልገውት ነበር፡ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እና፡ በመሳሰሉትን፡ እና በ—በሰምርኔስ እንዳየነው፡ ይህን ኒቆላዊነትን ይፈልጉት ነበር።

104 እንግዲህ ይህ ኒቆላውያንነት ቀድሞ እንደነበረ እንደ “ስራ” ሳይሆን… አሁን **እዚህ** ጋር እየተቀየረ ነው፡ **እዚህ** ግን “ትምህርት” ሆኗል። **እዚህጋ** “ስራ” ስለ ነበረ፡ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ሙከራ ላይ ነበሩ፡ እዚህ በሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ግን የሊቀ ካህናት፡ አንጋፎች፡ “ትምህርት” ሆነ። አሁን፡ ገና ጳጳስ ተብለው አልተጠሩም፡ ነገር ግን፡ እንደ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ አንጋፎች፡ እያችሁ፡ ታዋቂዎች ይባሉ ነበር። ትምህርታቸውም፡ መደበኛ፡ ተራ እና መደበኛ ነበር።

105 በመንፈስ-ከተሞላው፡ በመንፈስ ቅዱስ-ከሚመራው ቤተክርስቲያን እየራቁ ነበር። በአናሣዎች ተርታ መደቧቸውና “መናፍቃን” ብለው ጠሯቸው፡ ምክንያታቸውም ከእነዚህ ከታላላቅ የሐይማኖት ተቋማት ጋር አንድ አንሆንም በማለታቸው ነው። ቤተክርስቲያን ግን ክርስቶስ በሰጣቸው ተሰፋ መሰረት፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስር በነፃነት እንድትቆይ ፈለገች፡ ይህም እርሱ ከእነርሱ ጋር በመሆን፡ ንጉሳቸው ይሆን ዘንድ ነው። ኦህ! ንጉሳቸው!

106 እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በአንዳንድ የ—የቦርድ አባላት ለመመራት፡ አመለካከቷን ለውጣ አታውቅም… እዚያ ምን ብላችሁ እንደምትጠራቸው አላውቅም፡ ካርዲናሎች፡ እና ቢሾፖች፡ እና ጳጳሳት፡ ስሕተት አልባዎች። የማይሳሳት አንዱ ብቻ እንደሆነ እናምናለን፡ እርሱም አሁን በመንፈስ ቅዱስ መልክ ከእኛ ጋር የሚኖረው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሳችን ነው፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ሆኖ፡ ከእኛ ጋር እየኖረ፡ ወደ ሕይወት ውኃ እየመራን፡ ራሱንም እየገለጠ፡ በእነዚያ በቀደሙት ቅዱሳን እና ሰማዕታት መካከል እንዳደረገው፡ የፍጥረት አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን፡ ያሳያል፡ ድውያንን ይፈውሳል፡ ሙታንን ያስነሣል፡ ራእዮችን ያሳያል፡ አጋንንቶችን ያወጣል።

107 ከእነዚያ በሮም በተሿሿሙት የኒቆላውያን ቤተ ክርስትያን፡ ከጳጳሱም ይሁን፡ ከቢሾፖች ሁሉ ግን አንድም ጊዜ እንኳን እንዲህ አይቼ አላውቅም፡ ከእነዚህ ቢሾፖች ሁሉ ሙታንን ያሥስነሳ፡ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር ያደረገ አለ የሚል የታሪክ መዝገብ አንድ ጊዜ የለንም፡ ምክንያቱም ክርስቶስ (ማለት ትንሣኤው) በልባቸው ውስጥ አልነበረም። ብኩርናቸውን በመሸጥ፡ የሐይማኖት ተቋም ለመስራት በሕብረት ሄደው ጠፍተዋል። የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ኃይል ነበራት፡ ሌላዋ ቤተ ክርስቲያን ግን በውስጧ የተከበሩ አለቆች ነበሯት፡ እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ግን በመንፈስ ጸንታ ቆየች። እየገባችሁ ነው? በጣም ጥሩ።

108 አሁን ይሄ… ስለዚህ ቆስጠንጢኖስ፡ ግዛቱን አንድ ላይ ለማጣመር፡ ያደረገው ይኸው ነው። እነዚያን ኒቆላውያንን ተቀበላቸው፡ እና አብሯቸው ሆነ (ይህም ክርስትና መሣይ የነበረ ነገር ነው)። በደንብ ገብቷችኋል? ያለ መንፈስ ቅዱስ፡ ክርስትያኖች ነን ባዮች፡ ክርስትያን፡ ተብዬዎች-ነበሩ። አቤት፡ ይህ ነገር ከውስጣችሁ ላይወጣ ስጥሞ ቢቀር ምኞቴ ነው። እያችሁ? መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው፡ ክርስትያኖች፡ የሐይማኖት ተቋም ክርስትያኖች ነበሩ። በስም ክርስቲያን ነበሩ፡ አንድ ላይ በመሰብሰባቸው ክርስቲያን ነበሩ፡ ቅዱስ ቁርባን ይወስዳሉ፡ ስርዓቶችን ይጠብቃሉ፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ግን፡ አይቀበሉም። ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው ብለው ስለሚያስቡ፡ በመካከላቸው ድንቆች እና ተአምራቶች አልነበሩም፡ ቤተ ክርስትያን ለንግስና ብቻ ይጠቀሙበት ነበር። ምን አይነት ንግስና እንደሆነ፡ ከአፍታ በኋላ እናየዋለን። እያችሁ?

109 እንግዲህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን እራሷን ከእንደዚህ አይነት ነገሮች መራቅ ነበረባት። በጴርጋሞስ፡ ግን፡ ሁሉም የተነገረው ለጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን **መልአክ** ነው። አያችሁ? ይህ ሁሉ ያደርግ ዘንድ የእርሱ ሐላፊነት ስለነበረ ነው።

110 ቆስጠንጢኖስ ግን ስለ ክርስትና ፍላጎት አልነበረውም፡ የአረማውያን ቤተ ክርስትያን፡ የቅድመ አያቶቹን ማለትም አረማዊነት ማምጣት ፈለገ። ሥር የሰደዱ የሎዶቅያ... ወይም ወደ ሮም በመግባት ሥር የሰደዱ እና የተደላደሉ የኒቆላውያን ታላቅ ትዕይንትን አሳዩ፡ አብዛኛዎቹ ሰዎችም የክርስቲያን አማኞች (ተብዬ-ዎች)፡ ተራዎች ነበሩ። እውነተኛይቱም ቤተ ክርስቲያን ግን በአናሣዎች ተርታ ነበረች፡ ሁሉጊዜ እና ሁልጊዜም እንዲሁ ነበር! በደንብ ጠልቆ እንዲገባችሁ፡ ጥቂት ደቂቃ እጠብቃለሁ። አያችሁ?

111 አስታውሱ፡ እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የምትገፋ ታናሽ መንጋ ናት። እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ድርጅት ስላልሆነች፡ ተደራጅታ አታውቅም፡ በምድር ላይ በመንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ብልቶች ውስጥ የምትንቀሳቀስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢራዊ አካል ናት። ስለዚህ ክርስቶስን ድርጅት ማድረግ አትችሉም፡ አትችሉም። አሁን፡ ይህ ነገር በሎዶቅያ ዘመን ላይ እንድትይዙት እፈልጋችኋለሁ። አስታውሱት ጠብቁትም፡ ምክንያቱ የተናገርኩት ቃል ሁሉ በዚህ ቴፕ ውስጥ ተቀድቷል። አሁንም አስታውሱት፡ በአእምሯችሁ ውስጥ ያዙት፡ እውነተኛይቱ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ ተደራጅታ አታውቅም።

112 በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀ ድርጅት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ከሷ በፊት የተደራጀ ድርጅት በጭራሽ አልነበረም፡ ካቶሊኮች እንደሚሉትም እ—እሷ “እናት ቤተ ክርስትያን” ይሏታል። እሷ “እናት ቤተ ክርስትያን” ናት። የድርጅት አብያተ ክርስትያናት እናት። መጽሐፍ ቅዱስም ይናገራል፡ ስለዚህ “እናት ቤተ ክርስቲያን” ናት ሲሏችሁ መጨቃጨቅ አትችሉም፡ በርግጥም “እናት ቤተ ክርስቲያን” ናት። በራዕይ 17 ላይ በደንብ ተመስላለች፡ አሁን በቀጥታ ወደ እሷ እንሄዳለን። በጣም ጥሩ።

113 እንግዲህ፡ ቆስጠንጢኖስ፡ በዚህ አእምሮው ግዛቱን ለማጠናከር (ሮም ሁልጊዜ፡ የዓለምን ቁልፎች ለመያዝ እንደምታደርገው)፡ የክርስትና ሃሳቦች በማስወገድ የአረማዊ ሃሳቦቹ ማስገባት ፈለገ፡ እንደምንም ብሎ ሁለቱን በአንድነት ቀየጣቸው፡ ይህም ሁለቱም አንድ ላይ በመበየድ ሁለተኛ የሌለው ግዛት ለራሱ ለመስራት ስለፈለገ ነው። አያችሁ? ምክንያቱ ይህ ነገር... ቆንጦንጢኖስን፡ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ ገዥ እንዲሆን ስለሚያስችለው ነው።

114 ስለመለወጥ ከሆነ ግን፡ ገና—ገና ፖለቲከኛ ነበረ፡ አንዳንዶች ሊያደርጉት እንደሚሞክሩ፡ የእግዚአብሔር ሰው አልነበረም። አልነበረም! ለእኔ ክርስትና የሚመስል አንድም ነገር በጭራሽ አላደረገም። ስለዚህ በኒቆላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአንዱ ጉልላት ላይ መስቀል አኖረ፡ እና ክርስትናን የሚመስለውን የተድረገ ሌላ ማንኛውንም ነገር፡ በጭራሽ አላየሁም፡ ምናልባት... በዚያች ሌሊት ህልም ስላለመ፡ ያኔ **እዚያ**፡ በጋሻዎቹ ላይ ቀብቷል፡ ክርስቲያኖቹም ጦርነቱን እንዲያሸንፍ ጸልየዉለት ነበር።

115 እንግዲህ፡ ግዛቱን ማጠናከር ወደደ። እና ይህን ለማድረግ፡ ወደ ኒቆላውያን ቤተ ክርስቲያን፡ የአረማውያን የጣዖት አምልኮ በዓላትን አስተዋወቀ። ይቋቋም ወደ ነበረው መደበኛ ቤተ ክርስቲያን ብዬዋለሁ። የጣዖት አምልኮ ሥርዓቶችን ወደዚህ የኒቆላውያን ቤተ ክርስቲያን አመጣ፡ እና የካቶሊክ እምነት መወለድ ያ ነበር።

116 አሁን፡ ወንድሜ፡ ታሪክን እየጠቀስኩ ነው። እኔም በሺዎች የሚቆጠሩ የካቶሊክ ጓደኞች አሉኝ፡ እና ልክ እንደ ፕሮቴስታንቶቹ እነርሱም ጓደኞቼ ናቸው። ግን ፕሮቴስታንቶች ሊመኩባቸው አይችሉም፡ እስከ ማታ ድረስ ጠብቃችሁ፡ እዩአቸው። አያችሁ? ተመሳሳይ ነገር ሲያደርጉ ታያላችሁ። ማሰሮ ጀበናን አንቺ "ጥቁር" አትላትምና። አያችሁ፡ ምክንያቱ ያ—ያው ነው አይለያዩም፡ በሁለቱም ላይ የገባ መንፈስ አንድ ነው። እና ለምን ያንን ነገር ሁልጊዜ እንደምኮንነው ትረዳላችሁ። ምክንያቱም ስህተት ነው! በውስጤ ያለው መንፈስ፡ እንዲህ ለማድረግ ከሞከርኩ፡ ከውስጤ የሚገፋኝ ድምጽ ካለ፡ እኔ ዝም ማለት አይቻለኝም፡ ሁሌም እንደዚያ ነው። እነርሱ የሚጠራሩበት...

117 ታላላቅ ሰዎች፡ ታላላቅ የሐይማኖት መሪዎች እንዲህ ብለውኛል፡ "አገልግሎትህን ታበላሻለህ። ወንድም ብራንሃም፡ አንተ የምታደርጋቸው ነገሮች" እንዲህ ይላሉ፡ "ይህ—ይህ አንተን አይመለከትህም። እግዚ አብሔር አንተን የጠራው ለታመሙት እንድትጸልይ ብቻ ነው።"

118 እግዚአብሔር ለታመሙ ሰዎች ከመጸለይ በላይ እንድሠራ ጠርቶኛል። የታመሙ ሰዎች የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ የምጠቀምበት አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ያ ብቻ ነው፡ ለታማሚዎች፡ ለታመሙት መጸለይ ትንሹ ነገር ነው። አያችሁ? የምንናገረው ስለ **መልእክቱ** ነው። እነዚያ ነገሮች እንደገና ይመለሳሉ፡ የታመመ፡ አንድ የታመመ ሰው፡ ሊፈወስ እና እንደገና ሊሞት ይችላል። በእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ሰው ግን የዘላለም ሕይወት አለው። ስለዚህ እግዚአብሔር የታመሙትን ለመፈወስ ብቻ አይዞርም። ያ ስጦታ ለአጥቢያው አካል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛል፡ አንዱ ላይ፡ ከዚያም ሌላው ላይ፡ እና ከዚያም ሌላኛው ላይ፡ ከዚያም በሌላው። አያችሁ? እነዚያ፡ ስጦታዎች፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይመላለሳሉ። ያ ግን ከዚያ በላይ ነው፡ እንደተረዳችሁት ተስፋ አደርጋለሁ። በጣም ጥሩ።

119 የካቶሊክ እምነት መወለድ፡ እንዲህ ለማድረግ ነበረ፡ ይህም የክርስትያኖችን እና የአረማውያን ዓይን ለ—ለመማረክ፡ ሁለቱም አንድ ቤተ ክርስትያን እንዲሆኑ ለመበየድ ነበር።

120 ኦህ፡ በቀደምለት ማታ አንድ ሰው ቁራጭ ወረቀት እዚህ አስቀምጦ ነበር፡ ብይዘው ኖሮ መልካም ይሆን ነበር። ረሳሁት እንጂ፡ አመጣዋለሁ ብዬ አስቤ ነበር፡ ክፍሉ ውስጥ እዚያም እዚህ ብዙ ነገሮች ስለነበሩ ነው። አሁንም እነሱ ተመሳሳይ ነገር እያደረጉ ይገኛሉ፡ የምትመርጡት የመጨረሻው ሰው በመረጣችሁ ጊዜ ትጀምሩታላችሁ። ካቶሊክንም ሆነ፡ አይሁዱን፡ ወይም ፕሮቴስታንቱን የማይጎዳ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ ለመጻፍ አሁን እየሰሩ ነው። ለነገሩ ሁሉ የሚስማማ መጽሐፍ ቅዱስ ሊያዘጋጁላቸው ነው። የሌላኛው ቆስጠንጢኖስ ተንኮል አይታያችሁምን? ታሪክ ራሱን እየደገመ ነው። አሁን፡

እያችሁ፡ እና ያንን... በቀደም ማታ ላይ ሳነበው ሰምታችሁኛል፡ አይደል? እና ቤ—ቤት ውስጥ ተቀምጧል፡ ለብዙ ዘመናት ሲሰሩት የቆየ ነገር ነው።

121 አሁን እንዲህ ይላሉ፡ "በ 62 እንዲህ ይሆናል... " እና እስተውሉ ፖፕ ጆን 12ኛው እንደመጡ-... ሁሉም ትናንሽ ሴቶች ልጆች አብያተ ክርስቲያናት ወደ እናት ቤተክርስትያን ወደ ቤት እንዲመለሱ ጠየቁ። ታያላችሁ፡ ትመለሳለች። ይመለሳሉ! አይቀርላትምች፡ ድሮም ተመልሰዋልና። ወደ ኋላ መመለስ አያስፈልጋቸውም፡ አሁን እዚያ ናቸው።

122 እንዳልኩትም፡ "ይህች አገር እንዲህ ትላለች፡ 'ሚስተር ኬኔዲ፡ ከተመረጠ፡ ካቶሊኮች ያሸንፋሉ።'" ያሸንፋሉ? ድሮ ከረጅም ጊዜ በፊት አሸንፈዋል፡ እናንተም ምንም አታውቁም። ለመምህራኖቻቸው የሚከፍላቸው ማነው? እነዚህ ነገሮች ወደ ትምህርት ቤታቸው እንዴት ገቡ፡ ካቶሊካዊነትን በትምህርት ቤቱ ውስጥ እንዲያስተምሩ እንዴት ያደርጋሉ? እና እናንተ ግብር ከፋዮችም ትከፍላላችሁ። አቤት፡ እንዲህ፡ እዩት እስኪ፡ አፍንጫችሁ ስር ነው። ኦህ፡ ማይ፡ እንዴት እንደሚሰራው! መፅሃፍ ቅዱስም በሽንገላ ያደርጋል ይለዋል፡ ደግሞም አድርጎታል፡ አያችሁ፡ በትክክል፡ አያችሁ፡ በምንም ላይ ግብር ያስከፍላል። ስለዚህ፡ አቤት፡ እዚህ ላይ ብዙ ማለት ይቻላል። ከእነዚህ ነጥቦች ልውጣና፡ እንደገና እነዚያን ለማንሳት ልመለስ።

123 ይህ ነገር እንዲሠራ ለማድረግ፡ ቆስጠንጢኖስ ብዙ ዓለማዊ መዝናኛዎችን አዘጋጅቷል ይህም የአረማውያንንም ሆነ የክርስቲያኖችን ትኩረት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሳብ ነው። መንፈሳዊ አስተሳሰብ አላችሁን? ታስባላችሁ ወይ? የዘመኑ መልዕክት ይህ አይደለም ወይ? ቤተክርስቲያን የቡንኮ ጨዋታዎች፡ ግብዣዎች፡ የመኪና ሰጦታዎች አሉ፡ ይህም እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ብቻ፡ እዚሁ ላይ ግሩም ሰፍራ እስኪያገኙ ድረስ፡ ኃይላቸውን በአንድነት ለመበየድ ነው።

124 እንግዲህ፡ ያ ታሪክ ነው፡ ሌላ ነገር ለመናገር—ማንም ምክንያት አይኖረውም፡ የሆነውን ብቻ እየጠቀሱ ናቸው። እርሱ ያደረገው ግን፡ የኒቆላውያንን ቤተ ክርስቲያን አንድ ላይ ለማሰባሰብ፡ ዓለማዊ መዝናኛዎችን በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን አንድ ላይ ለማጣመር ነው። አስታውሱ፡ ያን ዳግም-የተወለደችውን ቤተክርስቲያን መንካት አልቻለም። አልቻሉም፡ ወዳጄ፡ ማናቸውም አልቻሉም። መደበኛዋ የኒቆላውያን ቤተ ክርስቲያን ግን ወደቀችላቸው።

125 አሁንስ በፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናችን ምን አለ? የሾርባ እራት፡ መዝናኛዎች፡ ስኬቲንግ፡ (ኦህ፡ ማይ!) የጨርቃ ጨርቅ ንግድ፡ እና ወዘተረፈ፡ አያችሁ። ይህ እውነት እንደሆነ፡ እናንተም ታውቃላችሁ። እሺ፡ እንግዲህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህ—የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፡ እውነት ነው። ስለዚህ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጥፋተኞች ናቸው! አያችሁ?

126 እንግዲህ፡ ምድር ቤት ውስጥ ውስጥ የሾርባ እራት እና ጭፈራዎች መደረግ በእግዚአብሔር—ዕቅድ በፍጹም አልነበረም፡ ሌሎች የሚደረጉ ነገሮችም፡ ለፓስተሩ ክፍያ መክፈል እና የመሳሰሉ ነገሮች አልነበሩም። ሰዎች አሥራት እንዲያወጡ ብቻ ቢማሩ ኖሮ፡ ያ ብቻ ይሆን ነበር። የእግዚአብሔር እቅድ

ያ ነውና። እግዚአብሔር የራሱ ዕቅድ አለው፡ ሰው ግን የእግዚአብሔር ዕቅዶችን በማዳቀል፡ የራሱ ዕቅድ ማውጣት ይወዳል። እሺ።

127 እንግዲህ፡ እነርሱ ይህ በማድረጋቸው፡ ሕብረት አደረጉ እና የጥንቷ... በኋላም፡ ጥንታዊቷ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ሰሩ። ይህም በመጀመሪያው ታላቁ የኒቂያ ጉባኤ ነበረ... እኔ ይህን ባነበብኩ ጊዜ፡ በጉልበቴ ላይ ወደቄአለሁ። ታላቁ የኒቂያ ጉባኤ የተካሄደው 325 **ዓ.ም.** ነበረ፡ ሁሉም ተሰብሰበው ነበር፡ የክርስትና እምነት አባቶች እና ጳጳሳት ሁሉ በኒቂያ ተሰበሰቡ። በ325 **ዓ.ም.** ነበረ፡ የኒቂያ ጉባኤ የተባለበት ምክንያት ለዚህ ነው። ወ—ወ—ወደ ኮንቬንሽኑ ወይም ወደ ጉባኤው፡ አንድ ሺ አምስት መቶ የሚሆኑ ልዑካን መጥተው ነበር፡ አንድ ሺ አምስት መቶ ልዑካን፡ የምእመናን ብዛት ግን (ልዑካኑን) በቁጥር አምስት ለአንድ ይበልጡ ነበር፡ ሆኖም ግን፡ እነዚህ ሁሉ ኒቆላውያኖች ነበሩ (ተራ እና መደበኞች) እና የቆስጠንጢኖስ ፖለቲካዊ እቅድ፡ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስትያን በምርጫ-ቁጥር ብዛት ድል ተነሣች፡ ሰርዓት እና ትእዛዛት—በኤጲስ ቆጶሳት እና በሰዎች ቅዱስ ትዕዛዝ ለማስተላለፍ፡ መንፈስ ቅዱስን ወደ ጎን በማድረግ፡ ስልጣኑን በኤጲስ ቆጶሳት፡ በካርዲናሎች፡ እና ጳጳሳት፡ ወዘተረፈ ተደረገ።

128 በባለፈው ሰብሰባ ላይ የዲሞክራት ፓርቲ የተጫወተበት ተመሳሳይ ጠማማ ሰምምነት ይህ ነበረ! እንግዲህ፡ ትክክል ነው። አሁን፡ እኛም... እኔ... ሪፓብሊካኖች እንደው በጣም-ቀርፋፎች ይሆናሉ። እኔ ግን የማወራው ስላረጋገጡት ነገር ነው፡ በካሊፎርኒያ (ኤድጋር ሁቨር) እና በሌሎች ብዙ ቦታዎች፡ አቶ ኒክሰንን የምትመርጡባቸው ማሽኖች በብዙ ጣብያዎች ተቀምጠው ነበር፡ ሰትመርጡ ግን በተመሳሳይ ጊዜ ለ—ለ ኬኔዲ ትመርጣላችሁ። ዕድል የለውም። እንግዲህ፡ ይህ "ስህተት" መሆኑን ካረጋገጡ፡ ታዲያ ለምን መፍትሄ አያደርጉም? እየኖርንበት ያለው ሰዓት፡ ያ ነው፡ በመጨረሻው ዘመን እየኖርን ነንና። ያውቁታል፡ ጠማማ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡ አሁንም ምንም ነገር አያደርጉም።

129 ያኔም ጠማማ አለባበስ ነበረ፡ እነሆ አሁንም በድጋሚ በመወለድ ይገኛል፡ ወደ አንድ ትምህርት ለመጠቃለል፡ አሁንም በአንድ ሰው ውስጥ ለመግባት፡ ወደ ኒቆላውያን ትምህርት ለመግባት፡ ይህም ያኔ—**ስራ** ብቻ የነበርው፡ አሁን "ትምህርት" የሆነ ነው። በእነ አል ሰሚዝ ዘመን **ስራ** የነበረ፡ አሁን ግን "ትምህርት" ሆኗል። ኧህ-ህህ፡ ኧህ-ህህ። አሁን እዚህ፡ በእኛ ዘንድ ገብቷል። "አቤት፡ አሪፍ-ቅምጥል ፕረዚዳንት እንደሚሆን፡" በአእምሮዬ ውስጥ ምንም ጥርጥር የለም፡ ያለ ጥርጥር፡ በቀጣይ ዙር፡ እስኪበየድ ድረስ፡ ተራ የሆኑትን አረማዊ ክርስትያኖችን በአንድነት ይበይዳቸዋል።

130 ጳጳሶቹም፡ ካርዲናሎቹም፡ ይህን ወደ አንድነት ለማምጣት፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እየሰሩ ይገኛሉ። የእንግሊዝ ሊቀ ጳጳስ፡ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ፡ አግኝቼዋለሁ፡ ሰላም ተባብለናል፡ እኔ ራሴ፡ አነጋገርኩት፡ በእንግሊዝ በነበርኩበት ጊዜ፡ ጭኑ ድረሰ ሌጊንግ የለበሰ፡ እና (አቤት!) አሰቂኝ-ልብስ የለበሰ ሰው ነው። እና ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ከመቶዎች ዓመታት በኋላ፡ ጳጳሱን ለመጎብኘት ሄዶ ነበርና። ምንድነው ይሄ? የመጨረሻው ሰዓት ላይ ነን!

131 ለዛ ነው ዛሬ ማታ ሌላ ቦታ ከመዋል ይልቅ እዚህ መድረኩ ላይ የተገኘሁበት ምክንያት ይህ ነው ለታመሙ ለመሰበክ እና ለመጸለይ። ሁሉንም ሰው በዚህ መድረክ ላይ ላገኛቸው አልችልም (እነዚህ መልዕክቶች ግን ደጋግመው ይችላሉ)፡ በቴፕ እየቀዳን ወደ ዓለም ሁሉ የምንልክበት ምክንያትም ለዚህ ነው፡ ምናልባት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ወደ እምነት ይመለሱ ይሆናል።

132 ክርስትያን ዘመን መጨረሻ፡ በይሁዳ፡ የራእይ መጽሐፍ ከመጻፉ አስቀድሞ፡ ማለት የኢየሱስ ወንድሞ፡ (አብሮ አደግ ወንድም) የሚባለው ቅዱስ ይሁዳ፡ እንዲህ አለ፡ "አንድ ጊዜ ለቅዱሳን ስለ ተሰጠ እምነት እንድትጋደሉ እወዳለሁ።" ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ከሞተ በኋላ፡ ከእሱ መራቅ ጀመሩ። አሁንስ ዛሬ ማታ ምን ያህል ርቀዋል? ተመልከቱ።

133 እንግዲህ፡ የመጀመሪያው የኒቂያ ጉባኤ፡ በ330... 325 **ዓ.ም.** ነበረ። በሰብሰባው ላይ ወደ አንድ ሺ አምስት መቶ የሚጠጉ ልዑካን እና ጳጳሳት ተገኝተዋል፡ ነገር ግን በጭጋጋማ፡ አውሎ ነፋሳማ ሸንጎ ውስጥ፡ የበላይ ሆኑባቸው። የበላይ ሆነው፡ በዚያም ኒቆላዊነትን በመምረጥ አሸነፏቸው፡ ይህም የሆነበት ምክንያት... ቤተ ክርስትያኒቱ በሙሉ፡ ከጳጳሳት ወይም—ወይም ቢሾፖች፡ ወይም በሌላ ነገር ቁጥጥር ስር ለማድረግ፡ ሥልጣኑን ከቤተክርስቲያን ተቀብሎ ለጳጳሳት አሳልፎ ለመስጠት፡ ይህም ቤተ ክርስትያኒቱ በቢሾፖች እንድትመራ እና እሷን በሚመለከት ሁሉ እነርሱ ብቻ እንዲሆኑ ነው።

134 ዛሬ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አስተውላችኋል? "መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ አትችሉም፡ እናንተ መተርጎም አትችሉም። ያ የቢሾፑ ስራ ነው።" ከየት እንደመጣ አያችሁ? አሁን ኒቆላውያኖች መጓተት እና መንከባለል ከመጀመራቸው በፊት ምን እንደነበሩ ማየት ትችላላችሁ። ይያኔ በዚያ ተወለደ። ይህ እውነት ነው። የክርስትና መልክ ነበረው፡ አሁንም ያው ነው!

135 ከዚያ በኋላ ፕሮቴስታንቶችም ያንኑ ዓይነት ስልት ቀጠሉበት። መጽሐፍ ቅዱስ በራዕይ 17 ላይ፡ "እናታቸው እና ሴቶች ልጆቿ፡" ይላቸዋል። ጌታ ቢፈቅድ፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንገባበታለን። አሁንም ተመሳሳይ እንደሆነ አስተውሉ፡ ወረውታል። አሁን፡ ቆስጠንጢኖስ የተጠቀመው የበለዓምን ስልት ነው።

136 እንደው፡ የቻላችሁትን ያክል እንድትሰሙኝ እፈልጋለሁ። አሁን፡ እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ "እምነቴን አጥበቀህ ይዘሃል፡" ይላል። አሁን፡

> ... **የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ፡ ምክንያቱም በአንተ... ዘንድ... ምክንያቱም በአንተ ዘንድ እነዚያ ነገሮች** ይዛችኋል... (እነዚህ **እዚህ** አይደሉም፡ ነገር ግን **እዚያ፡** እነዚያ **ነበሯቸውና፡** "በጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን—ውስጥ ታገኟቸዋላችሁ፡" አያችሁ) ... ይዛችኋል **የበልዓምን ትምህርት—በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን እንዲጥል ለጣዖት የተሠዋውን እንዲበሉ፡ እና** እንዲሴስኑ፡ **ባላቅን ያስተማረ ትምህርት።**

137 ስለዚህ፡ ቆስጠንጢኖስም በለዓም ያደረገው ዓይነት ስልት ተጠቀመ። ቢሾፖች፡ አብያተ ክርስትያኖች ወዘተረፈ ሊመሯት እና ስልጣንን ከምእመናን

እንዲወስዱ ከተመደበበት፡ ከዚህ ከጉባኤው በኋላ፡ ስብሰባ አካሂደው ነበር፡ “ህዝቡ ስለራሳቸው ማሰብ የማይችሉበት፡ ቅዱሳት መጻሕፍትንም የመተርጎም መብት የሌለበት ሁኔታ።” የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ሁሉ፡ ለካህናት የተመደበ ነበረ።

138 በመጨረሻም፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ **ዋና** ካህን ሾሙ፡ እርሱም... ምስሌኔ፡ ማለት ጳጳሱ ነበር። አሁን ግን ጨርሶ እንዲህ ወደ ማለት ደርሷል፡ “ዕውቀት ሁሉ—የካህኑ ነው፡ ጉባኤው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የለበትም፡ ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልጋቸውም፡” እና፡ በእውነትም፡ ከሆነ... መጽሀፍ ቅዱስ ከአጠገባቸው ተወሰደ። አሁንም ሐላፊነቱን በሙሉ በራሳቸው—ላይ አደረጉና ጥሩ መስሎ ስለታየ ለእኛም የግድ መርጠውልናል።

139 ሀብታሞች እና የመሳሰሉ ነገሮች ስለነበሩ፡ ነገሩ ጥሩ ይመስላል፡ እሱም የሰጣቸውም... በዚህ ታላቅ ስብሰባ ላይ፡ በአንድነት በጠራቸው ጊዜ፡ ቆስጠንጢኖስ ለቢሾፖቹ ጥሩ ሕንፃዎችን ሰጣቸው፡ ጠቀም ያለ ገንዘብ ያዘና—እነዚያን ግዙፍ ታላላቅ ሰፍራዎች... ሕንጻዎች፡ እነዚህን—እንደ ቤተ ክርስቲያን ቤቶች፡ መጠቀም እንዲችሉ ለቤተ ክርስቲያን አሳልፎ ሰጠ። አቤት፡ እጅግ የሚያማምሩ፡ በደንብ የተሰሩ፡ ዓይነት ቤቶች ነበሩ፡ ሁሉንም ለቤተ ክርስትያን ሰጣቸው።

140 ከዚህም በተጨማሪ፡ እነዚህን ቢሾፖች ታላላቅ መጎናጸፊያዎች፡ እስከነ ውስጥ ሱሪ እና ውስጠኛው መደረቢያዎች ሁሉ አለበሳቸው። ከዚህም በተጨማሪ፡ ከፍ ያለ ቦታ ሠርቶ... ወይም ገንብቶ፡ በዚያም እንደ ጣዖት አቆማቸው። ከበታቻቸውም የእብነበረድ መሠዊያዎችን፡ በታቻቸው ሠራ። ይህንንም ሁሉ ከአረማዊ ሃሳቦችን፡ በሌላ፡ በመቀየር፡ ቢሾፓቸውን በመውሰድ ክርስትናን ወደዚያ አደረሰው። አያችሁ፡ ጣኦትን በማውረድ ቢሾፖቹን ያቆማቸው ነበር። አያችሁ፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ መሠውያን ይሰራለታል፡ አምላክ ያደርገዋል። ቢሾፑን ያቆማል፡ ያም ሰልጣን-ሁሉ አለው፡ በደንብ ያለብሰዋል አምላክ ያሰመስለዋል። የአረማዊው አምላካቸው ከማድረግ ይልቅ፡ ኢየሱስ የለበሰው መጎናጸፊያ አይነት ያደርጉበታል። አያችሁ? እና እንደ ጣኦት የተቀመጠ እንዲመሰል ያደርጉታል።

141 አቤት፡ አረማዊው ምን እንደሚል እሰቡት፡ “እንዴ፡ ወደዚያ መሄድ አለብኝ፡ አሁን የሚመልሰልን አግኝቻለሁ። ድሮ ለጣኦታት እናገር ነበር፡ ይህ ሰው ግን ያነጋግረኛል ይመልስልኛል።”

142 ክርስቲያኖችም እንዴት አሰበው ይሆናሉ፡ “እንዴ፡ ይሄ ቆንጆ ነገር ነው። አሁን እምላካችን አጠገባችን ስላለልን የወደድነውን ሁሉ እናደርጋለን። ብንፈልግ... ብንፈልግ እናናግረዋለን፡ እሱም ማድረግ የሚገባንን ይመክረናል። ሐጢአት ብንሰራም፡ እንናዘዝለታለን፡ ትንሽ ክፍያ ነገር እንሰጠዋለን፡ እና ትንሽ... ትንሽ ጸሎት ዓይነት ነገር እናደርጋለን፡ እና ከዚያ በኋላ እንደው፡ ነጻ ነን፡ እንደገና በነጻነት መንገዳችንን እንሄዳለን። ስለ ሌላ ምንም መጨነቅ አያስፈልገንም።”

143 “አቤት፡ በጣም ጥሩ ነገር ይመሰላል።” አዎን! ለባለ አእምሮ አሁንም ጥሩ ነው፡ ዳግም-ለተወለደ ለእግዚአብሔርን ልጅ ግን ይህን በፍጹም አትከትቡትም። ይህን ፈጽመው ሊያደርጉበት አይችሉም። ያመነውን ያውቃልና

የሰጠውንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ መጠበቅ እንዲችል ገብቶታልና። እና ያለፈውን ነገር እየረሳን፥ በክርስቶስ ያለውን ታላቁን ጥሪ ለመያዝ እንዘረጋለን። አሜን! አቤቱ፥ ምስጋናዬ ብዙ ነው!

144 በደንብ ያለብሰዋል፥ ከፍ ብሎ ይቀመጣል፥ ጥሩ ቤተክርስትያን፥ ከሰሩም ቆንጆ የእምነ በረድ መሰዊያ ይደረግለታል። ኦህ፥ ማይ፥ በሙሉ የተሰተካከለ ነው። በጣም ጥሩ። መሰዊያው፥ እምነ በረዱ የተለበጠ ነው፥ ቆንጆ ነው። ገና ወደፊትም ታዩታላችሁ፥ አንድ ናቸው። መሰውያ፥ በወርቅ የተለበጠ፥ በዕንቆች እና በከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ ነው። ቆንጆ! ለኒቆላውያን እና ለአረማውያን በጣም የሚመጥናቸው ነበር። ምን እንዳደረገ አይታችኋል? የጣዖት ገድላት ሥርዓቶችን፥ የአረማውያንን ሀሳቦች ወሰደና፥ ክርስትናንም ከዚህ የተሻለ የማያውቁትን፥ ቀዝቃዛና ተራዎቹን ወሰደና፥ የተለየ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ያልነበራቸውን፥ በዚህ ምድር ላይ አምላክ አደረጋቸው፥ መሠዊያም አደረገላቸው፥ ኃጢአታቸውን ያስተሰርይ ዘንድ የሚቆም አምላክ አደረገላቸው። መንፈሳዊያን ናችሁን? ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ? ምን እንደሆነ አይታችኋል? በምድር ላይ ኃጢአትን-የሚያልፍ ይቅርታ።

145 ይህ ከራሴ አሳብ አውጥቼ አልጠቀስኩም፥ ይህ ታሪክ ነው። የዚህን ቅዱሱን ታሪክ ገጽ እና ቁጥር ልነግራችሁ እችላለሁ፥ ልክ እንደነ ጆርጅ ዋሽንተን እና፥ እንደ አብራሃም ሊንከን፥ እና እንደ ጌቲስበርግ ጦርነት፥ ወዘተረፈ ልነግራችሁ እችላለሁ። እዚህ የጠቀስኳቸው ነገሮች ሁሉ ታሪክ ናቸው፥ በትክክል።

146 እና፥ ለእነዚያ ተስማምቷቸዋል... ዳግም-ለተወለደች ቤተ ክርስቲያን ግን አይጠቅምም። አይ፥ ጌታዬ! እንግዲህ፥ አንድን ሰው ሊቀ ጳጳስ እንዲሆን፥ እና ገድላትን እንዲያነብ፥ እዚያ ሲያስቀምጡት፥ እውነት ነው ሙሉ ወንጌልን ከውስጡ አሽቀንጥሮ ይጥላል። ዛሬም እንዲሁ ነው። እነዚያ ዘመናት አሁን አልፈዋል፥ እያችሁ፥ ሌላ ቀን ሆነው፥ በሌላ ምሳሌ፥ ተደርበው ይቀጥላሉ። አቤት፥ አንድን ሹም እንደ አምላክ እዚያ ሲያስቀምጡ፥ አንዳንድ የሚናገራቸው ገድሎች ይኖሩታል።

147 አረማውያንም ወደ ሞቱት ቅድመ አያቶቻቸው እንደሚጸልዩ ልብ በሉ። የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንም ቆማ እንዲህ ትላለች፥ "በቅድስት ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እና በቅዱሳን ተራዳኢነት አምናለሁ።" እናንተ አንተ ሜቶዲስቶች ሆይ፥ ፕሬስቢቴሪያኖች እና ሉተራኖች አሁን ፊታችሁን ደብቁ። በሙታን የሚማልድ ማንኛውም ነገር መናፍስታዊነት ነው! በትክክል። አሁን፥ ግን፥ ፕሮቴስታንቶች ካቶሊኮች ላይ መሳቅ አይችሉም፥ እሱም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፥ እነዚህ ሁሉ ኑዛዜዎችን-በሙሉ ይፈጽማል የሚያምነውም ያው ነው፥ በውኃ ጥምቀቱ ወደ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይጠመቃል፥ ኑሮአቸውን በትክክል የሚኖሩትን ሁሉ ይሳለቅባቸዋል ይቃወማቸዋል፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል በእግዚአብሔር ኃይል የሚጮኹ ሰዎችን ሲያይ፥ ወደ ውጪ ወጥቶ ይሳለቃል። ይህ ሁሉ ያደርጋል።

148 እያችሁ፥ መናፍስት አይሞቱም፥ ሰዎች ይሞታሉ፥ መናፍስት አይሞቱም። እያችሁ? መንፈስ ቅዱስ፥ አይሞትም። ያኔ ኢየሱስ ላይ የነበረው፥ አሁን በቤተክርስትያኑ ውስጥ ነው፥ እሷ አካሉ ናትና፥ **ለ**ቤተክርስቲያኑ እስኪመጣላት

ድረስ ሁል ጊዜ ይኖራል። አያችሁ? አሳዳጆች ቢሆኑም፡ ያኔ—በዚያ ዘመን ይሳለቁባቸው ነበር፡ ዛሬም አሉ። እግዚአብሔር ባርያውን እንጂ መንፈሱን ከምድር ላይ አያነሳም። ዲያብሎስም ባርያውን እንጂ መንፈሱን ከመሬት አያወጣም።

149 የኢየሱስን ሞት ያጸደቁት ካህናት፡ እሱ "ሟርተኛ ነው፡" ወይም "ዲያብሎስ ነው" ያሉት ሁሉ፡ እነዚያ ወገኖች እንደሌሎች ሐይማኖተኛ ሰዎች በጣም ሐይማኖተኞች የነበሩ ናቸው። በትክክል። መጽሐፍ ቅዱሱን ቃል በቃል ያውቁታል፡ ትክክለኛ ትርጓሜው ግን አያውቁትም። የራሳቸው ሀሳብ ነበራቸው፡ ሌላ ምንም ነገር አይሰሙም። ያን ጊዜም እርሱን አይተውታል እና አውቀው... ኢየሱስ እያንዳንዱ ነቢይ ስለ እርሱ የተናገረውን ሁሉ ለማድረግ ብቁ እንደነበረ እንዴት ማየት ተሳናቸው? ዕውሮች ነበሩ። እግዚአብሔርም እኛ የመዳን እድል እናገኝ ዘንድ፡ በራሱ ዕቅድ አይኖቻቸውን እንዳሳወራቸው ይናገራል።

150 አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንደገና ትንቢት ይናገራል... ይህም እኛ በዚህ በጴንጤቆስጤ ዘመን ውስጥ እንዳለን፡ ይህም "የተራቆተ፡ ጎስቋላ፡ ዕውር ሲሆን፡ መሆኑን የማያውቅ።" የፊላዴልፊያ፡ የቤተክርስቲያን ሁኔታ ነው። ኦህ፡ እናንተ መደበኛ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያኖች፡ እና ጴንጤቆስጤዎች ሆይ! ይኸው፡ እራሳችሁን ተመልከቱ። አንዳንዴ እዚህ ለተቀመጣችሁ ሰዎች አይደለም፡ በቴፕ ላይ ነኝ፡ አያችሁ፡ ወዴት እንደሚሄድ አውቀዋለሁ። አያችሁ? ንስሐ ግቡ! ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱ! ወደ ክርስቶስ ተመለሱ!

151 እሺ፡ ያኔ የተፈጸመው ነገር ግን ይህ ነው፡ ወንጌሉ በሙሉ ተገፍትሮ እንዲወጣ ተደረገ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ምልክቶችና ድንቆች ተወገዱ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ወገን የነበሩት አባላት ከሌሎቹ መካከል ከተባረሩ በኋላ፡ ከዚያም የእንዲህ ዓይነት ነገሮች ዘመን አልፏል በማለት ካዱ። እና በዚያ ላይ... ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ! በትክክል ነው። የነገሩን መንፈሱን ማየት አይችሉም? መጀመሪያ፡ እንደነገርኳችሁ፡ መንፈሳዊ አስተሳሰባችሁን ታጠቁ፡ እግዚአብሔር ልባችሁን ይክፈት። ወዲያ ወዲህ አትፍገምገሙ፡ ጸንታችሁ ስሙ፡ ከዚያም "መንፈስ ቅዱስ፡ ገልጦልኛል። አይቼዋለሁ፡ ይኸው ነው፡" በሉ።

152 ገድሎች። የት ነው? ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤዎች ሳይቀሩ፡ ሃይማኖታዊ ገድል ብቻ ሆነዋል። አንድ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ፒያኖ መምታት፡ **ሌላ ሌላ ነገር**፡ ትንሽ ወደላይ እና ወደ ታች ይዘላሉ፡ ፒያኖው እንደቆመ፡- ብርርርርር! ይወጣሉ፡ ያታልላሉ፡ ይሰርቃሉ፡ ይዋሻሉ፡ ምንም አይቀራቸውም። እውነተኛው ነገር... ከመጋዝ ጋር እስከ መጣላት ቁጣቸው ብዙ ነው፡ ስለ ሰው ሁሉ እና ስለነገሮች ሁሉ ያወራሉ። አያችሁ? ይኸው ነው። ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ካቶሊክ ብቻ ሳይሆኑ፡ የዚህ የሎዶቅያ ዘመን የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ጭምር።

153 ኸረ፡ የቀድሞ አባቶች ወደነበራቸው ነገሮች ለምን አትመለሱም? ክርስቶስን ወደ እኛ ወደሚያመጣ፡ በመንፈስ ቅዱስ ወደሚቀድሰና ወደሚሞላን እውነተኛ ጴንጤቆስጤ ለምን አንመለሰም? የምንፈልገው ያ ነው። እሺ። አሁንም፡ ዛሬም ያው ነው!

154 አሁን፡ **ጴርጋሞን** የሚለው ቃል “ያገባች” ማለት ነው። **ጴርጋሞን** የሚለው ቃል ራሱ ትርጉሙ “ያገባች።” የኒቆላውያን ወገን፡ የሆነው ክርስትና፡ መደበኛው ወገን፡ ከመንግሥት ጋር፡ ከአረማዊ ገድላት ጋር ተጋባ። የአረማውያን ገድላት! በዚያ ጊዜ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ልደት ያኔ ነበር።

155 አሁን፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኒቂያ ጉባኤ እንደተፈጠረች ማንም ያውቃል። ከዚያ በፊት፡ በእግዚአብሔር **ኒቆላውያን** ይባሉ ነበር፡ ትርጉሙም “ኒቃኡ፡” **ኒቃኡ**፡ “መውረር፡” አማኞችን ማሸነፍ፡ መጣል ማለት ነው። ያን ባደረጉ ጊዜ፡ መንፈሱ በሕዝቡ መካከል እንዲሁም ደግሞ፡ **በፓስተሮች**፡ ትርጉሙም “እረኞች” መካከል እንዲሆን አልፈለጉም፡ መንፈስ ቅዱስን ለመከልከል...

156 እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንዴት፡ ካህን እረኛ መሆን አይችልምን? ” የሚመግባችሁ ምግብ ምን አይነት ምግብ ነው? በጴንጤቆስጤ ቀን እንደነበራቸው፡ ተመሳሳይ ፍሬ አላችሁን? በእርግጠኝነት አይደለም! “ሰላም ለኪ ማርያም፡” በጰንጠቆስጤ ቀን ያየ ማን ነው? ጸሎተ ኑዛዜ፡ ሶስት አማልክትን በመጥራት፡ ማፍሰስ፡ እና ይህ ሁሉ ዓይነት መረጨት (“አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ”)፡ በጴንጤቆስጤ ቀን የት ነበር? ኢየሱስም፡ “የእስራኤል ቤት በእውነት ይወቅ፡ እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም፡ አድርጎታል።” ትክክል። እነዚያን ነገሮች ከየት አገኘናቸው? ከጅምሩ ጀምሮ ከካቶሊካዊነት የተቋቋመ፡ የኒቆላውያን ነገር ነው።

157 አሁንም እናንተ ደግሞ “ኧረ፡ እኔስ ከነሱ መካከል ባለመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡” ትላላችሁ። እንግዲህ በጣም እርግጠኛ አትሁኑ። አያችሁ? አሁን አስታውሱ፡ ክርስትና፡ ኒቆላውያን። አሁንስ ታሪኩን ተረድታችሁታል? ወደ ፊት ከመቀጠላችን በፊት በደንብ አዳምጡ። እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ እዚህ ብንቆይም እንድትረዱት እፈልጋለሁ። ስለዚህ፡ ኧረ-ህህ... ስለዚህ፡ ወ... ወንድሜ ሆይ፡ ነፍስህ ናት! “እኔ፡ የእከሌ ነኝ... ” እንደምትለው አይደለም፡ ያ አይደለም—አይደለም። ወንድሜ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስን ከሌለህ፡ ስንት ቤተ ክርስቲያን እንዳለህ አይገደኝም፡ ጠፍተሃል። በእግዚአብሔር መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ ጠፍታችኋል፡ ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት አላገኛችሁም፡ እግዚአብሔር በትንሣኤ የሚያነሣው ብቸኛው ነገር የዘለአለም ህይወትን ነው፡ ምክንያቱ የሚቀረው ብቸኛው ህይወት እሱ ነው።

158 የበቆሎ እህል... ስለ ግብርና ሰዓታት፡ እዚህ ተቅሼዋለሁ። በሄንሪቪል የሜቶዲስት ሰባኪ የነበረውን አንጋፋው ወንድም ሰፐርጅንን፡ የምታስታውሱት ስንቶች ናችሁ? ባለ ድንቅ አንጋፋው ባህርይ። በሬድ ፈርኒሽ ጋር፡ በአይስክሬም ፋውንቴን፡ ላይ አንድ ቀን አይስክሬም እየበላን ነበር፡ እና እዚያ ስላደረግኩት ስብሰባ እየተነጋገርን ነበር፡ እና ሰዓቱ የግብርና ወቅት ነበር። እና ሬድ—እዚያ ጋር ካለው፡ ከተቀመጠው ሬድዮ ላይ... ትንሿን ስፒከር ከፍቷታል። እና ከሆነ አገር ይናገራሉ... በእርግጥ መልእክቱ የሚለቀቀው ከሉዊስቪል ነው። እና የ 4-H ክለብ—ወደ ሰብሉ ካልሺየም እና ፔትሮሊየም እንዲሁም ሌላ ሌላ ነገሮች ጨምረህበት፡ ወደ ቦቆሎ ሰብል የሚለውጥ ማሽን፡ እናም ልክ እንደተሰራ የሚመስል፡ የሚያደርገው ማሽን ሰሩ...

159 በቆሎውን እውነት እስኪያስመስለው ድረስ፡ 4-H ደርሶበታል ተዘርቶ ከበቀለው እህል፡ እና በማሽን ከተሰራውም ከሁለቱ እፍኝ ብትወስዱ፡ ይሄኛው (በማሽን የተሰራው) አንድ አይነት ኮርን ፍሌክስ፡ ወይም የበቆሎ ቂጣ ይወጣበታል። እና በእውነቱ ሁለቱ ስብሎች፡ ወደ ላቦራቶሪ ወስዳችሁ ለሁለት ብትከፍሏቸው፡ አንዱን ከሌላው መለየት አትችሉም። ተመሳሳይ የፔትሮሊየም መጠን፡ ተመሳሳይ—ተመሳሳይ የካልሲየም መጠን፡ እና—እና እርጥበት፡ በአንድ እህል ውስጥ ሊገኝ የሚገባው ነገር ሁሉ፡ በሌላኛውም ነበረ።

160 እንዲህ አለ፡ "የትኛው በማሳ የበቀለ የትኛውም በማሽን እንደበቀለ፡ የምታውቁበት ብቸናው መንገድ፡ ሁለቱም ቅበሯቸው። ሁለቱም ይበስብሳሉ፡ በማሽን የተሰራው እንደገና አይነሳም፡ እግዚአብሔር ያደረገው ግን፡ እንደገና ሕያው ይሆናል።" ለምን? የበቀለ ስላልሆነ ነው።

161 እናንተም እንደ ክርስቲያን ልትመስሉ፡ እንደ ክርስቲያን ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ ማድረግ የሚቻላችሁን መልካም ስራ ሁሉ ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ ለቤተ ክርስቲያናችሁ ታማኞች መሆን ትችላላችሁ፡ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ሕይወት፡ የዘለአለም ህይወት ከሆነውን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፡ ካልተዘራችሁ በቀር፡ በመናዘዝ ሳይሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ **ስጦታ** ካልሆነ በቀር አትበቅሉም። እንዴት ታገኙታላችሁ? ሐኪሙ የተናገረው፡ የመድኃኒቱን ማዘዣ የጻፈው፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ነበረ፡ "ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፡ እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው። እግዚአብሔር የሚያነሣው ያ ብቻ ነው። ሊበቅል የሚችለው ሕይወት ያለው ነገር ብቻ ነው። አያችሁ? መሆን የሚችለው ብቸኛው ያ ነው። ግልጽ ይመስለኛል። እግዚአብሔር ይግለጽላችሁ።

162 እንግዲህ፡ ኒቆላውያን በዚያን ጊዜ መደበኛው ወገን ነበራቸው፡ ስለዚህ ከአረማዊው ቤተ ክርስቲያን ጋር ተጋቡ፡ የአረማውያን መሠዊያዎች በማምጣት፡ የክርስቲያን መሠዊያዎች ማድረግ፡ የአረማውያን አማልክት በማምጣት፡ የሚናገር እና የሚመልስ፡ ቢሾፕ በምሳሌው አሰቀመጡ። ቁጭ ያደርጉታል፡ አማልክት እንዲመስል መጎናጸፊያ ልብስ ያለብሱታል። አያችሁ? ከውጪ ያለው ሳይሆን፡ ከውስጥ ያለው ነው። ሁለቱ የበቆሎ እህሎችም ይመሳሰላሉ፡ በውጪ ያለው ሳይሆን፡ ከውስጥ ያለው ነበር። ውስጠኛው፡ አያችሁ፡ ህይወት። ስለዚህ፡ የተሰራው በዚያ ነበረ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ልደትም በዚያ ነበረ፡ እሷም የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተቋሞች እናት ነበረች።

163 እናንተም እንዲህ ትሉ ይሆናል፦ "እንዴ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ... ካቶሊክ ስላይደለሁ ትላላችሁ።"

164 አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ በነገራችን ላይ፡ አንድ ለአፍታ ያህል እዚህ እናቁመው። እና ሁላችንም—አሁን ወደ ራዕይ፡ ምዕራፍ 17 እንሂድ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። በቀጥታ ወደዚያ እንለፍ። አሁን፡ ይህ የማን መገለጥ ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለአብያተ ክርስቲያናቱ። እኔ እነባለሁ፡ እናንተም በደንብ ስሙ፡

> **ሰባቱንም ጽዋ ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፡ ተናገረኝ፡ ወደዚህ ና...** እለኝም፡ **በብዙ ውኆች ላይ** የተቀመጠችው **የታላቂቱ ጋለሞታ ፍርድ... አሳይሃለሁ አለኝ፡**

165 እስኪ፡ ለምስክር እንዲሆነኝ፡ **ሴት** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እንደ ምሳሌ በተጠቀሰች ቁጥር፡ “ቤተ ክርስቲያን” ማለት እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? እሺ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰ ይህች ታላቂቱ “ጋለሞታ፡” “በሰባት ተራሮች ላይ የተቀመጠች ከተማ፡” እንደሆነች ስንቶች ታውቃላችሁ? እሺ።

166 መጽሐፍ ቅዱስ “ውኆች” ማለቱን ስንቶች ታውቃላችሁ? እሷ የተቀመጠችባቸው “ብዙ ውኆች” ናቸው፡ “ውኆች” እንጂ **ውኃ** አይልም። **ውኆች** ማለት “ህዝብ” ማለት ነው። ምክንያቱ፡ 15ኛው ምዕራፍ ውሰዱ፡ 15ኛው ቁጥር፡ እዩት፡ ማየት ትችላላችሁ፡ አያችሁ፡

> **እንዲህም** አለኝ፡ **ያየሃቸው፡ ውኃዎችም፡** ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው፡ ህዝብ፡... ወገኖችና፡... አሕዛብም፡ ቋንቋዎችም ናቸው። (አያችሁ? አያችሁ? )

167 አሁን፡ ሴቲቱም ከሃዲ ነበረች። አይደለችም ወይ? እንግዲህ ይህ ትምህርት ነው፡ ሕሊናችሁን ገለል አርጉት አሁን። አያችሁ? “ጋለሞታ” የተባለች ያቺ ወራዳ ሴት ምንድናት? ለጋብቻዋ ለቃል ኪዳኗ ያልታመነች ሴት ነች። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያኒቱ፡ ማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ የክርስቶስ ሙሽራ እና ሚስቱ እኔ ነኝ ትላለች። መነኮሳቶቻቸው ሳይቀር ጸጉራቸውን እየቆረጡ፡ ሰጋዊ ፍቅራቸው ይጠፋል፡ “ፍቅራቸው ሁሉ ለክርስቶስ ነው።” ልክ ነው? አዎን። ወይም ማንም ይምጣ...

168 እኔም የመጣሁበት የካቶሊክ ዳራ አለብኝ፡ አያችሁ። **የእምነታችንን እውነታዎች** የሚለውን እና ሌላ መጽሐፍቶቻቸውም አለኝ፡ የእናንተም የፕሮቴስታንቶች፡ እና ባፕቲስቶች፡ እናንተ የምታምኑት ሁሉ፡ በጥናቴ ላይ ይዤዋለሁ። ስለዚህ ማንም ሰው መጥቶ አንድ ነገር ቢናገር፡ **ውውውፕ** ቢል፡ ወደ ራሳችሁ አባባል ላስገባችሁ እችላለሁ። አያችሁ? ስለዚህ፡ ይህ ሁሉ የሚወገድበት ጊዜ አሁን መጥተዋል።

169 እንግዲህ፡ ከሁሉ በፊት፡ ህዝብ ሁሉ ይህን ያውቁት ዘንድ፡ እግዚአብሔር ምልክቶችን፡ ድንቆችን፡ እና ተአምራትን እያሳየ፡ በሀገሪቱ ውስጥ መንቀሳቀስ ነበረበት። የእግዚአብሔር በጎች ድምፁን ያውቃሉ፡ ያውቃሉ፡ በትክክል ያውቃሉ። ከሁሉ በፊት ያን ማወቅ አለባችሁ... ሳታውቁት ስትወጡ፡ ያኔ እንደው... ምን ታደርጋላችሁ? ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጥፋት ታደርጋላችሁ። ተውለት... እግዚአብሔር እንዲሰራው ተውለት። አያችሁ?

170 “የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ።” እንግዲህ፡ እሷ እንዲህ ከነበረች፡ ያልሆነችውን ለማለት የምትሞክር ሴት... ምንዝር ትሰራ ነበር! ልክ ነው? ይሁን፡ እንግዲህ፡ ቤተ ክርስቲያን ከነበረች፡ በእግዚአብሔር ላይ የምታመነዝር ነበረች። ልክ ነው? ስለዚህ ይህ ዝሙት፡ **መንፈሳዊ** ዝሙት፡ ምንዝርና ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል ያልሆነ ነገር ለሰዎች ታስተምራለች። ልክ ነው? እውነት ያልሆነ ነገር እያስተማረች ነው። ኒቆላዊነት ይህ ነው። እዚህ ሲገባ ተመልከቱት? መንፈስ ቅዱስን ወደ ጎን በመተው፡ ካህናትን፡ እና ጳጳሳትን ይሾማል፡ “የተአምራት ዘመን አልፈዋል”፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ለዘላለም ያው ነው፡” ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ “ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

ተጠመቁ፡” ይለናል፡ እሷ ግን፡ በመረጨት፡ እና በማፍሰስ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡” ነው ትላለች። ኦህ፡ ማይ! አያችሁ?

171 እሺ፡ ሴቲቱ ያደረገችውን ነገር ተመልከቱ፡

> ... **የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር** ሴሰኑት፡ **በምድርም የሚኖሩ...** ከዝሙትዋ **ወይን ጠጅ ሰከሩ።**

172 “ሰከሩ!” ወንድሜ፡ ይገድሉሃል፡ ወደ ሞት ይነዱሃል፡ ይተኩሱብሃል፡ ብዙ ነገር ያደርጉብሃል። በዛ ነገር ላይ በፍፁም ሰክረዋል። አያችሁ?

173 “ወይን።” የዝሙትዋን ወይን እየሰጠች ያለችው፡ አየህ፡ ይህንን ነው። “አንድ ነገር ልንገራችሁ! እናቴ ካቶሊክ ነበረች፡ እና... ” እሺ።

174 “ከባድ ነገር ነው፡” ትላልችሁ። ቆይ እናንተ ፕሮቴስታንት ሆይ፡ ተረጋጉ እስኪ። ኧሃ! (እየተናገርኩ ያለሁት በቴፕ ለሚያዳምጡ ነው፡ እሺ።)

> **በመንፈስም ወደ በረሃ ወሰደኝ፡ እኔም ይህንን እየሁ—— እንዲት ሴት በቀይ አውሬ ላይ** ተቀምጣ **አየሁ፡...**

175 አሁን፡ **ቀይ** የሚለው ቃል ምን ለይቶ ያሳያል? “ንግስና” ያሳያል። ማለት... አባባሌ፡ አባባሌ፡ “ንግስት፡ ንግስት፡ ንግስት፡” አያችሁ፡ ልክ እንደ ነገሥታት ዓይነት።

> **... የስድብ ስም የሞላባቸው፡ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት።**

176 አሁን፡ ሰባቱ **ራሶች** ከተማይቱ የተቀመጠችባቸው ሰባቱ “ተራሮች” ናቸው። ከተማይቱም ሴቲቱ ራሷ እንደውሆነች፡ አውቀናል።

> **ሴቲቱም በሐማራዊ ልብሰ ተጎናጽፋ ነበር...**

177 “ሴቲቱ።” አውሬውም **ቀይ** ነበረ፡ ሴቲቱ ግን **ሐምራዊ** ልብሰ ተጎናጽፋ ነበር። አሁን፡ ባለፈው ጊዜ፡ ሶስት ዓይነት መጋረጃዎች አሉ ብዬ አላስጠነቀቅኳችሁምን? እኔ ለምን ያህል ጊዜ እንደምኖር አላውቅም፡ ነገር ግን ይህን እንዳትረሱ። ከብዙ አመታት በፊት እንደነገርኳችሁ፡ “ሩሲያን ጠብቋት።” ሶስት መጋረጃዎች አሉ፡ ይህን አስታውሱ። **የብረት** መጋረጃ አለ። **የቀርከሃ** መጋረጃ (ቀይ ቻይና እና **የመሳሰሉት**) አለ። እና ሐምራዊው መጋረጃም አለ፡ ያንን መጋረጃ ጠብቁት፡ አታላይዋ እሷ ናት። እጅግ በጣም...

> **... ሴቲቱ ሐምራዊ ልብሰ ተጎናጽፋ ነበር... ቀይ** ቀለሞች፡... **በወርቅ... በከበሩ ድንጋዮች እና ዕንቁዎች ያጌጠች፡** (የመጀመሪያው የኒቆላውያን መሠዊያ ምን እንደነበረ እዚህ የተናገርኩትን ነገር ታስታውሳላችሁ? አያችሁ? **ሴት** “ቤተ ክርስቲያን” ነች።) **በእጇ የወርቅ ጽዋ ያዘች** (አስታወሳችሁት? በወርቅ የተለበጠው መሰዊያ፡ ለህዝቡ ጽዋውን ትሰጣችኋለች።) **የሚያስጸይፍ** የዝሙትዋም ርኩሰት **የተሞላ** ነው፡

178 ለሰዎች የምትሰጠው ይህ ነው፡ እነርሱም ይለጉት ነበር። በትክክል። በዚያም ይሰክሩበታል! ሰክረዋል! ያ ሁሉ አይሪሽ፡ እና ፈረንሳይ፡ እና ሌሎች በሙሉ፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ አንድ ነገር ትንፍሽ ብትል ጉሮሮህን ይቆርጡሃል። በትክክል፡ ያደርጉታል። አያችሁ?

**በግምባሯም የተጻፈ ስም፡ ምስጢረ፡ ባቢሎን የሚል ስም ተጽፎ ነበር…**

179 አሁን፡ ባቢሎን ከየት መጣች? ከባቢሎን ወደ ጴርጋሞስ፡ መጣች እና… ሰይጣን ዙፋኑን አዞረው። አቤት፡ ይህን ሁሉ ማየት እንድትችሉ፡ ራእይ መጽሐፍን በሙሉ ብንፈትሸው ምኞቴ ነው።

**… ታላቂቱ ባቢሎን፡ የጋለሞታዎች እናት…** የ**ጋለሞታዎችና የምድር እርኵሰት እናት።**

180 ምን ነበረች? የጋለሞታ እናት። ወንዶች ልጆች አይደሉም። ናቸውን?

181 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]… ቤተክርስቲያናቸው። አዎን፡ ወዳጄ። እና፡ "ቤተክርስቲያን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ 'ባቢሎን' አልተባለችምን? " በራሳቸው መጽሐፍ ውስጥ፡ ተመልከቱ። እሺ።

182 እንግዲህ፡ እሷ አመንዝራ፡ ጋለሞታ፡ እና የጋለሞታዎች እናት ከሆነች፡ ሴቶች ልጆች ወልዳለች። እንግዲያውስ ሴት ልጆቿ ከተባሉ፡ ሴቶች ነበሩ፡ ማለት አብያተ ክርስትያናት ነበሩ። እስኪ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ከየት መጣች? ልክ ነው? በጋለሞታ እና በጋለሞታዎች—መካከል ምን ልዩነት አለ? አንድ ነው።

183 ማርቲን ሉተር ወጣ፡ ለውጥ ለማምጣት፡ ለእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን እድል ለመስጠት፡ ዌስሊም፡ በጴንጤቆስጤ ላይ፡ ኋላ ግን ወደ ኒቆላውያን ድርጅታዊ አስተሳሰብ ወደ ኋላ ተመለሱ፡ የበላይ አስተዳደር፡ እና ሌላ ሌላ ነገር በመሾም፡ አስቀድመው በተጠመቁት ያንኑ ጥምቀት ወደ ኋላቸው ተመለሱ፡ ብበተመሳሳይ ስሌት፡ ተመሳሳይ ገድላት፡ አብዛኞቹ ካቴኪዝም እና '**ሰላም ለኪ ማርያም**' ሳይቀር ተቀብለዋል። **ሰላም ለኪ ማርያም፡** ሳይሆን… ይህ እሱን መሳይ ነገር ምንድነው? ያ **የሐዋርያት ሃይማኖት መግለጫ።** ወንድሜ፡ የሐዋርያትን ሃይማኖት መግለጫ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስኪ አሳየኝ። የ—የሃይማኖት መግለጫ ቢኖራቸው፡ የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ነው፡ ይህም ሁሉም እንዲፈጽሙት የታዘዘ ነው። አንድ ሐዋርያ፡ የሃይማኖት መግለጫ ሲያነበንብ ከወዴት ሰማችሁ፡ "በቅድስት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ። በቅዱሳን ተራዳኢነት አምናለሁ።"?

184 ያኔ… መክፈቻዎቹን የያዘ፡ ጴጥሮስ፡ ሲናገር፡ "ከክርስቶስ ኢየሱስ በቀር፡ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሌላ አስታራቂ የለም።"

185 የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ግን እዩአቸው። ምን አደረጉ? ሊረኩ አልቻሉም። የወጡት ሁሉ ሲወጡ፡ የጴንጤቆስጤ በረከት ይዘው ወጡ። በትክክል እውነት ነው። ማርቲን ሉተር እንኳ በልሳኖች ተናግሯል። በትክክል እውነት ነው። እሱ ራሱ፡ ስለራሱ "እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህ እኔ የምናገራቸው ተብታባ ቃላት፡ ምን እያልኩ እንደሆነ አላውቅም፡" በማለት ተናገረ። አያችሁ? አዎን፡ በልሳን ያምናል። በትክክል፡ ያምናል።

186 እንግዲህ፡ በእነዚያ ሁሉ ዘመናት—መነፈስ ነበራቸው፡ ነገር ግን የመጀመሪያው እንቅስቃሴ መስራች ከሞተ በኋላ ግን ሁልጊዜ ድርጅትን ወደ ማደራጀት ይመለሳሉ። የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሳትደራጅ ብታስቀጥሏት፡ እና ባታደራጇት ኖሮ፡ ጴንጤቆስጣል ትሆን ነበር። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን

ምንድን ነው? እውነተኛውን ጴንጤቆስጤ ማለቴ ነው። አሁን ተቋም የሆነው ማለቴ፡ አይደለም፡ አሁንማ በድጋሚ “ማሰሮ እና ጀበና” ሆኗል። አያችሁ? ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል፡ ይህም በመጀመሪያ እንዳደረጉት በቀጥታ ወደ ኒቆላዊነት እንዲመለሱ አድርጓቸዋል። ሰንቶች ገብቷችኋል? “እሜን” በሉ። [ጉባኤው “አሜን!” አለ፡—አርታዒ።] በትክክል። እንደው፡ እየገባችሁ እንዳለ ለማወቅ ያክል ነው...

187 አያችሁ፡ የ “ሴተኛ አዳሪዎች” እናት። ሴተኛ አዳሪዎች ከሆኑ፡ እንዴት ሴተኛ አዳሪዎች ሆኑ? በእግዚአብሔር ቃል ላይ ዝሙት በመፈጸም። የእግዚአብሔር ቃል፡ “ንስሓ ግቡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ” ካለ፡ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የኢየሱስ ስም ጥምቀት ተጠምቀዋል፡ አንተ ግን “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ” ተጠመቅክ። ሴተኛ አዳሪነት ይህ ነው! ልክ ነው? መጽሐፍ ቅዱስም መጠመቅ (በግሪክ ቃል፡ **ባፕቲዞ**) በመጥለቅ ከሆነ፡ ታድያ አንተ እንዴት ትረጫለህ እንዴትስ ታፈሳለህ? ያ መቼ እና የት መጣ? በመንፈስ ቅዱስ ምትክ በእጅ መጨባበጥ፡ ወይም ዋፈር በመቀበል፡ ወይም እንደዚያ ያለ ልዩ ነገር ተቀብላችሁ፡ በመዋጥ ከለወጣችሁት፡ መንፈስ ቅዱስም እንደ ብርቱ ኃይለኛ ነፋስ ከሰማይ መጥቶ ሕዝቡን ሞልቶ፡ በልሳኖች እንዲናገሩና፡ እንዲጮሁም፡ እንደ ሰካራም እንዲሆኑ አድርጓቸው ሳለ፡ እናንተ ግን እጅ በመጨባበጥ፡ ወይም ቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ደብዳቤን በማስቀመጥ፡ ወይም በመሳሰሉ ነገሮች ከለወጣችሁት፡ መንፈሳዊ ዝሙት ከምትፈጽሙበት መንገድ እንዴት ታመልጣላችሁ?

188 እንግዲህ፡ ወንድሞች ሆይ እራሳችሁን ጠይቁ። አእምሮአችሁን ዝቅ አርጉ፡ ልባችሁን ክፈቱ፡ እና ቅኖች ሁኑ። በመንገዱ መጨረሻ ላይ ደርሰናል። እነዚህ ጉባኤዎች በከንቱ የተቀመጡ አይደሉም፡ በእግዚአብሔር የታዘዙ ናቸው። እጅግ እርግጠኛ ነው ብዬ አምናለሁ... የእርሱ አገልጋይ እንደ ሆንሁ ታምናላችሁ። እኔ ወደዚህ እንድመጣ እግዚአብሔር በልቤ ላይ እንዳደረገው፡ በኢየሱስ ስም እናገራለሁ። ይህን ለማድረግ አንድ ሳንቲም አይከፈለኝም። ምናልባት እኮ ለታመመ ሰው በመጸለይ፡ የሆነ ቦታ ላይ መቆየት እ—እ—እ—እ—እችላለሁ። ወይም ወደዚያው ወጥቼ ዓሣ በማጥመድ፡ ከቤተ ክርስቲያን እንደማገኘው ክፍያ፡ ገንዘቤን ማግኘት እችላለሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር በልቤ ላይ አስቀመጠው፡ ከዚ መራቅ አልችልም፡ በውስጤ ላይ እጅግ ይጮኻል፡ እኔም የቻልኩትን ያህል እያደረግኩ ነው። የቻልኩትን ያህል እያደረግኩ፡ እነሆ በጌታ ፊት ቆሜአለሁ። እንዲያልፋችሁ አትፍቀዱ።

189 አሁን፡ እናንተ ፕሮቴስታንቶች ሆይ፡ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ስለ ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባችኋልን? እንደው... አንደኛው እንደሌላው ተመሳሳይ ነው። በትክክል እውነት ነው።

190 እንግዲህ፡ ያገባች ማለት ነው፡ **ጴርጋሞን** “ያገባች” ማለት ነው።

191 አሁንም እንቀጥል... እንዲህ አለ፡ “በአንተ መካከል የበለዓም ትምህርት የያዙ አሉህ።” እስኪ ይሄን እንውሰድ።

192 ጊዜ አለን? የቻልኩትን ያህል እፈጥናለሁ። ወይንስ በጠዋት ተመልሰን መጥተን ብናይ ይሻላችኋል? ትንሽ እንቀጥል የምትሉስ፡ ሰንቶች አላችሁ? እ... እሺ፡ አሁን፡ እዚህ እንደሚሞቅ አ—አውቃለሁ። እንግዲህ እናንተ አርፋችሁ

ተቀምጣችሁ ከሞቃችሁ፡ እዚህ ምን እንደሚሆን አስባችሁታል? አያችሁ? ግን፡ ኦህ፡ ማይ፡ ከዚያ እጅግ የሚያቃጥል ሙቀት ለማምለጥ እየሞከርን **ነው**። አያችሁ፡ ነገሩ—ያ ነው፡ ምክንያቱ፡ ዘላለማዊያን ነንና።

193 አሁን፡ ያኔ እንደዛ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ሲያቋቁሙ፡ ምን ተፈጠረ? ልጆቼ ሆይ፡ አሁን በጥሞና አድምጡኝ። ምን ተፈጠረ? እንዴታ፡ እርግጥ ነው፡ መንፈስ ቅዱስን ከቤተ ክርስቲያን አራቀ። ከቢሾፖቻቸው ሁሉ አንዱስ እንኳ ሙታን ማስነሣት ወይም አንድም ተአምር አለማድረጉ በእውነትም አይገርምም። ስለ ቅዱሳን አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ በመካከላቸው እንዳሉ ያወራሉ! ስራቸውን ይቃወሙታል፡ እነርሱን ግን የእኛ ናቸው ይሏቸዋል!

194 ያቺን ወጣት ልጅ፡ ጆአን ኦፍ አርክን ተመልከቱ። እናንተ ካቶሊኮች፡ ወይም ፕሮቴስታንቶች፡ ማንኛችሁንም እጠይቃችኋለሁ። ጆአን ኦፍ አርክ፡ በዘመኗ፡ ቅዱሳንን ካጨናነቀችው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቀር፡ በፈረንሳይ ውስጥ ምንም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ያችን ልጅ አነሣት መንፈስ ቅዱስም ነበራት። ምን አደረገች? ትንቢት ትናገራለች፡ ጌታ ራዕዮችን ሲያሳያት ትንቢትን ትናገራለች። ለታመሙት ጸለየች። ለሞተች ትንሽ ሕፃን ጸለየች፡ ሕጻኗም እንደገና ወደ ሕይወት ተመልሳለች። ጴንጤቆስጤ ማለት ይህ ነው። አያችሁ? እና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመቃወሟ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ምን አደረገቻት? ችሎት ብለው ጠሩዋት፡ እንደ "ጠንቋይ" እንጨት ላይ አቃጠሉዋት።

195 አሁን ግን "**ቅድስት** ጆአን ኦፍ አርክ፡" ትሏታላችሁ። ከሁለት መቶ ዓመታት፡ በኋላ፡ እሷ ቅድስት እንደነበረች፡ ቤተ ክርስቲያንም የፈጸመችው ነገር ከተገነዘበች በኋላ፡ ኦህ፡ ለሞት አሳልፈው የሰጧት እነዚያ ካህናት፡ አጽሟን ቆፍረው አወጡ፡ ወደ ወንዙ ጣሉት፡ እውነት ነው ንስሓ ገብተዋል። ያ ግን ደሟን ከእጃቸው የሚያጥብ ይመስላችኋልን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "የ—የቅዱሳን ደም ሁሉ ተገኘባት።" የእግዚአብሔር መልአክ በባቢሎን ተገኘ ብሎ የተናገረው ያ ነው። "ግድያ ሁሉ፡ ወይም ሰማዕትነት ሁሉ፡ በሰማዕትነት የተገደሉ የክርስቶስ የቅዱሳን ደም ሁሉ፡ ከኒቆላውያን ዘመን ጀምሮ የተገደለ የእያንዳንዱ ሰማዕት፡ በሷ ውስጥ ተገኝቷል።" አሰቡት እስኪ። (አመሰግናለሁ፡ ወንድም ቤን።) አሁን፡ እስኪ አስቡት።

196 አሁን፡ ትንሽ ገፋ እንድርግ። የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ከ—ከ ባ... ባቢሎን ጋር ተጋባች። **ጴርጋሞን** ማለት "ጋብቻ" ነው።

197 ስለዚህ፡ "የበለዓም ትምህርት። በእናንተ መካከል የበለዓም ትምህርት የያዙ አሉ።"

198 ኦህ፡ እነዚህን ነገሮች ደስ ይሉኛል። አቤት፡ እንደው ትንሽ ጊዜ መቆየት በቻላችሁልኝ፡ አያችሁ፡ ግን... ይሄን እንድታዩት እና ወደ ሌላ ነገር እንድናልፍ እንፈልጋለን፡ ምክንያቱ ውስጡ በ—በወርቃማ ዕንቆች የተሞላ ነው። እኔ የከበሩ ድንጋዮች አሳሽ ነኝ፡ ወደ ታች ቆፍሬ የሚያበሩ ዕንቆቹን አውጥቼ፡ እንዲህ ወልውዬአቸው፡ እንዳያቸው እወዳለሁ። እያንዳንዳቸውም ኢየሱስ ክርስቶስን ያንጸባርቃሉ! አያችሁ፡ እያንዳንዳቸው። እያንዳንዳቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ያንጸባርቃሉ። አልፋ እና ኦሜጋ ነው፡ በዕንቁ ውስጥ ያለውን የወርቁን—

እያንዳንዱ ካራት እርሱ ነው። በትክክል። አንዲት ሳትቀር እሱ ራሱ ነው። እሱ አምላክ በመካከላችን ሰጋ ሆነ የሆነው፡ ምክንያቱ ይህ ነው።

199 ስለዚህ፡ ይህን ለማግኘት... ለዚህ—ጊዜ አላጠፋም፡ ምክንያቱ... ዘጠኝ ሰዓት መሆኑን አይቻለሁ። እና እ—እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ዛሬ ማታ ልገባበት የምፈልገው ሌላ ነገር ይዣለሁ። እና አሁን ጽፋችሁ ይዙ እና ነገ እንድታነቡት እፈልጋችኋለሁ፡ ስለዚህ ዘኅልቍ ከ 22 እስከ 25 ድረስ ያዙ። አሁን እንድታነቡት እፈልጋለሁ፡ እኔን ከእኔ በኋላ ልትከታተሉኝ ትችላላችሁ። እና አሁን—አሁን ዘኅልቍ 22 እስከ 25።

200 እስራኤል—እስራኤል የእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ እንደነበረ እናውቃለን። ልክ ነው? ነበሩ... ጴንጤቆጤዎች ነበሩ። መንፈሱ በመካከላቸው ነበረ። የትናንት ምሽት መልእክት ታስታውሱታላችሁ? ያ ሙሴ ከደሙ፡ ደሙን የሚወክል የቀይ ባህርን፡ ወይም የሙትን ባህርን ተሻግሮ፡ በቀይ ባህር፡ ከኋላው ከሆነ በኋላ... እርሱንና ያሰጨነቁት አሰጨናቂዎች የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ነበሩ። ሙሴ እጁን ወደ ላይ ዘርግቶ በመንፈስ ዘመረ። እነሆ፡ እያንዳንዳችን ሙሴ መሆን እንችላለን ወደ ጌታ ኢየሱስ ቀይ ደም ወደ ኋላ መለስ ብለን እያንዳንዱ ሰካር፡ እያንዳንዷ ጠርሙስ፡ እያንዳንዳቸው አጉል ሴቶች፡ በሕይወታችን ያሳለፍናቸው እያንዳንዱ ቆሻሻ ድርጊቶቻችን ሰናየው፡ ሁሉም በጌታ በኢየሱስ ደም ውስጥ ሞተዋል። ይህም በመንፈስ እንድንዘምር ያደርገናል! ሲጋራዎች፡ ትምባሆዎች፡ አጉል ልምዶች፡ እና ሌላ ነገር በሙሉ፡ በጌታ በኢየሱስ ደም ውስጥ ሞተዋል፡ ስለዚህ እጆቻችን ወደላይ አንስተን በመንፈስ መዘመር እንችላለን። አያችሁ?

201 ነቢይቱ ማርያም፡ ያደረገችውን ተመልከቱ። እሷ፡ ነቢይት እንደነበረች፡ አስታውሱ። ከበሮ ያዘችና ከበሮ እየመታች በመንፈስ መዝለል ጀመረች፡ የእስራኤልም ሴቶች ልጆችም ከበሮአቸውን እየመቱ፡ በመንፈስ እየዘለሉም ወደ ባህር ዳርቻው ተከትለዋት መጡ። እውነተኛው ጴንጤቆስጤ!

202 ከዚያም በኋላ ካስተዋላችሁ ወደ ሞዓብ መጡ። አሁን እየተመለስን ነው... አሁን ያለነው፡ መጽሀፍ ቅዱስ ላይ፡ በ "በለዓም ትምህርት" ላይ ነን። ሞዓብም፡ ሞዓብ ለእስራኤል ወንድሙ ነበረ። ሞዓብ ከየት እንደመጣ ስንቶች ታውቃላችሁ? እሺ። ሞዓብን ዲቃላ ብዬ እጠራዋለሁ፡ ምክንያቱም ሞዓብ የተወለደው ከሎጥ ሴት ልጆች ነው። ሎጥ ከገዛ ሴቶች ልጆቹ፡ ሁለት ልጆች ወለደ። ከእነርሱም አንዱ ሞዓብ ነበረ፡ እርሱም የሞዓብ ነገድ፡ አገርን ሠራ። እና፡ በርግጥ፡ ሎጥ የአብርሃም የወንድም ልጅ ነበር፡ እርሱም አንድ ግንድ የተገኘ ነበረ። ይህን እናውቀዋለን። አንዳንድ በቅርቡ ተውኔቶቻችን እንደሚሰጧችሁ፡ እነሱ ጣዖት አምላኪ እንዳልነበሩ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ... አማኞች እንደነበሩ፡ አስታውሱ። እዚጋ፡ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር በመንገዳቸው በወጡ ጊዜ፡ በግዳጅ መንገዳቸውን እየገሰገሱ ሳሉ፡ እነሆ ሞዓብ በመንገዳቸው ላይ ተዘርግቶ ሰፍሮ ነበረ። ወደ ሞዓብም፡ መልክተኞችን ልከው "በምድርህ እንለፍ። እኛ ወንድምህ ነን፡" አሉት።

203 እንግዲህ፡ ሞዓብ ኒቆላውያንን ይወክላል። ከአፍታ በኋላ ትዩታላችሁ። እስራኤልም እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይወክላል። በልዓምም ከዋናዎቹ ቢሾፖች፡ ጳጳሶች መካከል አንዱ ነበረ። አሁን አስተውሉ፡ እና ሰጋዊ ክርስትናን

ተመከቱት። የጸጋ ስጦታ እንደነበረው እናስተውላለን፡ በዚያ ላይ ጥርጥር የለም። ብዙዎቹ ጥሩ ተናጋሪዎች፡ የፍልስፍና ዶክተሮች፡ እና—ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። ያንን መካድ አትችሉም። ነገር ግን፡ "የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል።"

204 ወደ መጀመሪያ ጰንጠቆስጤ ተመለሱ! ከዚያም አትራቁ። ከራቃችሁ፡ ጠፍታችኋል። በዚያ በረከት ቆዩ። ያ ነው፡ የባለበረከቱ በረከት ይህ ነው።

205 አሁን ጉዞ ላይ ሳሉ፡ አስተውሉ። ወደዚህ መደበኛ ዲቃላ ቤተ ክርስቲያን መጡ፡ እና እንዲህ አሉ፡ "በሪቫይቫል እያለፍን ነው። ወደ ተሰፋይቱ ምድር እንሄዳለን። እንድናልፍ ትፈቅድልናለህን? ከብቶቻችን ስለሚበሉት ሣር፡ ስለሚጠጡት ውሃ ሁሉ፡ እንከፍላለን።"

206 ከዚያ ምን አደረገ... ? ንጉሱ ባላቅ፡ በጣም ተነቃቃና፡ በቤተ ክርስቲያኑ ወይም በአገሩ ውስጥ እንደዚያ ያለ ጉባኤ እንዲሆን አልፈለገም። ታዲያ ምን አደረገ? መልዕክት ወደ ጳጳሱ፡ ወይም ወደ ቢሾፑ፡ ወደ በልዓም ላከ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብን የሚወድ፡ ቅጥረኛ ነቢይ ነበር። ንጉሡ ባላቅም "ወደዚህ መጥተህ ይህን ህዝብ ከረገምክልኝ፡ ታላቅ ሰው አደርግሃለሁ፡" አለው። እግዚአብሔርም ባላቅን ተናገረው። እና እንደዚህ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ-... በለዓም ማለቴ ነው። ዛሬ ማታ በዚህ ዓለም ውስጥ ስንት በልዓሞች ይኖራሉ? የሜቶዲስት አገልጋዮች፡ የባፕቲስት አገልጋዮች፡ የካቶሊክ ቄሶች፡ (አቤቱ ማረን!) ያ እግዚአብሔር ያውቀዋል... እኔ ያነበኩትን ታሪክ እና ተመሳሳይ መጽሐፍ ካነበባችሁ። "በልዓም!"

207 አሁን፡ አስተውሉ። ከዚያም እንዲህ አለ፡ "ውረድና ህዝቡን ርገምልኝ።"

በለዓምም "እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ፡" አለ።

እግዚአብሔር "አትሂድ!" አለው፡

208 በነጋታው፡ እንዲህ አለ... ሄዶ ለካህኑ፡ ወይም ለ—ንጉሡ ነገረው።

እሱም ተመልሶ መጥቶ፡ "እነሆ፡ እኔ—ታላቅ ሰው አደርግሃለሁ፡" አለው።

በለዓምም ቀጠለ። እግዚአብሔርም "ቀጥል እንግዲህ፡ ቀጥልበት፡" አለው።

209 እያችሁ፡ እውነትን መከተል ከፈለጋችሁ... ኒቆላውያን ሆይ፡ እናንተ፡ እንዲህ የምታደርጉትን እግዚአብሔር የሚሰራላችሁ ይመስላችኋልን... ኦሪጂናል እውነት አለ! የወሰዳችሁት የእግዚአብሔር የፈቃዱ ፈቃድ ብቻ ነው። "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰጥቶናል፡" ትላላችሁ፡ ደግሞም "እርሱ ባርኮናል፡ እንዲሁም 'በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ' ተጠምቀናል ትላላችሁ።" እናንተ በልዓማውያን! እዩት፡ የበለዓም ትምህርት ነው። እብሪተኝነት ካበዛ በኋላ፡ በገዛ ፈቃዱ እራሱን ለመስቀል፡ እግዚአብሔር ተናግሮ፡ ለቀቅ አደረገው። ወደ እውነት ወደ መሰረታዊው እውነት፡ መመለስ አለባችሁ። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱ። "ኦህ፡ እሱ'ማ፡ ባርኮናል! እና-... " አይ፡ ይሄ'ማ አውቀዋለሁ። በልዓምን፡ እንዲሁ፡ አላለውምን፡ "ቀጥል። መሄድ ከፈለግክ፡ በዚያ... መሄድ ወሰኛለሁ ካልክ፡ የድርጅት መንገድ መከተል ከፈልግክ፡ ሂድ፡ ውሰድ።"

210 ወዲያውም በልዓም ተነሣ፡ በቅሎው ላይ ወጣ፡ ማለቴ፡ በቅሎ ሳይሆን፡ አህያው ላይ ወጣና፡ መንገድ ጀመረ። የመጀመሪያው ነገር፡ ታውቃላችሁ፡ የጌታ መልአክ መንገድ ላይ በፊቱ ቆመ። እና፡ ታውቃላችሁ፡ ያ ነቢይ፡ ያ ጳጳስ፡ ቢሾፕ፡ ካርዲናል፡ ምንም በሉት፡ ለመንፈሳዊ ነገሮች በጣም ታወረ፡ በኤፍራጥስ ወንዝ ይኖር ስለነበር፡ ሹመት አገኛለሁ ብሎ አሰቦ ነበር። አንዳንድ ርስት ነገር እንዳሰበ እገምታለሁ፡ እንደ "'በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ ጴጥሮስ፡" ወይም ሮም ውስጥ በነበረ አንድ ድንጋይ ላይ፡ ወይም በሆነ ነገር አሰበ። ወደ ሰፍራው በደረሰ ጊዜ ግን፡ ሰይፉን መዘ የቆመ መልአክ ገጠመው፡ ይሁን እንጂ ማየት እስኪሳነው ድረስ ታውሮ ነበር። በቅሎውም እግሩን ከቅጥሩ ጋር አጣበቀው። አሁንም ግን ተቀምጦ ጋለበው፡ መልአኩም እንደገና—በመንገዱ ቆመ። እግዚአብሔር በሮችን ሁሉ ዘጋጋበት! አሁንም በቅሎው ዞሮ ተመለሰ። ዘሎ ወረደና፡ ዱላውን ያዘ በያዘውም ይመታው ጀመረ። ይህ ምስኪን አህያ፡ መንገድ ላይ ወድቆ፡ ጭንቅላቱን ተመታ።

211 እኔም፡ የቀየረው ምን እንደሆነ፡ እና ያንን አይነት ተግባር እንዲያደርግ ያስደርገው ነገር፡ በትክክል አውቀዋለሁ፡ በቅሎውን በልሳን እንዲናገር ስላደረገው ነው። በቅሎ አይደለም፡ አህያ ነበረ! "በቅሎ" ነበረ አትበሉ፡ ቢሆን'ማ አይገባውም ነበር፡ ዲቃላ ነውና። አያችሁ? ያ ኦሪጂናል ዘር ነው።

212 ሞዓብም፡ "ምልክቶች የሉም፡ የእንደዚያ ነገሮች ዘመን አልፏል" ባይ ነው። እስራኤል ግን ምልክቶች ይከተላቸው ነበር።

213 ምስኪኑ አህያ ግን ፊቱን አዙሮ እንዲህ አለ፦ "ሁሌ አህያህ አልነበርኩም ወይ? እንዲህ እርጌህ አውቃለሁን... " አይነ ሰውሩ ቢሾፕ ግን—አሁንም ላይዋ ላይ ሆኖ፡ አሁንም በቅሎዋን ይደበድባታል፡ በቅሎዋም በማይታወቅ፡ በቅሎውን ልሳን ማናገርዋን ቀጠለች።

እርሱም እንዲህ መለሰላት፦ "አዎን፡ አንቺ—አህያዬ ነሽ።"

"ከዚህ በፊት አልሸከምህም ብዬህ—አውቃለሁን፡ ወይስ አልታዘዝም ብዬሃለሁን? "

"አይ፡ አላልሽኝም። ይሁን እንጂ ዛሬ ሰይፍ ቢኖረኝ፡ በገደልኩሽ ነበር፡ ስብሰባውም በቀረብኝ ነበር። እነዚያን ሆሊ-ሮለሮች በዚህች ምድር እንዳያልፉ ለማስቆም መንገድ ላይ ነኝና። አንቺ ላይ—ባደረኩት ነበር።" አያችሁ?

214 ከዚያ የመጀመሪያ ያደረገው ነገር፡ ዙርያዉን አየት አደረገና፡ እንዴ "ምንድነው፡ ይገርማል። በቅሎዋ ሰታወራ እሰማለሁ፡" ብሎ አሰበ።

215 በለዓም፡ ሆይ! እምም! ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለሰዎች ባልታወቀ ልሳን ተናግሯል። በእንትና ዘመንም አድርጓል... እናንተ ግን "በጴንጤቆስጤ ዘመን ብቻ ነው፡" ትላላችሁ። ኦህ፡ አይደለም። አይደለም፡ አይደለም። በብልጣሶር በዓልም በልሳኖች ተናግሯል፡ በቅጥሩም ላይ ጽሕፈት ጽፈዋል። በዚያም የመተርጎም ስጦታ የነበረው ሰው ነበራቸው፡ እርሱም ተረጎመላቸውና፡ ምን እንደ ሆነ ነገራቸው። ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው።

216 ስለዚህ፡ የሚተረጉምለት ስላልነበረ፡ እግዚአብሔር በልዓምን (ካርዲናሉን) አነቃው እና ምን እንደነበረም ተገነዘበ። እና ግን ይህ ዓይነ ሰውር ምስኪን ዝም ብሎ መንገዱን እንደቀጠለ ታውቃላችሁን? በትክክል። ዛሬ

ዛሬ የሚያደርጉት ነገር ያው ነው፡ ተመሳሳይ ነው፡ ሞዓባውያን፡ ኒቆላውያን፡ መንገዳቸውን ቀጠሉ። በቀጥታ መንገዳቸውን ቀጠሉ፡ እርሱም ሄደ... አሁን ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር የመሠረታዊነት አክባሪ ቢሆን ኖሮ፡ ሞዓብን የመባረክ ግዴታ ነበረበት፡ ምክንያቱ፡ በለዓም ሰባት መሠዊያዎች መሰራቱን፡ አስተውሉ። ያ ትክክል ነው።

217 ሰባት ቁጥር፡ ሰባት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ናቸው። መንፈሳዊው አተገባበር አያችሁት? አሁን፡ ያንን ያዙልኝ አሁን፡ መንፈሳዊ አተገባበር። በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ ወደ ከባዱ ሰፍራ፡ እገባለሁ። አያችሁ፡ መንፈሳዊው አተገባበር። ሰባት መሠዊያዎች፡ ሰባት ወይፈኖች (ከንጹሕ እንሰሳት) እና ሰባት አውራ በጎች፡ ክርስቶስ ከመምጣቱ ከመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት፡ ስለ መምጣቱ የሚናገር ነበር።

218 ግን፡ አማኞች ነበሩ። ምን ያምናሉ? በያሕዌ በእግዚአብሔር ያምኑ ነበር። ሌላስ ምን ያሙ ነበር? ንጹሕ መሥዋዕት እንደሚቀርብለት ያምኑ ነበር። ትክክል። መሲሑ ይመጣል ብለው ያምኑ ነበር፡ ምክንያቱ፡ ተባዕት የሆነ—አውራ በግ መሰዋዕት ስለሚያቀርቡ። ልክ ነው?

219 እስኪ፡ አሁን አንዱ ብቻ ከባፕቲስት ነገር ጋር አዛምዱት፡ እና ሰራቸው አንድ አይነት ካልሆነ መርምሩት። ይህ በትክክል እውነት ነው።

220 ታዲያ አሁን፡ ልዩነቱ ምንድነው? እነሆ እስራኤል በኮረብታው ራስ ላይ ያቀረቡትን ተመሳሳይ ዓይነት መሰቅዋዕት እያቀረበ፡ እና ተመሳሳይ አምላክ እያመለከ፡ ከኮረብታው በታች ሰፍሮ ነበር። ኒቆላውያኖቹን አታዩአቸውምን? ዲቃላዎቹ! አያችሁት? እውነተኛው መንፈሳዊነትስ አይታያችሁምን? ልዩነታቸው ምን ነበር? ከመካከላቸው አንዱ የሚከተሉት ምልክቶች ነበሩት! አንደኛው የነገር **ቅርጽ** ነበረው፡ ሌላኛው ግን **የሚከተሉት ምልክቶች** ነበሩት።

221 እዚህ በኒቂያ ጉባኤ፡ በኒቆላውያን፡ መደበኛው ክርስትና ውስጥም፡ ተመሳሳይ ነገር ነበረ። አሁንም መንፈስ ቅዱስ እንደገና መጥቶ "የበለዓምን ትምህርት በመካከላችሁ አለ፡" ይላቸዋል። አያችሁ? "እናንተ... እነርሱ የያዙት ትምህርት፡ የእስራኤል ልጆች እንዲሰናከሉ ያስተማረው፡ የበለዓም ትምህርት የኒቆላውያን ሰራዎችን ናቸውና እነዚህን እጠላቸዋለሁ።" እንዴት አደረገ?

222 ዎቹንስ ሊረግም በወጣ ጊዜ፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡ "እንደበትህን አስርሃለሁ፡ እኔ ተናገር ብዬ ካዘዝኩህ ሌላ ምንም አትናገርም። የባረኩትን መርገም አትችልምና።" ያኔ አሻግሮ አየ።

223 አሁን ግብዙን ተመልከቱት! አይይ፡ በቃ አሁን እንተዋቸዋለን፡ አያችሁ። ያን ንጉስ ባላቅን ተመልከቱት አሁን፡ የ—የ—የ—የሁሉ ራስ የሆነው ሰው፡ ሃሰተኛውን ነብይ ነገረው፡ እንዲህ በማለት፡- "ወደዚያ ውረድ እና በጀርባ በኩል ተመልከታቸው።"

224 ትላልቆቹ አብያተ ክርስቲያናት—ለታናሹ የእግዚአብሔር መንጋ መናገር የሚፈልጉት በዚህ መንገድ ነው። "ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ከእነርሱ አንደኛውን አውቀዋለሁ። ጃል! ምን እንዳደረገ ልንገራችሁ? እንዲህ—እለ **እንዲህ** አደረገ፡ **ያንን** አደረገ። ጴንጤቆስጤዎቹ። አዎን።" አቤት፡ **ስለነሱ** አንዳች ነገር ብታገኙባቸውኮ፡ ጋዜጣው እና ሌላው ሁሉ ያዳፍንላቸዋል። ነገር

ግን አንድ ጴንጤቆስጤ የሆነ ሰው በሰሱ ከመሰመር ይውጣ፡ አገሪቱ በሙሉ አካኪ ዘራፍ ትልበታለች። በትክክል። አዎን፡ ወዳጄ።

225 አሁን፡ ግን አስተውሉ፡ እንዲህ አለ፦ “የጀርባውን፡ የኋላውን፡ ደካማው ጎን ብቻ እይልኝ።” በልዓምም አለ፦ “አዎን፡ በጀርባቸው በጎን በኩል እያለሁ፡ ጉዳቸውን እመለከታለሁ። እኔ የማደርገው ያንን ነው፡ አሸንክታቦቻቸውን—ብቻ እመለከታለሁ፡ ጉድለታቸው-ላይ።” ያየኸው ጉድለታቸው-ላይ ከሆነ፡ ተራ ናቸው። አዎን። በዘመናቸው ሁሉ ኃጢአትን አድርገዋል። ማየት የተሳነውን ነገር ግን፡ የተመታው ድንጋይ፡ የነሐስ እባቡን፡ በመካከላቸው ያለውን የንጉሱን ደስታ ማየት ተሰኖታል፡ ፈውስ፡ ምልክቶች፡ ድንቆች፡ እና በላያቸው የሚያልፈው የእሳት ዓምድ አላየውም።

226 ያ የታወረው ነቢይ ሊያየው አልቻለም። አልቻለም፡ ጌታዬ። ነገር ግን ደካማ ጎናቸውን እያሳያቸው ነበር፡ “አየህ፡ ይሄኛው የሌላ ሰው ሚስት እንደሚከተል አውቃለሁ። ይ—ይህን አውቀዋለሁ፡ ገንዘብ የሰረቀ ነው።” ትክክል። ልክ ነው። እኔም አምንበታለሁ፡ ይሁን እንጂ ሌሎቹ ያንኑ ነገር ሲያደርጉ፡ ስለ ጉዳዩ ማንም ሰው አይናገርም። እያችሁ? እና ደካማው ጎናቸው እያሳየው ነው።

227 እግዚአብሔር ግን፡ ኣንዲህ አለው፡ “እኔ የምለውን ብቻ ትናገራለህ።” በለዓምም መንፈስ ውስጥ ገባ፡ ራዕይም በላዩ ላይ ወደቀ፡ እሰራኤልንም ከመራገም ይልቅ፡ ባረካቸው። አሜን! ያ ነው።

228 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር... እነዚህን በመሰረታዊነት የሚታወቁ ነገሮችን፡ እነዚህ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን፡ እና ታላላቅ ሰሚናሪዎች እና ኮሌጆች፡ እነ ፒ.ኤች.ዲ እና ዲ.ኤል.ዲ.ዎችን እና፡ ኦህ፡ ልዩ ልዩ ዓይነት ዲ.ዲ.ዎችን ቢያከብር ኖሮ... እንግዲህ፡ እነዚያን ነገሮች አክባሪ ቢሆን ኖሮ፡ እንግዲህ፡ መቼም፡ አክብሮት ሊኖረው... ይገባ ነበር። እያችሁ? እርሱ ግን እነዚያን ያከብራቸው ሰዎቹንም በበረከት ባርኳቸዋል፡ ምክንያቱም መንፈሱ፡ እና ንጉሱ... “በሰፈሩ ውስጥ የንጉሱ ዕልልታ ሆነ፡” ብለውታልና። ምን? ምን? “**የቅዱሳን ንጉሥ**።” ዕልልታ እና ደስታ! የምን ደስታ? የሌላ መንግሥት።

229 የሐይማኖት ተቋም እንዳልነበሩ አረጋግጥላችኋለሁ። እንዳረጋግጥላችሁ ትፈልጋላችሁ? ለዛ የሚሆን ቅዱስ ቃል እዚህ ያሰቀመጥኩ ይመስለኛል። አዎን፡ ወዳጄ። እስራኤል እንደዚያ አልነበረችም... ዘህልቁን እንክፈት፡ እንዳልነበሩ እንድታዩ ብቻ ነው። እነሱ... እነ፡ ሞዓብ ታላቅ የሐይማኖት ተቋምም ነበር። ዘኍልቍ 23፡9ን እንከፍታለን፡ በዚያም 8ኛውን ቁጥር—እየዋለሁ፡

> እና... **እኔስ**—(አለ በልዓም)፡ **እግዚአብሔር ያልረገመውን፡ እንዴት እረግማለሁ? ወይስ ጌታ ያላረከሰው፡ እንዴት አረክሰዋለሁ?** (ኧሀ-ህሀ።)

230 እሱ ያለውን አሁን... በደንብ ያዳምጡ፡

> **በ—በአምቦች ራስ ላይ ሆኜ** እየዋ**ለሁ፡...** (ያም እግዚአብሔር ነው። ከታች ከሸለቆው ውስጥ ሳይሆን፡ ከአምቦች ራስ ላይ። ኦ! “እይናቹ በድንቢጦች ላይ ነው፡ እኔንም እንደሚመለከተኝ አውቃለሁ።”)... **ከአንቦች ራሰ ላይ ሆኜ** እየ**ሁት፡...** (አሜን! በአንዳንድ ጎን... ከሸለቆዎች በሰተጀርባ ጨረፍታቸው ለማየት ብቻ ሳይሆን፡ “ሁሉንም ነገር እይቼዋለሁ፡” ይላል እግዚአብሔር።) ...

**ከአንቦች ራስ ላይ ሆኜ አየዋለሁ፡ በኮረብቶችም ላይ ሆኜ እመለከተዋለሁ፡ እነሆ፡ ብቻውን የሚቀመጥ ሕዝብ ነው፡ በአሕዛብም መካከል አይቈጠርም።**

231 ይህ ይመልሰዋልን? “ሕዝብ፡” እንጂ የሐይማኖት ተቋም አልነበሩም። ኦህ፡ ትንንሽ ትልዕኮዎች፡ በድንኳኖች፡ በአውራ ጎዳናዎች፡ መንገድ ጥግ ላይ፡ ተቅበዝባዦች ነበሩ። ጀርባ ላይ ይወጣሉ፡ ይከራያሉ፡ ያባርሯቸዋል፡ እግዚአብሔር ወደ ሌላ አገር እንዲሄዱ መድቧልና። አያችሁ? ተቅበዝባዦች! በትክክል!

232 በቅርብ ጊዜ፡ ጃማይካ ውስጥ፡ የጸና ጥሩ የጴንጤቆስጤ የሰነመለኮት ዶክተር ነበር። እኔም አልኩት፡ “ኦህ፡ ጌታ የጥንቷን የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንደባረከ፡ ምንም አልነበራቸውም።” “እንደው፡ ወዲያ ወዲህ ተቅበዝባዦች ነበሩ፡” አልኩት።

“ኧሃ፡ ወንድም ብራንሃም? ” አለኝ፡

የምወደው፡ መልካም ወንድም ነው፡ “አዎን፡ ወንድሜ፡” አልኩት።

እርሱም “የሳትክበትን ስፍራ ላሳይህ እ—እፈልጋለሁ፡” አለኝ።

እኔም አልኩት፡ “ኦህ፡ የተቀደሰ አሳብ ነው። ሁልጊዜ ስሕተቴን ማወቅ እ—እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ያውቃል፡ እ—እኔ መሳሳት አልፈልግምና።” “እንግዲህ፡ ወንድሜ፡ ተሳስቼ ከሆነ፡ በእርግጠኝነት ማወቅ እፈልጋለሁ። አመሰግናለሁ፡” አልኩት።

“ጴንጤቆስጤዎቹን ሁልጊዜ ታወድሳቸዋለህ፡” አለኝ።

“አዎን!” አልኩት፡

“ንብረታቸውን በሸጡ ጊዜ መሸጣቸው እጅግ አስከፊ ስህተት አድርገዋል፡” አለኝ። አለኝም፡ “ስደቱ በተነሣ ጊዜ፡ የሚሄዱበት ቤት እንኳን አልነበራቸውም። የተቅበዘበዙት፡ የሚሄዱበት ቤት ስላልነበራቸው ነው።”

“በትክክል የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ነበር፡” አልኩት።

“ለምን? ” አለኝ፡

233 እኔም አልኩት፡ “ቤት ቢኖራቸው ኖሮ ይመለሱ ነበር፡ ነገር ግን የምስራቹን ዜና ለማሰፋፋት፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ የመምጣቱ ዜና ለመናገር፡ ከቦታ ወደ ቦታ፡ መሄድ ነበረባቸው። እግዚአብሔር ስህተት ይሳሳታል አትበለኝ። በጭራሽ አይሳሳትም። እንዴት እንዲሰራ ያውቃል። ዜናውን በየቦታው እያሰራጩ፡ ንብረታቸውን ሸጠው ዟሪዎች ሆኑ።” እና እንዲህ አልኩት፡ “ዜናው በዚያን ዘመን በመላው ዓለም በሚታወቀው ዓለም ተሰራጨ፡ ይህም መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት ሁሉንም ትተው በተቅበዘበዙ ሰዎች ነው።” እነዚያም ሰዎች የአንድ ሐይማኖት ተቋም አባል አልነበሩም። አያችሁ?

234 አሁን፡ አስታውሱ፡ እግዚአብሔር እየጠራ ያለው የሐይማኖት ተቋምን ነው፡ “የበልዓም ትምህርት የተወጉ ናቸውና።” እና፡ እንግዲህ፡ ወደ ሐይማኖት ተቋም ሊያገባቸው ባልቻለ ጊዜ፡ በለዓም ያደረገውን ታውቃላችሁን? አሁን፡ በደንብ አዳምጡ፡ ወደ መዝጊያው እየቀረብን ነው። አሁንም በለዓም ያደረገው ነገር፡ ያኔ በኒቂያ ጉባኤ ያደረጉትን ተመሳሳይ ድርጊት እንዲሁ አደረገ።

“የበለዓምን እና የእነዚያን ኒቆላውያንን ትምህርት በመካከላችሁ አለ፡” ያለበት ምክንያት ያ ነው።

235 እንግዲህ፡ ኒቆላውያን ማለት ድርጅቶችን እና—ልዩ ልዩ ነገሮችን ለመሰራት የወጡ ሰዎች ናቸው። ያም፡ በስተመጨረሻ... እስኪ “ድርጅት” ብዬ ስናገር፡ ስንቶቻችሁ እውነት እንደሆነ ይገባችኋል? የእግዚአብሔር እውነት በትክክል ያ ነው። በመጨረሻም በመላ ዓለም ትልቁ ድርጅት አቋቋሙ። እና ምን አደረጉት? ካቶሊክ። እና **ካቶሊክ** የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? “ዓለም አቀፋዊ።” ዓለም-አቀፍ፡ የተደራጀ፡ ድርጅት፡ “ሌሎች ሁሉ ጥቃቅን ነገሮች ወደ እንዲት ቤተ ክርስቲያን መምጣት አለባቸው።” አሁን፡ ካስተዋላችሁ። ኦህ፡ እ... ዝም ብላችሁ ቀጥሉ።

236 ተመልከቱ! ባቢሎን ምን ነበረች? ባቢሎንን የመሰረተው ማን ነው? ናምሩድ። ምን አደረገ? በአንድ ትልቅ ከተማ ውስጥ አንድ ትልቅ ግንብ ሠራ፡ ሌሎቹም ከተሞች ሁሉ ለዚህች ከተማ ግብር እንዲሰጡ አደረገ። ድርጅት! ዳራዎቿ እነዚህ ናቸው። በእርግጠኝነት። በቤተ ክርስቲያን ዘመን ወደዚህ ኑና ተመልከቱት፡ ተደራጅተው አሕዛብን ሁሉ ወደ እርሷ አስገቡ። እና እዚህ ላይ “አሕዛብን ሁሉ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ያጠጣች ጋለሞታ፡” ይላታል። “ክርስትያን” ነኝ እያለች፡ በምትፈጽማቸው ምንዝርናዎቿ እነዚያን ኮተታኮተቶች ሰጠች፦ ካቴኪዝም፡ የጸሎት መጽሐፍት፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ። ፕሮቴስታንቶችም ተመሳሳይ ነገር ናቸው፡ መንገዷን ተከትለው፡ ልክ እንደዚሁ መጡ።

237 እሺ፡ አሁን ትንሽ ራቅ ብለን እንቀጥል። እሺ። እሺ። እሱም፡ “የበለዓም ትምህርት ይህ ነበር፡” አለ።

238 አሁን፡ በለዓም እስራኤልን መራገም እንዳልቻለ—እንደማይችል ሲያውቅ ምን አደረገ? ያኔ፡ እነዚህ ሰዎች ወደ አማልክትህ በዓል ብትጋብዛቸው መልካም ነገር ነው፡ በማለት ባላቅን መከረው። ታላቅ ክብረ በዓል ለማድረግ... እየተዘጋጁ—በዚያም፡ ዝግጅት—ላይ ስለነበሩ ነው። የበዓሉ ስያሜ “የበዓል-ጲ-ዖ-ር በዓል፡ በዓለ-ጲዖር”... ይባላል። ጲ-... ጲዖር፡ በዓል-ጲዖር። የአምልኮ፡ በዓል የ—የነበረ ይመስለኛል።

239 በለዓምም እንዲህ አለው፡ “ባላቅ ሆይ፡ አሁን፡ እነግርሃለሁ፡ ጥሩ አሳብ እሰጥሃለሁ። እንግዲህ... አንተም ካሰብክበት... እግዚአብሔር አይረግማቸውም፡ አለቀ ደቀቀ፡ ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብን እነግርሃለሁ። እነሱን ማሰወገድ አንችልም፡ እነሱን ከጋበዝካቸው ግን፡ ሁሉንም ነገር ወደ ራስህ መንገድ ታንቀሳቅሰዋለህ።”

240 አያችሁ፡ በትክክል፡ ቆስጠንጢኖስ ያደረገውም በትክክል ይህ ነው። ፍጹም! “የበልዓም ትምህርት” ምክንያቱ ይህ ነው።

241 ምን አደረጉ? ከዚያ... የባላቅ ትምህርት በእስራኤል መካከል ወረደ። እስራኤላውያንን፡ ወደዚያ ወደ ታላቅ ግብዣ ጠሩአቸው። አቤት፡ አንድ ታላቅ ድግስ፡ ግርግር የበዛበት ነገር አዘጋጅተው ነበርና። እስራኤላውያን ወደዚያ በደረሱ ጊዜ፡ እነሆ፡ ሴሰኛ-አለባበሰ የለበሱ፡ ቆንጆ የሞዓባውያን ሴቶች ማየት ጀመሩ። አዎን፡ በመካከላቸው እንደነበሩ ተራ ልጃገረዶች አልነበሩም። “አቤት፡ ውበታቸው እጅግ የተዋቡ ነበሩ። አቤት! ከአፈጣጠራቸው ጀምሮ፡ ኦህ፡

እራሳቸውን ማሳየት ይችሉበታል።" ለዚህም ነገር ወደቁና፡ ማመንዘር ጀመሩ። በለዓምም እግዚአብሔር ባይረግማቸውም እንኳ፡ ወደዚህ ወደ ሐይማኖታዊ ተቋም አሳልፎ እንደሚሰጣቸው እና የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚቀሰቀስ እርሱም እንደሚያጠፋቸው አውቆ ነበር፡ ስለዚህ እርሱ ከእውነት መንገድ ብቻ ቢያስወጣቸው፡ እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያጠፋቸው አውቋል።

242 እናንተም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመቀበል ይልቅ የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የወጣችሁ ለታ፡ ሞታችኋል! (**እዚህ** ጋር እንጂ፡ ለእናንተ አይደለም፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ በደንብ እንዲሰርጽ አደርገዋለሁ።) የሞተ! የሰርዴሱ ዘመን፡ ማርቲንን "ስም አለህ፡" ብሎታል። **ሰርዴስ** ማለት ትርጉሙ "የሞተ" ማለት ነው። "ህያው እንደመሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል!" እግዚአብሔር የተናገረው ያ ነው። አዎን። አያችሁ?

243 በዚያም መንፈሳዊ ዝሙት በፈጸሙ ጊዜ፡ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይልቅ የሐይማኖትን ተቋም ጋር ተጋባች፡ ያኔ ሞተዋል። እውነቱ ይህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም የተናገረው፡ እግዚአብሔርም ያለው፡ ለአብያተ ቤተክርስቲያን የተናገረው ያ ነው።

244 አሁን አንድ ነገር ላነብላችሁ እፈልጋለሁ፡ ይህም...

245 እግዚአብሔርስ፡ ምን አደረገ? እና ይህን ክፉ ነገር ባደረጉ ጊዜ፡ ምንዝርና ባደረጉ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ አርባ-ሁለት ሺ ሰዎች ገደለ፡ ስለ ምንዝርና ስራቸው፡ አርባ-ሁለት ሺህ። ታዲያ በዚህች በቤተክርስቲያን ውስጥ ምን ይባል ይሆን? "ክርስቲያን ነን" እያሉ እንደ ዓለማዊ ኑሮ የሚኖሩት፡ መንፈሳዊ ምንዝርና። ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበል! ከእነዚህ አሮጌ የእምነት መግለጫዎች እና ሌሎች ነገሮች ራቅ... የሞቱ ናቸውና፡ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ፡ ወይም ሌላ ዓይነት የሃይማኖት መግለጫን መድገም፡ እና ከጸሎት መጽሃፍ የተፃፉ ጥቂት ጸሎቶችን መናገር ወይም እንደዚህ ያለ ነገር ማድረግ ሞት ነው። ኢየሱስ ሕዝቡን ጸሎት እንዲደግሙ በጭራሽ አልነገራቸውም፡ "ጸልዩ!" አላቸው፡ ጸልዩ! በቃ።

246 አሁን፡ የቆስጠንጢኖስ በዓል፡ እንደ በልዓም ነበረ። አሁን ተመልከቱ። ልክ እንደ በለዓም አረማዊ በዓል፡ ቆስጠንጢኖስ አረማዊ በዓል ነበረው። እሺ። ጴርጋሞስም ተጋብዛለች። እና አሁን ይህን አስተውሉ...

247 አንድ ነገር ጽፌ ይዣለሁ፡ ለአሁን ግን እተወዋለሁ። ይሁን እሺ። ይሁን እሺ። እዚህ ያሰቀመጥኩት... ማስታወሻውን ለመያዝ እየሞከርኩ ነበር።

248 ጴርጋሞንም ተጋበዘች። እሺ፡ የኒቂያን ጉባኤ ክብረ በዓል ለመካፈል ተጋብዘዋል። **ዊንተር ሶሊስቲስ** ወደተባለው ክብረ በዓል ተጠሩ፡ ትርጓሜውም "የጸሐይ፡ የጸሐይ አምልኮ፡" ማለት ነው ይህም አረማዊ አምላክ ነበር፡ በዓመቱ አጭሯ ቀን ላይ፡ በታሕሳስ 21 ቀን የወረደ ይባላል። በእነዚያም ዓመታት... እስከ ታሕሳስ 25 ቀን ድረስ ጊዜው ተመሳሳይ ነው አይለወጥም። አረማውያን ሁሉ ያከብሩታል፡ ይህም የጸሐይ-አምላክ የልደት ቀን ነው። ይህ የጸሐይ-አምላክ የልደት ቀን በዓመቱ ካሉ ቀናት አጭሩ ቀን ነው፡ ታሕሳስ 21 ቀን። እናም የአብያተ ክርስቲያናትን ታሪክ ያነበበ ማንም ሰው አረማውያን በዚያች ቀን አምልኮ እንደሚያካሂዱ ያውቃል። በዓል ነበረ።

249 እንግዲህ፡ ያኔ ሮማውያን… ትላልቅ ጨዋታዎችን፡ ማለትም የሮማውያንን የሰርከስ ትርኢት ያካሂዳሉ። ያንን በቅርብ ጊዜ፡ የለቀቁት፡ ማን እንደሚሉት እንጃ፡ ሰንቶቻችሁ አይታችሁታል? ቤን ሁርን! እያችሁ? እንግዲህ፡ ሮማውያን በጸሐይ ቀን ሲያደርጉት የነበሩትን፡ የሮማውያን ሰርከስ ያ ነበር፡ ይህም የጸሐይ-አምላክ የልደት ቀን በማስመልከት የሚደረግ አምልኮ ነው። እያችሁ?

250 አሁንም… በዚያም ታላቅ በዓል አደረጉና ኒቆላውያንን እንዲመጡ ጋበዙ። አቤት! ፍጹም አይደለምን? “የበልዓም ትምህርት በመካከልህ አለ።” እያችሁ፡ ጴርጋሞስ ዘንድ የነበረው ሲነገር፡ ታላላቅ የሩጫ ውድድሮች ነበሩ። እነዚያም ደግሞ ሲያሰቡት… ኒቆላውያኖች እንዲ አሰቡ፦ “እንዴ፡ አሁን፡ ይህ ነገር ጥሩ ነው። ይህ ታላቅ ድግስ በየዓመቱ የሚከበር በዓል ነውን? አዎን።” ስለዚህ ያኔ ምን እንደሚሉት እንጃ ብቻ፡ በዚህ ግብዣ ላይ ሊ—ሊ—ሊቀ-ጳጳስ እና ሌሎችም፡ ተብየዎቹ ሁሉ ተጋብዟል፡ ቀጣይነት ያለው ለማድረግ፡ ዝሙትን በማምጣት፡ አመንዝራነትን በማምጣት፡ የካቶሊክ ቤተክርስትያንን ሰሩ፡ ይህም የፕሮቴስታንት ሐይማኖት ተቋማት ሁሉ አባል የሆኑበት፡ ድርጅት ነው። እግዚአብሔር ግን ድርጅት የለውም፡ መጠሪያው ራሱ እጅግ ይጠላዋል። መጽሐፍ ቅዱስም ይመሰክራልና።

251 እና ይህን ሲያደርጉ፡ ምን ተፈጠረ? መንፈሳዊ—አተገባበር ሊኖራቸው… ስለሚገባ እንዲህ መከሩ፡ (የጌታ ኢየሱስ) የእግዚአብሔርን ል-ጅ የልደት ቀን ከሚያዝያ ቀየሩት (የበግ ጠቦቶች እና ሌሎች ፍጥረታት በሚወለዱበት፡ በሚያዝያ የተፈጥሮ ወር እንደተወለደ፡ ጥሩ ምሁራን፡ እና መንፈሳዊ መገለጥ ያላቸው ሰዎች በሙሉ ያውቁታል።) ወደ ታኅሣሥ 25 ቀን ድረሰ ወሰዱት። አሁንም ገና በማለት ያመልኩታል፡ አሁን የገና አባት አርገውበታል፡ ኸረ ምንድነው… አቤቱ፡ ማረን። እያችሁ? አሁንም ተጨማሪ አረማዊ በዓላት ይጨመርበታል። ያ ነው። እነሆ፡ በለዓም፡ ተጋብዘዋል። “በእናንተ መካከል የበለዓም ትምህርት አለ።” ይኸው ነው። (አምላክ ሆይ፡ ግለጥልን፡ አባቴ።) እያችሁ? የልደት ቀኑ ከሚያዝያ…

252 አሁን፡ የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት “ኢየሱስ የተወለደው ህያዋን ሁሉ በሚወለዱበት የሚያዝያ ወር እንደሆነ ምሁራን ሁሉ ያረጋገጡት ነገር ነው።” ይሁን እንጂ ወደ አምስት ወራት በኋላ፡ ወደ ታሕሣስ 25 ቀይረውታል (እያችሁ? ) አረማዊነት እና ክርስትናን በመቀየጥ፡ በአረማውያን አምላክ ስም፡ የጋራ በዓላቸውን ለመሰራት ነው። ስለዚህ ካቶሊካዊነት የአረማውያን አጉል እምነቶች እና የተሻሩ-የክርስትና ልምዶች ጣምራ ከመሆን የዘለለ በዓለም ላይ ትርጉም የለውም። ትክክል ነው። እውነት ነው። እዚህ ነገር ላይ የተንጠላጠሉ ፕሮቴስታንቶችም የአመንዝራዋ እናታቸው ሴቶች ልጆቿ ናቸው። ይህ እውነት ነው።

253 አሁን፡ አምላካዊ ባልሆነ ነገር ሁሉ ላይ እውነተኛ ተቃዋሚዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን። እያችሁ? አቤት!

254 በዚህ ነገር ላይ መንፈሳዊ መተግበሪያውን ለመፈጸም፡ ቢሾፑ የሚናገረውን አውቃችኋል? ቢሾፑ እንዲህ አለ፡ “‘የጽድቅ ጸሀይ’ እሱ ራሱ ስለሆነ እኛ የወደድነውን የማድረግ መብት አለን።” እምም! አቤት፡ በማቴዎስ 28:19፡ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡” ላይ እንዳደረጉት ተመሳሳይ

ዓይነት፡ ነገር ለማድረግ፡ ክፍተት አገኙ። አዎን፡ ክፍተት አገኙ፡ ምክንያቱ እንግዳ አይነት መንፈሳዊ ትግበራ ሊኖራቸው ያስፈልጋልና፡ አያችሁ። ይሁን እንጂ...

255 መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይላል፡ “አንድ ቃል በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ይጸናል።” እግዚአብሔር በዚያ ሲናገር፡ ሦስት ጊዜ ተናገረ። እግዚአብሔር አንድን ነገር ለመፈጸም ሲፈልግ፡ ጴጥሮስን፡ ያዕቆብንና፡ ዮሐንስን ይወስዳል። የሚሰራውን ሁሉ ለማረጋገጥ፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ቃላት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ፡ ስራውን የሚያረጋግጡለት ሁለት ሶስት ምስክሮች ነበሩት። በትክክል።

256 ይሁን እንጂ፡ አያችሁ፡ እነዚያ ጥቃቅን ነገሮች ተለቅመው ያን ነገር ይሆኑ ዘንድ በዚያ ሁኔታ ውስጥ መገኘት ነበረባቸው። እግዚአብሔርም ዓለም ሳይፈጠር በፊት ይህን ያውቀዋል። እነርሱም በዚያ ውስጥ፡ መንፈሳዊውን መተግበሪያውን አገኙ፡ “እርሱ የእግዚአብሔር ል-ጅ ነውና፡ የአረማውያንን የ ጸ-ሐ-ይ የልደት ቀን ወሰደን የ ል-ጁ የልደት ቀን እናደርገዋለን፡ ምክንያቱ እርሱ ‘የጽድቅ ጸሐይ ነውና።” እምም! እምም! ፕሮቴስታንቶች አሁንም፡ ለዚያ እና መሳይ ነገሮች እንደሚወድቁ፡ ታውቃላችሁ። በርግጥ፡ ይወድቃሉ፡ ወዲያውኑ ከቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ሌላ ቦታ ያዞሩታል። ኦህ፡ ማይ! እ... ለአፍታ—ያህል እዚህ ቆም እንበል። እሺ።

257 እዚህ ማምጣጥ የምፈልገው ትንሽ ነገር አለ። የመጨረሻውን ጥቅስ በፍጥነት እዚህ ጋር እናምጣው። ማምጣት እንችላለን? አዎን። እሺ፡ ቶሎ እፈጥናለሁ፡ አሁን በትክክል እፈጥናለሁ። እናንተም... የነገሩን ዋና ዋና ነጥቦች እንነካካዋለን። እሺ። የት ነው የደረስነው?

> **ነገር ግን... እኔ ደግሞ... የምነቅፍብህን... ጥቂት ነገር አለኝ... በልዓም፡...**

ልክ ነው፡ አገኘሁት።

> **እንዲሁም**... የኒቆላውያን **ትምህርት በአንተ ዘንድ አለ...**

> **ንስሓ ግባ፡... አለዚያ ግን... ቶሎ... እመጣብሃለሁ... በአፌም ቃል** አንተን **እዋጋሃለሁ።**

> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ** ያለው **ይስማ፡...**

258 አቤት! ቆስጦንጢኖስ ይህን ባደረገ ጊዜ፡ ያን... ታላቅ በዓል በደገሱ ጊዜ። እ—እ... አሁንም ከዚያ መውጣት ጀመርኩኝ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኋላ እየመለሰኝ ስለሆነ ከማንበቤ በፊት እጠብቃለሁ፡ እንግዲያውስ ይህን ያደረግኩበት ምክንያትም ለዚህ ነው፡ “ያንን ወደ ኋላህ አትለፈው፡” አለኝ። አያችሁ? ይኸው መጣ! ኧህ-ህህ፡ ኧህ-ህህ፡ ኧህ-ህህ። በጣም ጥሩ። የዚህ ምክንያት...

259 ይህን ታላቅ ነገር ባዘጋጁ ጊዜ፡ (እናንተም እንድትረዱት ያኔ የሆነውን እነግራችኋለሁ።) የድህረ-ሺህ ዓመታት ልደት ነበር። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ባለ ጸጋ ሆና ነበር፡ ከዓቅሟ በላይ ባለጸጋ ሆነች። ያሰ ምን ነበር? ኃይል። ከመንግስት በላይ ነበረች፡ መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን አብረው ሆኑ።

260 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር እስከነ ግዛቱ? ኢየሱስስ የተናገርው ምን ነበረ... መንግስታት ሁሉ የኔ ናቸው፡ ኢየሱስን ሲናገረው፡ የዓለምን መንግስታት ሁሉ አሳየውና፡ እንዲህ አለው፡ "እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው። እኔ የወደድኩትን ሁሉ አደርጋቸዋለሁ።" ታዲያ እግዚአብሔር እና ዲያብሎስ አንድነት ፈጠሩን? አይ፡ አይቻላችሁም! በእርግጠኝነት፡ አትችሉም። ለዚህ ነው ያን ግዛት የተደራጀው። እነዚህ ድርጅቶች፡ እግዚአብሔር አይደለም። በጭራሽ፡ አይቻላችሁም።

261 ያኔ ግን ይህ ነበራቸው፡ ቤተ ክርስቲያናቸው እና ክርስትና፡ ከአገሪቱ ጋር፡ ከመላ የሮም መንግስት ጋር፡ በጠቃላይ አንድ ላይ አጣመሩት። በሁሉ ላይ የነበረው ያንን ቢሾፕ፡ ቦኒ-... ይባል የነበረውን ከጊዜ በኋላ ጳጳስ ብለው ጠሩት፡ በመጀመሪያ ግን—ቢሾፕ ነበረ። እና የመጀመሪያው ጳጳስ የሆነው ቦኒፌስ ሳልሣዊ ነበር።

262 ከዚያም እዚያ እንደ ጳጳስ ተሹሞ እናገኘዋለን... ያም በሰው አምሳል የሆነ፡ አምላካቸው ነበር። ታላቅ መሠዊያ ነበራቸው። እጅግ ባለጸጎች ነበሩ። በእብነ-በረድ የተነጠፉ፡ በከበሩ ድንጋዮች፡ በልዩ ልዩ ነገሮች ያጌጡ፡ ታላላቅ፡ መሠዊያዎች፡ ነበሯቸው። ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትም ነበሯቸው። ግዛቱን ተቆጣጠሩት። እና ምን እንደተባለ ታውቃላችሁ? ለምስኪኖች አይሁዶች የተገባላቸው ቃል ኪዳን "የሺህ አመት መንግስት ይህ ነው፡" የሚል ወሬ መናፈስ ጀመረ፡ ያም፡ (በፍፁም አልተዋችሁም ብሏቸው የነበረው) "እግዚአብሔር አሁን ትቷቸው ነበርና፡" እና ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የሺ ዓመት መንግሰት ለማድረግ ሞከሩ። የሺ ዓመት መንግሰት የሚሆነው ግን ኢየሱስ ሲመጣ ነው።

263 የድህረ-ሺህ ዓመት የትውልድ ቦታ ያ ነው። እናም ካቶሊኮች እስከ ዛሬ ድረስ፡ የኢየሱስን መምጣት የማያስተምሩበት ምክንያት ይህ ነው። "ሁሉም በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ነው። የሺሁ ዓመት መንግሰት ይህ ነው። ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ነገር ባለቤት ነች። ይህ ነው።" ድኅረ-ሺህ ዓመት (ኡህ፡ ማይ!) ከኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ሳይኖር፡ አያችሁ። ይህ የሆነው በ312 እና መካከል ቆስጠንጢኖስ በተገደለበት ዘመን—እ... **እ.ኤ.አ** ከ312 እስከ 606 ባለው ውስጥ ነው። ከዚያም ቦኒፌስ ሣልሳዊ በመላው ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ላይ ዓለም አቀፋዊ ቢሾፕ ወይም ጳጳስ ሆነ።

264 ይህንን ጥቅስ ማጠናቀቃችን አምናለሁ፡ ከዚያ በኋላ እንገባበታለን። እግዚአብሄር ይመስገን። አያችሁ? አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ አቆያችኋለሁ። 17ኛው ቁጥር፡

> **ጆሮ ያለው ሁሉ፡ መንፈስ—መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት** የሚለውን **ጆሮ** ያለው **ይሰማ፡ ድል ለነሣው... የተደበቀውን መና ይበላ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡ ነጭ ድንጋይም እሰጠዋለሁ፡ በድንጋዩም ውስጥ፡** ከተቀበለው በቀር **ማንም የማያውቀው አዲስ ስም ተጽፎአል።**

265 ለነገ ምሽት እናቆየው፡ ወይስ አሁን ይሁንላችሁ? [ጉባኤው መልስ፡ "አሁን!"—አርታዒ።] እሺ።

266 የሰማይ አባት ሆይ፡ ህዝቡ አሁን መረዳት እንድትሰጠው፡ በጌታ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፡ በሁሉም ስፍራ (ቴፑ በሚሄድበት ቦታ ሁሉ) መረዳት

ይሁንላቸው፡ እኔ—ይህን የምልበት ምክንያት አንተ—ለእኔ በሰጠኸኝ መለኮታዊ ትርጓሜ መናገሬን ያውቁ ዘንድ ይሁን። አሜን።

**... ድል ለነሣው...**

267 በመጀመሪያ እንድታስታውሱት የምፈልገው፡ እያንዳንዱ መልእክት የተነገረው ለቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፡ ለቤተ ክርስቲያን መልአክ መሆኑ ነው። ወደዚህ መለሰ ብላችሁ ተመልከቱ፡ የመጀመርያው፡ የኤፌሶን ቤተ ክርስ-... ወደ ቤተ ክርስቲያን... ምን...

**ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ...** (ልክ ነው? )

268 ከዚያም፡ የሚቀጥለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ 8ኛው ቁጥር፡-

**... ወደ የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ...**

269 ከዚያም፡ 12ኛው ቁጥር ላይ፡-

... ወደ **ጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን መልአክ**... (ልክ ነው? )

270 መልእክቱ የተነገረው ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ነው። ከመልእክቱ የሚርቀውን ሰው እግዚአብሔር ይርዳው! መልእክቱ የተሰጠው ግን ለመልአኩ ነበረ፡ መልአኩም በእጁ ቁጥጥር ስር ነበረ፡ ከእርሱም ከቀኝ እጁም፡ ኃይልን ይሰጠዋል። በቀኝ እጁ ውስጥ ናቸው፡ ማለትም፡ በምድር ላይ ሳሉ ባለ ከፍተኛ ስልጣን ናቸው፡ ለቤተ ክርስቲያን ዘመን ብርሃንን የሚሰጡ፡ ከእርሱ የመጡ ብርሃናት ናቸውና። አያችሁ? "ወደ ቤተ ክርስቲያን **መልአክ**።" ተጣያቂ ለሚሆነው (ለዘመኑ) **ኮከብ** የተላከ ነው። ቃሉን ካልሰበከ ተጠያቂው የቤተክርስቲያን መልአክ ነው። ትክክል ነው። ያ መልአክ በፍርድ ጊዜ መልሰ መሰጠት ይኖርበታል።

271 በቅርብ ጊዜ እዚህ የተሰጠ ራዕይ የሚያስታውሰ ማን ነው... ወደዚህ ተመልከቱ። አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ—ጋደም ብዬ፡ መንፈሰ ቅዱሰ መጣ፡ እና ወደ ኋላ ተመለከትኩኝ፡ እና ሚሰቴ አለች። በዚያም ተኛቼ፡ ወደ ሰማይ መገኘት ተወሰድኩ፡ እናም እነዚያን ሰዎች ሁሉ አየኋቸው። ያ ነገር ሰነግራችሁ ታስታውሳላችሁ አይደል? ሁላችሁም ታሰታውሳላችሁ። አያችሁ?

እኔም ጠየቅኩት፡ "እነዚህ፡ እነማን... ? "

እርሱም "ልጆችህ ናቸው፡" አለኝ።

እኔም "እነዚህ ሁሉ ብራንሃሞች ናቸውን? " አልኩት፡

ሚሊዮኖች ነበሩ። እርሱም 'አይደሉም፡" አለኝ። "በአገልግሎትህ የተለወጡ፡" ናቸው አለኝ።

"የተለወጡ? " አልኩት፡

272 "ያቺ እጅግ የምታደንቃት፡ ቆንጆ ወጣት ሴት አየሃት፡ እሷ'ኮ፡" "ወደ ክርሰቶሰ ሰትመራት ዘጠና ዓመት አልፏት ነበር፡" አለኝ።

እኔም እንዲህ አልኩት፡ "ኦህ!" አልኩት፡ "የፈራሁት ነገር ይህ ነውን? "

እርሱም "እዚህ የጌታን መምጣት እየጠበቅን ነው፡" አለኝ።

እኔም "እሱን ማየት እፈልጋለሁ፡" አልኩት።

273 አለኝም፡ “አሁን እሱን ማየት አትችልም፡ ግን” አለኝ፡ “በቅርቡ ግን ይመጣል። እርሱን እየጠበቅን ነው፡ ሲመጣ ግን፡ መጀመሪያ ወደ አንተ ይመጣል። አንተም በሰበከው ወንጌል መሰረት ይፈረድብሃል፡ እኛም ሁላችን የአንተ እንሆናለን።”

“እንዴ፡” “የዚህ ሁሉ ሰው ተጠያቂ እኔ ነኝ ማለት ነው? ” አልኩት፡

“የሁላችንም!”

“እንዴ፡ ሁሉም እንዲህ ይሆናሉን... ? ” አልኩት፡

“አንተ የተወለድከው መሪ ሆነህ ነው፡” አለኝ።

እኔም ‘ታዲያ፡ ሁሉም ተጠያቂ ይሆናሉን? ” ብዬ ጠየቅኩት፡

እርሱም “መሪዎች ሁሉ አዎን፡” አለኝ።

“ጳውሎስስ? ” ብዬ ጠየቅኩት፡

“እርሱም **ለገዛ** ዘመኑ ተጠያቂ ይሆናል፡” አለኝ።

“እንዴ፡” “እኔም እሱ የሰበከው ያው ወንጌል ሰብኬአለሁ፡” አልኩት።

እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ድምጾች ተነስተው፡ እንዲህ ብለው አወጁ፡ “እኛም በዚያ ላይ አርፈናል!” [ጉባኤው ሁሉ “አሜን!” አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? ይኸው ነው፡ “አርፈናል።”

274 ስለዚህ የእግዚአብሔር **መልአክ**፡ የቤተክርስቲያን መልእክተኛ፡ ቃሉን ካልሰበከ ተጠያቂ ነው። በጣም ጥሩ።

275 “ከተሰወረ መና።” የምንችለውን ያህል ትርጓሜውን እንስጥ። “ከተሰወረ መና” የምን ምሳሌ ነው? ከተሰወረ መና በአንድ ልዩ ሰፍራ ይቀመጥ የነበረ መና ነው... ወይም በመጽሐፍ፡ ቅዱስ ውስጥ ለካህኑ ብቻ የሚሰጥ፡ ህብስት ነበረ። ሰንቶች ታውቁታላችሁ? አያችሁ? ያም፡ ለጉባኤው አይሰጥም ነበር... የራሳቸው እንጀራ ነበርና፡ ለካህኑ ግን ልዩ ህብስት ይዘጋጅለታል። ልክ ነው?

276 ያ ልዩ እንጀራ ነው፡ ልዩ እንጀራ፡ **የተሰወረ** መና። ማን ነው? መናችን ማን ነው? ክርስቶስ ነው። እሺ፡ ማስታወሳ ለምትይዙ፡ ቅዱስ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 6፡ ከቁጥር 48 እስከ ቁጥር 50 ያዙ። ኢየሱስም “ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣው የሕይወት እንጀራ፡” መናው እኔ ነኝ ብሏል።

277 ታዲያ፡ “ከተሰወረ መና” ምንድነው? ለጉባኤው ሁሉ የማይሰጠው መና ነው። መገለጡ የቃሉ መገለጥ፡ በቤተ ክርስቲያን መልአክ ላይ ፈሰሰ። አያችሁ? የቃሉ መገለጥ ለዘመኑ መልአክ ይሰጠዋል፡ ከሌላ ሁሉ ግን ይሰወራል፡ ማለት (ከተሰወረ መና) ለእሱ የተገለጠ ነው... ለቤተ ክርስቲያኒቱ **መልአክ** የተነገረ ነው። አያችሁ? ገባችሁ? ሰለ ክርስቶስ ምንነት ትንሽ ተለቅ ያለ መገለጥ ነው፡ ምናልባትም ትንሽ ከፍ ያለ ጥሪ።

278 ሉተር ይህን አውቆ ይሆን? ዌስሊ ይህን በዘመኑ አውቆ ይሆን እላለሁ? ኦህ! ቅዱስ ማርቲን ይህን አውቆ ይሆን እላለሁ? ኢራኔዎስ? እንግዲህ፡ ቤተ ክርስቲያን እነዚያን ሰዎች በቀኖና እውቅና እንዳልሰጠቻቸው፡ ታውቃላችሁ፡ ለእነርሱ ቅዱሳን አልነበሩምና፡ ምልክቶች ይከተላቸው የነበረው ግን እነሱን ነበር። በቀኖና—የገዛ ቢሾፖቻቸው፡ ሌሎች ነገሮቻቸውን፡ አጸደቁ።

279 ለምን፡ በቅርቡ፡ አንዲት ሴት **የቅዱስ ማርቲንን ህይወት ታሪክ** መጽሐፍ በእንግሊዘኛ ከመደብር ውስጥ ለመግዛት ሄደች። እና… “ቅዱስ ማርቲን፡” በማለት ጠየቀችው።

280 ሰውዬው መደርደሪያውን ሳብ አደረገና፡ “በታሪክ ውስጥ አይታወቅም፡ ቀኖና አልተደረገለትም፡” አላት። አያችሁ? እስከ አሁኗ ቀን ድረስ የለም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ስሙ አለ፡ እግዚአብሔር ማን እንደነበረ ያውቀውልና።

281 አያችሁ፡ ልዩነቱ ያ ነው። ሰዎች ስሞቻቸው በታላላቅ ነገር ማስጠራት ይወዳሉ፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ግን እንዲህ አይነቱ ነገር ያሰወግዳል። ታላቅ እና ትልቅ ነገር፡ ወይም ታላላቅ እና ትልቅ ነገሮች አይፈልጉም፡ ትሑታን መሆን ይፈልጋሉ፡ ትሕትና። የከፍታ መንገዱ—በትሕትና ነው። “ራሱን የሚያዋርድ ከፍ ከፍ ይላል፡ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል።” እራሱን የሚያዋርድ። ትልቅ ነገር ለመሆን አትሞክር፡ ታናሽ ለመሆን ሞክር፡ ነገር ግን እራስህን ሁን። አያችሁ? በእግዚአብሔር ፊት ትንሽ ሁን፡ በራስህ እይታ ትንሽ ሁን፡ ሁሉም ከአንተ በላይ ይሁን። “ከእናንተም የሚበልጠው የሁሉ አገልጋይ ይሁን።”

282 እሱ ታጥቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ ከኢየሱስ ክርስቶስ በላይ ማን ይበልጣል? እግር-አጣቢ ባርያ፡ ሆነ። የሰማይ አምላክ፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ የቆሸሸ የዓሣ አጥማጆች እግር አጠበ (ኦህ!) ልብሳቸው ጠራርጎ ያመጣው፡ የመንገድ ላይ ትቢያ፡ እና ፋንዲያ፡ አጠበላቸው፡ እ ግር-አጣቢ ባርያ፡ ነበረ። እና ግን ስለራሳችን “እኔ እከሌ ነኝ። ዶክተር፡ ፒኤች.ዲ.፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ ነኝ**፡” ብለን እናስባለን። ኦህ፡ ማይ! ክርስቶስ እንደዚያ አይደለም። ያ ፍቅርን አያሳይም… የተወደደው ኢየሱስ ክርስቶስን አያሳይም። እርሱ ስለ ሁሉ ባርያ ሆነ። በትክክል። እርሱ እንዳደረገልን እርስ በርሳችን ልናደርገው የሚገባን ምሳሌ አስተምሮናል። ኦህ፡ ያ ነው—ጌታዬ ያ ነው። ታላቅ ያሰደረገው ምንድነው፡ እራሱን ታናሽ ሰላደረገው። አያችሁ፡ ታላቅ ያሰደረገው ይህ ነው።

283 በህይወቴ ውስጥ አንዳንድ ታላላቅ ሰዎችን የማግኘት እድል አግኝቻለሁ፡ እኔ ታላቅ ነኝ ብለው ስለ ራሳቸው **ከሚያሰቡ** ሰዎች ጋር የመገናኘት እድል አግኝቻለሁ። እውነተኛ ታላቅ ሰው ግን እርሱ አንሶ አንተን ታላቅ መሆንህን እንዲሰማህ ያደርግሃል። አያችሁ? ነገስታቶች፡ እና የእውነት ታላላቅ የሆኑ ልዩ ልዩ ሰዎች፡ ታገኛላችሁ። ከዚያም ድሪቶዎች፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች የለበሱ፡ ግትር ክርስትያኖችም ታገኛላችሁ። እንደውም አንዳንዶቹ ተኳኩለው ወደ ፑልቢቱ ይወጣሉ… አያችሁ? ኦህ፡ ማይ! ይሁን፡ እንግዲህ… እሺ።

284 “የተሰወረ መና፡” **ልዩ** የሆነ ነገር። **ልዩ** ነገር ምንድነው? እንደ መንፈስ ቅዱስ በረከት ነውን? እንደሱ ዓይነት አይደለም… በጭራሽ፡ አይደለም፡ ያ’ማ ለመላው ጉባኤ ነው። “የተሰወረ መና” ግን ሌሎችን ማስተማር ይችል ዘንድ የሚሰጥ ልዩ መገለጥ ነው። አያችሁ? ሌሎችን ማስተማር እንዲችል፡ ስለ ቃሉ የተሰጠው የተሻለ ዕውቀት ነው። እንዲሁ መሆን አለበትና። ልክ ነው? ከፓስተርህ በላይ መሆን አትችልም። አያችሁ፡ ያን አትርሱ። ምክንያቱ… እናንተን የሚመግባችሁ እረኛ ኣርሱ ነው። እረኛ ከሆነ፡ በጎቹን—የሚመግብበት መና፡ የት እንዳለ ማወቅ አለበት። ልክ ነው? እንግዲህ፡

ልዩ ነገር ነው። ይህንንም ለአንድ ደቂቃ ብቻ ተመልከተው፡ መገለጡን፡ የተሰወረውን መና።

285 እንግዲህ፡ “ነጭ ድንጋይ፡ ነጭ ድንጋይ ይሰጠዋል።” ይህ መልአክ ነጭ ድንጋይ ይኖረዋል። ድንጋይ ነው፡ አይደል? [አንድ ወንድም፡ “ንጽሕና” አለ።—አርታዒ።] አዎን... ልክ ነው፡ “ንጽሕና።”

286 አንድ ጊዜ ስምዖን የሚባል ሰው አገኘና፡ ስሙንም—ዓለት ብሎ ለወጠው፡ “ጴጥሮስ።” ለምን? ቁልፎቹ ነበሩት። ልክ ነው? ስሙን ቀይሮ ዓለት አደረገው። ልክ ነው? ጴጥሮስ የመንግሥቱ ቁልፎች የነበረው እሱ ስለነበር ቁልፎቹን ይዞ ነበር።

287 “አዲስ ስም፡ በዚህ ድንጋይ ውስጥ የተጻፈ ከራሱ በቀር ማንም የማያውቀው አዲስ ስም።” እሱ ማን እንደሆነ ያውቃል፡ ለሌሎች መናገር ግን አይችልም። አያችሁ? አያችሁ? ከራሱ በቀር ማንም አያውቅም። አያችሁ? ጴጥሮስ ቁልፎቹ እንዳሉት ያውቃል፡ ነገር ግን ቁልፍ ስለመያዙ ሲታበይ አትሰሙትም። አያችሁ? አንድ ነገር ስለሞሆናቸው የሚታበዩ ሰዎች ባዶዎች ናቸው። ኧህ-ህህ፡ ኧህ-ህህ። “በውስጡ አዲስ ስም የተጻፈበት፡ ነጭ ድንጋይ።” የራሱ ስም ሳይሆን፡ የሌላ ሰው ነው (አያችሁ?) ድንጋዩን የተቀበለው ሰው፡ እሱ ራሱ ብቻ የሚያውቀው፡ ስም ነው። አያችሁ፡ ቤተ ክርስቲያንን የምትመግብበት ልዩ መና፡ አስታውሱ።

288 አስታውስ ይህ ነገር በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ በተፈጸመ ጊዜ፡ በዚያ በተመሳሳይ ዘመን ነበረ (ይህም የተገለጠበት በተመሳሳይ ጊዜ ነው) ኒቆላውያን በላያቸው ላይ የቤተክርስቲያና**ቸው** ራስ፡ ጳጳስ የሾሙበት፡ ከበታቹም፡ ነጭ የድንጋይ መሠዊያ፡ ከሥሩ የእብነበረድ መሠዊያ አደረጉለት። ልክ ነው? **ለእርሱም** ውድ በሆኑ ምስሶዎች፡ እና በመሰል ነገሮች፡ አስነጠፉቸው።

289 ይህ የጌታ መልአክ ግን **እርሱ**፡ ማለት የእግዚአብሄር ልጅ፡ በ—በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ማን እንደነበረ ያውቀዋል።

290 ኒቆላውያን መሪያ**ቸውን** ሹመት ሰጥተውት የእብነበረድ ድንጋይ ከእግሩ በታች—ሲያኖሩለት (አያችሁ?)፡ እግዚአብሔርም በመንፈስ-ለተሞላ መንጋው በመንፈስ-የተሞላ መሪ፡ ማለት መልአኩ አቆመላቸው፡ ለእርሱም በማሕተም የታተመ ስም ሰጠው፡ ይገልጠው ዘንድ አይገባውም። ለራሱ ጠብቆ መያዝ አለበት፡ አያችሁ። “ከእርሱ በቀር ሌላ ሰው አያውቀውም።”

291 “የተሰወረ መና፡ ድንጋይ፡ ከራሱ በቀር ማንም የማያውቀው አዲስ ስም፡” ይህም ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ ተላከ። ሉተር አውቆት ይሆን ወይ እላለሁ? ዌስሊስ አውቆት ይሆን እላለሁ? ሌሎቹ—ታላላቅ መላእክቶችስ አውቀውት ይሆን?

292 እንግዲህ፡ ዛሬም እገረማለሁ... ይህ በቅርብ ወደ ዓለም የሚመጣው፡ ወደ እኛ የሚመጣው ታላቁ የብርሃን መልአክ፡ የሚመራን፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ፡ በኃይል ይመጣል፡ እኛንም ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደርሰናል። ምናልባት እሱም አያውቅም ይሆናል፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ቀናት አንዷ ቀን ላይ ይመጣል። እግዚአብሔር እንዲታወቅ ያደርገዋል... ያስተዋውቀዋል። እግዚአብሔር ያስተዋውቀዋል፡ እንጂ እራሱን ማስተዋወቅ አይጠበቅበትም።

እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ያረጋግጣልና። ኢየሱስ እዚህ በነበረበት ጊዜ የተናገረው ይህንን ነው እነርሱ ግን አላስተዋሉም፡ አያችሁ። እንዲህ አላቸው፦ “እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ አትመኑኝ፡ እኔ ግን የአባቴን ሥራ ባደርግ፡ እናንተም እኔን ባታምኑን፡ ሰራውን እመኑ።” ልክ ነው?

293 ኦህ፡ አይደንቅም ወይ! የራዕይ መጽሐፍ። አሁን፡ አብያተ ክርስቲያናት የት እንዳሉ አያችሁ? እንዴት እንደተጨናነቁ አይታችኋል? ቤተ ክርስቲያን እዚህ እንዴት እንደወጣች አይታችኋል? አሁን፡ ጌታ ቢፈቅድ ነገ ማታ የምናየው፡ **ይህ** ዘመን ይሆናል።

294 ብዙ ስላቆየኋችሁ፡ ይቅርታ አርጉልኝ፡ ይሁን እንጂ አንዳች ነገር—እንደምታውቁ ተ—ተ—ተሰፋ አደርጋለሁ። የያዝኳቸው ማስታወሻዎችን፡ ለመጨረስ... ጥቂቶች ቀርተውኛል፡ ሶስት ወይም አራት ገጾች ይዣለሁ፡ እንግዲህ፡ እንዳንጨርስ ጊዜ የለንም፡ እየመሸ ነው፡ ከአስራ ሰባት ደቂቃ ይላል... ምንም ቢሆን ግን፡ በመጽሀፍ ውስጥ እናካትተዋለን፡ ስለዚህ እና—እና—እናገኘዋለን።

295 እሺ፡ በሙሉ ልባችሁ የምትወዱት ስንቶች ናችሁ? በሙሉ ልባችሁ የምታምኑትስ ስንቶች ናችሁ? ኦህ! እንግዲህ፡ በድርጅቶች ውስጥ ስላልሆንን ብቻ እኔ እዚህ መቆም የምችል ይመስላችኋልን— ድርጅት ስላልሆንን ብቻ እነዚህ የምናገር ይመስላችኋል? ወንድሞች ሆይ፡ አሁንስ ገባችሁ፡ እንዴ እ—እኔ ይህ ነገር (በሕይወቴ ሁሉ) ተቃውሜዋለሁን? አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው። እኔ ራሴ አልገባኝም ነበር፡ ከጥቂት ቀናት በፊት አላውቀውም ነበር። አያችሁ? ያንን እንዳደርግ ያደረገኝ ምን እንደሆነ አላውቅም፡ የቆሸሸ ኑሮ ስለሚኖሩ ሴቶች፡ እና ስለ ሌሎች ነገሮችም፡ ሁልጊዜ ለምን እንደማለቅስ አይገባኝም፡ እንጃ አላውቀውም ነበር፡ አሁን ገባኝ። አያችሁ?

296 እንግዲህ፡ እነዚህ ነገሮች የተሳሳቱ መሆናቸውን ጌታ ያውቃል። እነሆ አሁንም ከታሪክ ተጎትተዋል፡ እናም ወጥቷል... መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር... አሁን ተመልከቱ፡ እነዚህ ነገሮች እንደሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ (ከመሆናቸው በፊት) ተናግሯል። እኛም አሁን፡ ያንን እናውቀዋለን፡ አይደል? ከዚያም የዚያን ዘመን ታሪክ ወሰደን፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው በትክክል እንደተፈጸመ እንመለከታለን። ልክ ነው? እንግዲህ፡ ወደ **እኛ** ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስንወርድና እና ስለ **እኛ** ዘመን ቤተ ክርስቲያን በትንቢት የተነገሩትን፡ ስናያቸው፡ እግዚአብሔር ይሆናል ባለው መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ታምናላችሁ? ኦህ! ትፈልጉታላችሁ አይደል...

አቤቱ፡ እናፍቃለሁ እርሱን ለማየት፡ ፊቱን አየው ዘንድ፡
በዚያም የማዳን ጸጋውን ለዘላለም እዘምራለሁ፡
በክብር ጎዳናዎች ላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ፡
ድካም ሁሉ አልፎ፡ ለዘላለም ደስታ፡ ደርሼ በቤቱ።

አቤቱ፡ እናፍቃለሁ እርሱን ለማየት፡ ፊቱን... (ስንቶቻችሁ ትናፍቃላችሁ? )
በዚያም የማዳን ጸጋውን ለዘላለም እዘምራለሁ፡
በክብር ጎዳናዎች ላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ፡
ድካም ሁሉ አልፎ፡ ለዘላለም ደስታ፡ ደርሼ በቤቱ።

አሁን እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ፡ ከፊት፡ ከኋላ፡ እና በዙሪያችሁ፡ ከሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ከሁሉም ጋር፡

እየዘመርኩ ስጓዝ፡ በዚህች ምድር ላይ፡
አቤቱ፡ ነፍሳትን ወደ ቀራንዮ (ወደ ቤተ ክርስትያን ሳይሆን፡ ወደ ቀራንዮ።)፡ ወደሚፈሰው ደሙ እያሳየሁ፡
ብዙ ፍላጻዎች፡ ነፍሴን ከውጭ ከውስጥ፡ ይወጉታል፡
ጌታዬ ግን ወደ እርሱ ይመራኛል፡ አብሬው ለመሆን።

አሁን እንቁም፡-

አቤቱ፡ እናፍቃለሁ እርሱን ለማየት፡ ፊቱን እየው ዘንድ፡
በዚያም የማዳን ጸጋውን ለዘላለም...

እጃችንን ወደ ላይ እናንሳ።

... እዘምራለሁ፡
በክብር ጎዳናዎች ላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ፡
ድካም ሁሉ አልፎ፡ ለዘላለም ደስታ፡ ደርሼ በቤቴ።

297 ኦህ፡ እንዴት እንደምወደው! እንዴት እንደምወደው! ድንቅ ነው! ድንቅ ነው!

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል ነው አምላኬ፡
አቤቱ፡ ያዳንከኝ፡ የጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረቴ፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ!

የጠፋሁ ነበርኩ፡ አሁን ተገኘሁ፡ ነጻ ከኩነኔ፡
ኢየሱስ ነፃነት ሙሉ ድነት ሰጥቶኛል ለእኔ፡
ያዳንከኝ የጠበቅከኝ፡ ከሀጢያት ከእፍረቴ፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ...

ሁላችሁ፡ ድምጻችሁን ከፍ አርጋችሁ፡

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል ነው አምላኬ፡
አቤቱ፡ ያዳንከኝ፡ የጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረቴ፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ!

ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው!

ኦህ፡ ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
እሱ መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል ነው አምላኬ፡
አቤቱ፡ ያዳንከኝ፡ የጠበቅከኝ ከሀጢያት ከእፍረቴ፡
ላምልከው ድንቅ ነው፡ ስሙን ከፍ አድርጌ!

298 አብረን "ስሙ ይባረክ!" እንበል፡- [ወንድም ብራንሃም እና ጉባኤው በአንድነት ተናገሩ—አርታዒ።]፡ "ስሙ ይባረክ!" ቤዛዬ! ቤዛዬ! ነገ ምሽት፡ ሰባት ሰዓትላይ እንዳትረሱ፡ እስከዚያ ድረስ፡ እንደገና እስክትመለሱ ድረስ፡ እንዲህ አድርጉ፡-

የኢየሱስን ስም ከአንተ ጋር ይሂድ፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታና፡ ምቾት ይሰጣል… (ወንድሞች ሆይ፡ እዚህ ስላየኋችሁ ደስ ብሎኛል፡ ጌታ ይባርካችሁ።)
… በሄድክበት ሁሉ።
ውድ ስም (ውድ ስም!)፡ ኦህ ድንቅ ስም! (ኦህ ድንቅ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም (ውድ ስም!)፡ ኦህ ድንቅ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

299 አሁን ለጸሎት፡ ለመጨረሻው መዝሙር፡ ወይም፡ ለመጨረሻ ጊዜ አንገታችንን እያጎነበስን፡

ለኢየሱስ ስም እሰግዳለሁ፡
በእግሩ ስር ወድቄ… (ጌታ አምላኬ ሆይ፡ እነዚህን፡ ፈውሳቸው… )… ዘውድ እንጭንበታለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

**የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ዘመን** AMH60-1207

(The Pergamean Church Age)

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሮብ ማታ፡ ታሕሳሰ 7 ቀን፡ 1960፡ በዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org